# አዲስ ዘመን

እናድ

እሁድ 83 ዓመት ቁጥር 195 መጋቢት 15 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!


# ‹‹ከመከላከያ ሠራዊት ጋር መቆም ከኢትዮጵያ ጋር መቆም ነው››

-ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ
የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም



ፎቶ፡- ገበሁ ገብሬ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ከመከላከያ ሠራዊት ጋር መቆም ከኢትዮጵያ ጋር መቆም መሆኑን የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ገለጹ፡፡

በመከላከያ ሠራዊት እውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሠረተ "ስለ እናት ምድር" ፊልም ትናንት በዓድዋ መታሰቢያ ሙዚየም ተመርቋል፡፡

በምርቃት ሥነ ሥርዓቱ ላይ ንግግር ያደረጉት የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ እንደገለጹት፣ በሰሜን ጦርነት ወቅት መከላከያ ሠራዊቱ የጦርነት ሥነ ሥርዓትን ተከትሎ ነው የተዋጋው፡፡ ፊልሙም ይህን እውነት የሚያሳይ ነው ።

ከመከላከያ ሠራዊት ጋር መቆም ማለት ከኢትዮጵያ ጋር መቆም ነው፡፡ ያሉት ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ፤ ፊልሙም መከላከያ ሠራዊት የኢትዮጵያ የመጨረሻው ምሽግ መሆኑን ያረጋገጠ ነው፡፡ መከላከያ ሠራዊት ሁሌም ታሪክ ይሠራል፤ ታሪኩም ይሰነዳል ብለዋል፡፡

ከመከላከያ ሠራዊት ጋር መሥራት ክብር ነው ያሉት ፊልድ ማርሻሉ፤ ሁሉም ሀብት የሚያፈራው በጀግናው መከላከያ ሠራዊት የሀገር ዳር ድንበር ስለሚጠብቅ ነው፡፡ መከላከያ ሠራዊቱ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና የሁሉም ኢትዮጵያዊ ምሽግ ነው፡፡ መከላከያ አለ ማለት ሀገር አለ ማለት ነው፡፡ በአንጻሩ መከላከያ ከሌለ ሀገር እንደማይኖር ገልጸዋል፡፡

እንደ ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ገለጻ፤ መከላከያ ሠራዊቱ በሰሜን በነበረው ጦርነት የጦርነት ሥነሥርዓትን ተከትሎ የተዋጋ ነው፡፡ ጦርነቱ ከተሞችንና ዜጎችን ከጦርነት ውጭ በማድረግ የተደረገ ነው፡፡ በዚህም የወደመ ከተማም አልነበረም ብለዋል፡፡

‹‹ከመከላከያ ሠራዊት ...ወደ ገጽ 5 ዞሯል

# ክልሉ በልማትና በመልካም አስተዳደር ሥራዎች ውጤት እያስመዘገበ ነው



ፎቶ፡- ዳኜ አበራ

**ማሕሌት አብዱል**

ወልቂጤ፡- የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በአዲስ መልክ ራሱን ችሎ ከተደራጀ ስድስት ወራት ብቻ ቢሆነውም በአጭር ጊዜ ውስጥ በልማትም ሆነ በመልካም አስተዳደር ሥራዎች ውጤት እያስመዘገበ መሆኑን የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ እንዳሻው ጣሰው አስታወቁ፡፡

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ እንዳሻው ጣሰው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ የክልሉ ምሥረታ ከተከናወነ አጭር ጊዜ ቢሆንም በግብርና በተለይም በሌማት ትሩፋት መርሐ ግብር፣ በኢንቨስትመንትና ቱሪዝም መዳረሻዎች ማስፋፊያ ሥራዎች የሚበረታቱና ውጤታማ የሚባሉ ናቸው፡፡

ክልሉ በልማትና...ወደ ገጽ 5 ዞሯል

# ለስምንት ዓመታት ያለማቋረጥ በየወሩ ቦንድ የገዙት አባት

**ሳሙኤል ወንደሰን**

**ዜና ሐተታ**

የ56 ዓመት የእድሜ ባለጸጋ የሆኑት አቶ ኪሮስ አስፋው ትውልድና ነዋሪነታቸው በትግራይ ማዕከላዊ ዞን በአቢይ አዲ ከተማ ነው፡፡ የአምስት ልጆች አባት እና የሕክምና ባለሙያ ናቸው፡፡

አቶ ኪሮስን እና ዓባይ ግድብን የሚያስተሳስራቸው ትልቅ ጉዳይ አለ። ይህም ለግድቡ ሥራ የሚውል የቦንድ ግዢ ነው። አቶ ኪሮስ ለዓባይ ግድብ ግንባታ ለሦስት ዓመት በተከታታይ ቦንድ ለመግዛት ወስነው የጀመሩ ቢሆንም ግድቡን የመጎብኘት ዕድል ከገጠማቸው በኋላ ግንባታው እስኪጠናቀቅ ድረስ ቦንድ ለመግዛት ቃል ገብተዋል።

ለስምንት ዓመታት...ወደ ገጽ 5 ዞሯል

# በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሠሩ ተሽከርካሪዎችን ቁጥር ለመጨመር ዕቅድ ተይዟል

- በርካታ የነዳጅ መኪኖች ወደ ሀገር እንዳይገቡ ተከልክለዋል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በሀገሪቱ ያለውን የታዳሽ ኃይል አቅም በአግባቡ ለመጠቀም በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሠሩ ተሽከርካሪዎችን ቁጥር ለመጨመር ዕቅድ መያዙን



አቶ በርኦ ሀሰን

በኤሌክትሪክ ኃይል...ወደ ገጽ 5 ዞሯል



















# ኅብረተሰቡ ለመቄዶንያ የሚያደርገውን ድጋፍ ሊያጠናክር ይገባል

**ማሕሌት ብዙነህ**



አዲስ አበባ፡- ኅብረተሰቡ ለመቄዶንያ የአረጋውያንና የአዕምሮ ሕሙማን መርጃ ማዕከል የሚያደርገውን ድጋፍ ሊያጠናክር እንደሚገባ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ጳጳሳትና አባቶች አስታወቁ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ጳጳሳት እና አባቶች የብፁዕ አቡነ አረጋዊ 1ኛ ዓመት መታሰቢያ ምክንያት በማድረግ የመቄዶንያ የአረጋውያንና የአዕምሮ ሕሙማን መርጃ ማዕከልን በትናንትናው እለት ጎብኝተዋል።

በጉብኝቱ ወቅት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማርቆስ እንደገለፁት፤ ከራስ በማስቀደም ድጋፍ ለሚሹት የሃይማኖቱም ዋነኛ አስተምሮት ነው። በተለይም ይሄን ያህል ሰው እየመገቡ እና አስፈላጊ ነገሮችን ከሟሟላት በተጨማሪም የመኖሪያ ሕንፃ መሠራት ፈጣሪ የተጨመረበት ሥራ ነው ብለዋል።

ሁሉም ኅብረተሰብ ማዕከሉን ከመጎብኘት ጀምሮ እንደ የአቅሙ በእውቀት፣ በጊዜ እና በገንዘብ መደገፍ እንዳለበትም ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መገናኛ ብዙኃን የበላይ ጠባቂ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ማቲያስ በበኩላቸው ፤ ማዕከሉ ብሔር፣ ቋንቋ እና ሃይማኖት ሳይለይ ከትንሽ እስከ ትልቅ ላሉና ድጋፍ ለሚሹት ሁሉ የሚስተናገዱበት የተባረከ ቦታ ነው። ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ በአጠቃላይ በአራቱ ወንጌላውያን የተፃፈው ወንጌል ማሳያ ነው ብለዋል።

በማዕከሉ ውስጥ በርካታ አቅመ ደካሞች እና የአዕምሮ ሕሙማን ይገኛሉ። ለዚህም ሁሉም ልደትም ሆነ ዓመታዊ መታሰቢያዎችን በማዕከሉ ከማድረግ ጀምሮ ለዚህ መልካም ተግባር የአቅሙን እንዲረዳም ጳጳሳቱ ጥሪ አቅርበዋል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ለዚህ ትልቅ ዋጋ ያለው ተግባርም ለመቄዶንያ በፀሎት እና አስፈላጊውን እገዛ እንደምታደርግም ገልፀዋል።

የማዕከሉ መሥራች ቢኒያም በለጠ (ዶ/ር) እንደገለፀው፤ ማዕከሉ አረጋውያንን እና የአዕምሮ ሕሙማንን ከጎዳና ላይ በማንሳት አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል።

ቤተክርስቲያኒቱን ከዚህ በፊትም የተለያዩ እርዳታዎች ያደረገች መሆኑን ገልፀው፤ ለዚህም ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

ማዕከሉ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ፣ ሐረር ጨምሮ በሀገሪቱ በሚገኙ የተለያዩ አካባቢዎች 26 ቅርንጫፎችን ያሉት ሲሆን በዚህም ከ7ሺህ 500 በላይ አረጋውያን እና የአዕምሮ ሕሙማን ይገኛሉ።

በቀጣይም ማዕከሉ ቅርንጫፎችን ወደ 120 በማሳደግ ከ20 ሺህ በላይ ድጋፍ የሚሹ ዜጎችን ለመጨመር እቅድ እንዳለውም አስታውቀዋል።

በሀገሪቱ ባለው ነባራዊ ሁኔታ ምክንያት ሰዎች የሚያደርጉት ድጋፍ መቀዛቀዝ ማሳየቱን አስታውቀው፤ ይህም በማዕከሉ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እየፈጠረ ነው ብለዋል።

በመሆኑም ማንኛውም ኅብረተሰብ የሠርግ፣ ልደትና ሙት ዓመት የመሳሰሉትን በዓላትን ቢጋራ በማዕከሉ ከማክበር ጀምሮ ምግብ፣ ልብስ፣ ዳይፐር፣ ሳሙና እንዲሁም ሙያዊ ድጋፎችን በማድረግ ሰብዓዊ ኃላፊነቱን መወጣት ይገባል ብለዋል።

ማዕከሉ በአዲስ አበባ ከተማ አያት ፀበል አካባቢ ከመንግሥት ባገኘው 3 ሺህ 600 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ባለ 15 ወለል ዘመናዊ ሆስፒታል እና የአረጋውያን መኖሪያ በማስገንባት ላይ ይገኛል።

የሕንጻው የፊኒሺንግ እና ቀሪ ሥራዎች አንድ ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር እንደሚያስፈልገው ገልፀው፤ ኅብረተሰቡ ለማዕከሉ እያደረገ ያለውን ድጋፍ አጠናክሮ እንዲቀጥልም ቢኒያም (ዶ/ር )ጥሪ አቅርቧል።

የቅዱስ ፓትሪያርክ ልዩ ጽሕፈት ቤት እና የውጭ ግንኙነት መምሪያ የበላይ ኃላፊ እና የድሬዳዋና የጅቡቲ ሀገረስብከት ሊቀ ጳጳስ የነበሩት የብፁዕ አቡነ አረጋዊ (ዶ/ር ) አንደኛ ዓመት የሙት ዓመት መታሰቢያ ጉብኝት ላይ የደቡብ አፍሪካና የምሥራቅ አፍሪካ ሀገረስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ፣ የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ዩኒቨርስቲ የበላይ ፕሬዚዳንት ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ ጨምሮ ሊቃነ ጳጳሳት፣ የቤተክርስቲያኗ የየመምሪያው ኃላፊዎችና የአብያተ-ክርስቲያናት አስተዳዳሪዎች ተገኝተዋል።



አቶ አስፋው ለገሠ

## በመዲናዋ በምግብ ዋስትና ፕሮጀክት 32 ሺህ እማወራዎችና አባወራዎች ተጠቃሚ ሆነዋል

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ በምግብ ዋስትና ፕሮጀክት 32 ሺህ እማወራዎችና አባወራዎች ተጠቃሚ መሆናቸውን የአዲስ አበባ ሥራና ክህሎት ቢሮ አስታወቀ።

በአዲስ አበባ ሥራና ክህሎት ቢሮ የሥራ ስምሪትና የምግብ ዋስትና ዘርፍ ቢሮ ኃላፊ አቶ አስፋው ለገሠ ለኢፕድ እንደተናገሩት፤ በአዲስ አበባ በምግብ ዋስትና ፕሮጀክት 32 ሺህ እማወራዎችና አባወራዎች ተጠቃሚ ሆነዋል። በእያንዳንዱ ቤት በአማካይ አምስት ሰው ስለሚኖር በፕሮጀክቱ ከአንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ የመዲናዋ ነዋሪዎች በቀጥታ ድጋፍ አድርጓል።

የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች ከሚያገኙት ገቢ 20 በመቶ ሲቆጥቡ መቆየታቸውን የገለጹት አቶ አስፋው፤ ይህም የነገ ሕይወታቸውን ለማሻሻልና ለመለወጥ የሚያስችላቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ፕሮጀክቱ በዓለም ባንክና በኢትዮጵያ መንግሥት ትብብር ተግባራዊ የሚደረግ መሆኑን ጠቁመው፤ የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ እና በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ሆነው ኑሯቸውን የሚገፉ ዜጎች መሆናቸውን አቶ አስፋው ተናግረዋል፡፡

እንደ አቶ አስፋው ገለፃ፤ ለ32 ሺህ እማወራዎችና አባወራዎችም ወደ አንድ ቢሊዮን ብር የሚጠጋ የገንዘብ ድጋፍ ተደርጓል። ድጋፍ የተደረገላቸው በፕሮጀክቱ የነበራቸውን ቆይታ በቅርቡ የሚያጠናቀቅ ሲሆን በቀጣይ የሚሠሩትን እቅድ ለተቆጣጣሪ አካላት ያቀርባሉ። ከዚያም የአዋጭነት ጥናት ከተደረገ በኋላ ሥራ ፈጣሪ እንዲሆኑ እንደሚደረግ አስገንዝበዋል።

ተጠቃሚዎቹን በአካባቢ ልማት ላይ በማሳተፍ ወደ ዘላቂ ተጠቃሚነት መሸጋገር የሚያስችላቸውን ሥልጠና፣ ገንዘብና የሥራ ትሥሥር መፍጠር መቻሉን የገለጹት አቶ አስፋው፣ ይህ ሂደት ከተሞች የምግብ ዋስትናን እንዲያረጋግጡ፣ ዜጎች ተመጣጣኝ ምግብ እንዲያገኙና ተጨማሪ ገቢ የሚያገኙበት እድል እንዲኖራቸው ያደርጋል ብለዋል።

ፕሮጀክቱ ከድህነት ወለል በታች ይኖሩ የነበሩ የከተማ ነዋሪዎችን ተጠቃሚ ማድረጉን ጠቅሰው፤ ለሥራው ውጤታማነትም ከከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር እና ከዓለም ባንክ ጋር በጥምረት እየተሠራ ነው ያሉት ፡፡

አቶ አስፋው፤ ፕሮጀክቱ በተጠቃሚዎቹ ሕይወት ላይ ያመጣው ለውጥ የሚገመገምበት ሥርዓት መፈጠሩን ጠቁመዋል። በዚህም ተጠቃሚዎቹ የቁጠባ ባሕልን ማዳበር እንደቻሉ እና በተፈጠረላቸው እድል ደስተኛ መሆናቸው ተረጋግጧል ብለዋል።

# ድጋፉ በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት የተጀመረው የሪፎርም ሥራ እውን ለማድረግ የሚያስችል ነው

**ልጅዓለም ፍቅሬ**



አዲስ አበባ፡- ለትምህርት ቤቶች የተደረገው የትምህርት መርጃ ቁሳቁስ ድጋፍ በከተማው በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ላይ የተጀመረው የሪፎርም ሥራ እውን ለማድረግ የሚያስችል መሆኑ ተገለጸ፡፡

የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ "በጨዋታ የማስተማር ሥነ-ዘዴ ለደስተኛና ውጤታማ ትውልድ" በሚል መሪ ሃሳብ ለቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚውሉ የተለያዩ የትምህርት መርጃ ቁሳቁስ ድጋፍ አድርጓል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ዘላለም ሙላቱ (ዶ/ር) በርክክብ ወቅት እንደገለጹት፤ የተደረገው ድጋፍ በቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ላይ የተጀመረው የሪፎርም ሥራ እውን ለማድረግ የሚያስችል ነው፡፡

የተደረገው ድጋፍ 20 የተለያዩ ቁሳቁሶች የያዘና ከ34 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገበት ነው ያሉት ዶክተር ዘላለም፤ በአጠቃላይ በሁሉም ክፍለ ከተሞች ለተመረጡ 40 ትምህርት ቤቶች የተሰጠ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ድጋፉ ሕጻናቱ በሚገኙበት እድሜ ክልል ላይ ጠቃሚ በሆነ ሥነ-ዘዴ ማስተማር እንዲቻል መንገድ የሚከፍት መሆኑን ጠቁመው፤ ተማሪዎች አስፈላጊውን እውቀት የሚያገኙበትና ወደ አንደኛ ደረጃ ለመሸጋገር የሚያስችላቸው አዕምሯዊ ቁመና እንዲይዙ የሚያደርግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በከተማው የቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ውጤታማ ለማድረግና ብቁ ትውልድ ለማፍራት በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን የገለጹት ዶክተር ዘላለም፤ ይህንንም እውን ለማድረግ በተለይ የመምህራን ሥልጠናና የመማሪያ ግብዓት ማሟላት ወሳኝ መሆኑን ጠቁመዋል።

እንደ ዶክተር ዘላለም ገለጻ፤ የተያዘው ውጥን እውን ለማድረግ ለትምህርት ቤቶች ድጋፍ ከማድረግ በተጨማሪ 14 ሺህ መምህራን ማሠልጠን ተችሏል፡፡ የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ ከታች ጀምሮ መሥራት ያስፈልጋል ፡፡

ድጋፉ ተማሪዎች ያለ ግብዓት እጥረት እየተዝናኑ እውቀት የሚጨብጡበት ለማድረግ ያለመ መሆኑን ተናግረዋል።

አዳዲስ የመማሪያ ሥነ-ዘዴዎች በማካተት እንዲሁም ከትምህርቱ ጎን ለጎን ሕጻናቱ ባሕልን፣ እሴትንና ማኅበራዊነትን የሚያጎለብቱበት ስለመሆኑንም ነው ዶክተር ዘላለም ያመላከቱት፡፡

የቀዳማዊ ልጅነት መርሐ-ግብር እንደ ከተማ በዘጠኝ ኢኒሼቲቮች እየተተገበረ መሆኑን አመልክተው፤ ሁለቱ በትምህርት ሴክተር ውስጥ የሚተገበር መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የልደታ ክፍለ ከተማ የትምህርት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ወይዘሮ እጅጋየው አድማሱ በበኩላቸው የተደረገው ድጋፍ ቀድመው የተጀመሩት የቅድመ አንደኛ ትምህርት በጫወታ ላይ የተመሠረተ የማስተማር ሥነ-ዘዴ የሚያግዝ ነው ብለዋል፡፡

ወይዘሮ እጅጋየሁ፤ በዚህ ረገድ ክፍለ ከተማው ከባለሀብቶችና ከቀድሞ ተማሪዎች ጋር በመሆን ተጨማሪ ሥራዎችን ለመሥራት እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

የኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ የትምህርት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ገነነ ዘውዴ በበኩላቸው ድጋፉ በከተማ ደረጃ የተጀመረው የቀዳማይ ልጅነት መርሐ-ግብር የሚያጎለብት መሆኑን አመልክተው፤ የተሻለ ትውልድ መፍጠር የሚቻልበት እንደሆንም አስረድተዋል፡፡

ሕጻናቱ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ላይ ብቁ መሆን ከቻሉ ነገ የተሻለ እውቀት በመያዝ ሀገር ተረካቢ መሆን የሚችሉበት መሆኑን አቶ ገነነ ተናግረዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ነፃነቷንና ብሔራዊ ክብሯን የጠበቀች ኢትዮጵያን ለትውልድ ለማስረከብ!

ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ ዕድገት ሠላም ቀዳሚ አጀንዳ ነው። በተለይም በሠላም እጦት ምክንያት ያሰቡትን ውጥን መፈፀም ላልቻሉ፤ በድህነትና በኋላቀርነት ብዙ ዋጋ እየከፈሉ ለሚገኙ ሀገራት ለድርድር የሚቀርብ አይደለም። ምክንያቱም የዛሬን ብቻ ሳይሆን የነገ ዕጣ ፈንታቸውን የሚወስንና ቅድሚያ የሚሰጡት ሀገራዊ አጀንዳቸው በመሆኑ ነው።

ድህነትና ኋላ ቀርነት የሀገር ነፃነትን እና ክብርን የሚገዳደር ነው። በያዝነው 21ኛው ክፍለ ዘመን ያለ ኢኮኖሚ ነፃነት ራስን ሆኖ መኖር ከባድ ፈተና ነው። እንደቀደሙት ዘመናት ከዓለም ተገልሎ መኖርም ፈፅሞ አይታሰብም። እንደ ሀገር ለመቀጠል፣ ብሔራዊ ጥቅምንና ክብርን አስጠብቆ ለመጓዝ ከድህነትን እና ኋላ ቀርነትን የመውጣት ጉዳይ አልፋ እና ኦሜጋ ነው።

አባቶቻችን በብዙ የሕይወት መስዋዕትነት ነፃነታችንንና ብሔራዊ ክብራችንን አስጠብቀው፤ ከእኛው አልፈው ለመላው ጥቁር ሕዝብ የነፃነት ጮራ ፈንጥቀው አስረክበውናል። እኛ ደግሞ ይህንን በገንዘብ የማይተመን ሉዓላዊ ክብር ድህነትንና ኋላ ቀርነትን አሸንፈን በመውጣት ታፍሮና ተከብሮ የቆየውን ሉዓላዊነታችንን፣ ባሕልና እሴቶቻችንን ማስጠበቅ የሕልውና ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ ይጠበቅብናል።

በጭቃ በተለውሱ እሾሆች (ሴራዎች) ዓለም ሰብዓዊነት በጎደለው መልኩ ብዙ ዋጋ እየከፈለች ነው። በዚህ ደግሞ ከማንም በላይ በድህነት አረንቋ ውስጥ ያሉ ሕዝቦች ግንባር ቀደም ተጎጂ ናቸው። በዚህ ምክንያት የውስጥ ሠላማችንን መጠበቅ እና በሴራው ላለመጠለፍ ከምንም በላይ ቅድሚያ የምንሰጠው ብሔራዊ አጀንዳችን ልናደርገው ይገባል።

እኛ ኢትዮጵያውያን በድህነትና በኋላ ቀርነት በብዙ ተፈትነናል። ሠላም ማጣትም ትኩረታችንን በትኖት የገባንበት ማጥ ውስጥ እንድንዳክር አስገድዶናል። ከሠላም ማጣት የተነሳም እያጋጠመን ያለው ፈተና እንደ ሀገር የሕልውና አደጋ ውስጥ ከቶናል። በምላሹም ብዙ ያልተገባ ዋጋ እንድንከፍል አስገድዶናል። በዚህ የተነሳ የተፈጠረው ሀገራዊ ስብራት እና ጠባሳ ብዙ ነው።

የሀገርን ሕልውና አደጋ ውስጥ ከከተቱ ጉዳዮችና ከውስጥ ችግራችን ባልተናነሰ ደግሞ በዓለም አቀፍ መድረኮች ድምፃችን ጎልቶ እንዳይደመጥ የፈጠረው ተግዳሮት በቀላሉ የሚታይ አልነበረም። ነፃነታችንን እና ብሔራዊ ክብራችንን የቱን ያህል እንደተፈታተነው ለማስታወስ አይከብድም።

ሠላም ማጣት ብዙ ትናንቶችን አሳጥቶናል፤ ብዙ የለውጥ መነቃቃቶችን አክስሞብናል። የሴራ እና የኃይል የፖለቲካ ባሕላችን በለውጡ ማግስት አዲስ ትንሳኤ አግኝቶ ዳግም ሀገርን የግጭት አዙሪት ውስጥ ለመክተት እየተፈታተነን ነው። ለጀመርነው ልማት ስኬት ዋነኛ አቅም የሆነውን ሀገራዊ ሠላም ፈተና ውስጥ ለመጨመር እየታገለን ነው። በተለመደው መንገድ የለውጥ ሞቅታዎችን አቀዛቅዞ ብሔራዊ ድባቴ ከፈጠረም ውሎ አድሯል።

መንግሥት ለውጡ ሠላማዊ እንዲሆንና ሂደቱ እንዲቀጥል ከዋዜማው ጀምሮ የሄደበት መንገድ ተስፋ ሰጪ ነው። ይሁን እንጂ የመጣንበት ኋላቀር የፖለቲካ ባሕል በፈጠረው ትርምስ ሁኔታዎች መልካቸውን እየቀየሩ ወደ ቀደመው የግጭት አዙሪት የገባንበት አጋጣሚ ተፈጥሯል።

እንደሀገር ብዙ ያልተገቡ ዋጋዎችን ለመክፈል ተገደናል፤ በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎቻችን ለሞትና ለአካል ጉድለት ተዳርገዋል። በሚሊዮኖች የሚቆጠሩት ደግሞ ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል፤ በቢሊዮን ብር የሚቆጠር የሀገር እና የሕዝብ ሀብት ለውድመት ተዳርጓል። ከጦርነቱና ከግጭቶች ጋር በተያያዘም እንደሀገር የተፈጠረው ስብራትና በዜጎች ላይ የደረሰው ስነ ልቦናዊ ጫናም መጠነ ሰፊ ነው።

ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ የታየው የፖለቲካ ባሕላችን ተስፋ ለምናደርጋቸው ብሩህ ነገዎች የቱን ያህል ፈተና እንደሆነ በተጨባጭ ያሳየ ነው። በተለይም ድህነትን በልማት አሸንፎ ለመውጣት በትውልዶች መካከል የነበረውን እና ያለውን ተስፋ በማደብዘዝ፤ የሀገርን ሕልውና ጭምር አደጋ ውስጥ የመክተት አቅም እንዳለው ያስገነዘበን ነበር።

እዚህ ጋር አንድ ነገር ሊሰመርበት ይገባል። ዘመናትን የተሻገሩትና አሁንም የሚፈጠሩት ችግሮቻችን መገለጫቸው ቢለያይም መሠረታዊ ምንጫቸው ግን ድህነትና ኋላቀርነት መሆኑ መታወቅ አለበት። በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚያጋጥሙን ፈተናዎችም ድህነትን አሸንፈን ለመነሳት በምናደርገው ብሔራዊ መነቃቃት ምክንያት የሚፈጠሩ ናቸው። አሮጌው የፖለቲካ ባሕላችንም ቢሆን የዚህ እውነታ ነፀብራቅ ነው።

እንደ ጥላ የሚከተለንን የሠላም እጦትና እርሱ የሚፈጥረውን ድህነትና ኋላ ቀርነት በቃ ልንል ይገባል። ሴራውን በብልሃት መሻገር እና መንቃት ይጠበቅብናል። የሠላም እጦት ወደ ብሩህ ነገዎች እንዳንሻገር እየተገዳደረን ነው። በመሆኑም አሮጌ የፖለቲካ ባሕላችንን ዘመኑን በሚዋጅ የፖለቲካ አስተሳሰብ በመቀየር ሉዓላዊነታችንን፣ ብሔራዊ ጥቅማችንን እንዲሁም ሠላማችንን ማጽናት ይጠበቅብናል። ይህ ደግሞ ለመንግሥት ወይም ለተወሰኑ ቡድኖች የሚተው አይደለም፤ እያንዳንዱ ዜጋ ኃላፊነት አለበት።

በለውጡ ማግሥት የጀመርነው ድህነትን በልማት ታሪክ የማድረግ ትግል ስኬታማ ሊሆን የሚችለው ሠላማችንን መጠበቅ ስንችል ነው። በዓለም አቀፍ መድረክ ተሰሚነታችን ጎልቶ የሚወጣውና ከጫና መላቀቅ የምንችለው አስተሳሰባችን በዚህ እሳቤ ሲቀረፅ ነው። ይህ እውን እንዲሆን ደግሞ ከአሮጌ የፖለቲካ ባሕላችን መላቀቅ ይኖርብናል። ያን ግዜ አባቶቻችን በብዙ የሕይወት መስዋዕትነት እና ተጋድሎ ያስጠበቁትን ነፃነታችን፣ ብሔራዊ ክብራችንን በተሻለ መልኩ አስጠብቅን እኛም ለትውልድ ማሻገር እንችላለን!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ከረጅም ዘመን የሀገረ መንግሥት ታሪካችን ልንማር ይገባል

በጋዜጠኛና ሲኒየር የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ
ሳንዱዘር አሥራት

ነጭና ጥቁር በሚል የቀለም ልዩነት የተጫነ የፖለቲካ ርዕዮተ-ዓለም መስሎ የተቀመጠ አመለካከት በጊዜ ሂደት በዓለም ላይ ተቀባይነት እያጣ እንዲሄድ የሆነው፤ ኢትዮጵያውያን ተግዳሮቶችን ተሻግረው በዓድዋ ሠንሠለታማ ተራሮች ላይ በፈጸሙት ድልና የጥቁር ሕዝቦች የአሸናፊነት ሥነ-ልቦና ነው።

"ጉልበት ያለህ በጉልበትህ ጉልበት የሌለህ በጸሎትህ አግዘን" ተብሎ ታውጆ የነበረውን የወቅቱን ንጉሥ የዳግማዊ አፄ ምኒሊክ ሀገርን ከወረራ የመታደግ ጥሪ በአራቱም ማዕዘናት ካለ አንዳች ልዩነት ኢትዮጵያውያን በአንድነት ተቀብለው በመሪዎቻቸው አማካኝነት ሺህ ኪሎ ሜትሮችን ለስድስት ወራት በጽናት፣ ቁጭትና የሀገር ፍቅር ስሜት በባዶ እግራቸው ተጉዘው ወረራው ካጋጠመበት የዓድዋ ሠንሠለታማ ተራሮች መድረስ ችለውም ነበር።

ሀገርህን ከወራሪ መከተህ አድን ጥሪውን ተቀብሎ የከተተው ወዶ ዘማች ኃይል፣ የአገሪቱን ዳር ድንበር ጥሶ የገባውን የጣሊያን ወራሪ አስቀድመው በአምባላጌና ዶጋሊ ላይ በመግጠም ድባቅ ለመቱ ነገሥታት ትልቅ አቅም መሆን ችሏል። ወራሪን በኋላ ቀር መሣሪያ ድል በመንሳት ለጥቁሮች፣ ለካሪቢያን ሀገራትና በዓለም ላይ ለሚኖሩ ጭቁን ሕዝቦች ሁሉ እንደሚቻል ያሳየ አንጸባራቂና ፋና ወጊ ድል በዓድዋ ተራሮች ላይ የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም ተቀዳጅተዋል።

የጣሊያን ወራሪ ዘመናዊ ጦሩን አሰልፎ ማንንም አልፋ የመንካት ታሪክ ጨርሶ ወደሌላት ሉዓላዊትና ጥንታዊት ሀገር ለወረራ በመጣበት ወቅት ሀገሪቱ በተፈጥሮና በሌሎችም የውስጥ ችግሮች ውስጥ እንደነበረች የታሪክ ማስረጃዎች ያስረዳሉ።

ለአብነት ያክል ኢትዮጵያውያን እንደ ሀገር በበሽታና ረሃብ ለከፍተኛ መከራ የተዳረጉበት መሆኑን ጨምሮ በውስን ፖለቲካዊ አለመግባባቶች ሳቢያ በክፍለ ግዛት አስተዳዳሪዎችና ማዕከላዊ መንግሥቱ መካከል ቅራኔና ኩርፊያ የነበረ መሆኑንም በወቅቱ ተሰንደው የተቀመጡ የታሪክ ማስረጃዎች ያመላክታሉ፡፡

በወቅቱ የነበረው ነባራዊ ሁኔታ ይሄንን የሚያሳየን ቢሆንም፤ ኢትዮጵያውያንን በውስጥ ያጋጠማቸው ሰው ሠራሽና የተፈጥሮ ተግዳሮት በአንድነት የውጭ ወራሪን አባሮ የሀገርን ዳር ድንበርና ሉዓላዊነት ከማስከበር ለአፍታም ሊያስቆማቸውና ሁለት ጊዜ እንዲያስቡ አላደረጋቸውም።

የዓድዋን ድል በወቅቱ ሲደረጉ ከነበሩ የሕልውናና የነፃነት ትግሎች ሁሉ ለየት የሚያደርገው ኢትዮጵያውያን የዘር፣ የሃይማኖትና የአካባቢ ልዩነቶች ሳያስቆሟቸው በአንድነት ከሀገር ክብር፣ ሕልውናና ቀጣይነት ወዲያ ምንም እንደማይኖር በልኩ ተገንዝበው በዓለም ጥቁር ሕዝቦች ታሪክ አጥንታቸውን ከስክሰውና ደማቸውን አፍሰው ያዋለዱት ኢትዮጵያዊ አሸናፊነት፣ ሀገርን ለአንድ ተመሳሳይ ዓላማ ያሰለፈ እምቢተኝነት፣ ኅብረ-ብሔራዊ አንድነትና ኢትዮጵያዊ አይበገሬነትንም ያሳየ ነው፤ በዓለም ላይ ፈጽሞ ታይቶ የማይታወቅ አዲስ የጥቁር ሕዝቦች የድል ምዕራፍ ጅማሮ ተደርጎ ለቀጣይ የነፃነትና በሁሉም ረገድ አንድነትን የማረጋገጥ ትግሎች ፋና ወጊ መሆን የቻለም ነው።

ዓድዋ የአንድነት፤ የፅናትና የሕዝባዊ ቁርጠኝነት ውጤት ከመሆኑም ባለፈ የሀገር ፍቅርን ለትውልድ በሚገባ ያስተማረ የኢትዮጵያዊ አርበኝነት የድል ታሪክም ጭምር ነው፡፡ በዓድዋ ተራሮች ላይ ኢትዮጵያውያን በጣሊያን ወራሪ ኃይል ላይ በአንድነት የተቀዳጁት ድል በዓለም ላይ ለዘመናት በበላይነት ጸንተው የነበሩ ኢ-ፍትሐዊነት የተጸናወታቸው የፖለቲካ ርዕዮተ-ዓለሞችና የዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ባሕሪያት ዘመኑን በሚዋጅ መልኩ እንዲለወጡና እንዲተኩም ያስገደደም ጭምር ነው።

በዓድዋ የሕልውና ትግል ወቅት ከአንድነት በስተቀር በሀገር ልጆች መካከል ምንም አይነት መጠላለፍ ጨርሶ ያልታየበት፤ የኢትዮጵያዊ ድል አድራጊነት ዓለም ላይ ያልነበረ አዲስ አሰባሳቢ ጽንሰ ሃሳብ/ፍልስፍና መሆኑን በጥልቀት መርምረው የተረዱ በወቅቱ በየሀገራቱ ቅኝ ግዛትና ጭቆናን በልዩ ልዩ ሁኔታ ሲታገሉ የነበሩ ኃይሎች የዓድዋን ድል ፋና ወጊነትና አዲስ አሰባሳቢ ጽንሰ ሃሳብነትን ለነፃነት ትግላቸው ተጠቅመውበታል።

ለዚህም ተጨባጭ ማስረጃ የሚሆነው ኢትዮጵያኒዝም በሚል የትግል መርሕ እ.አ.አ በ1960 በርካታ የአፍሪካ ሀገራትን ጨምሮ በቅኝ ግዛት ጭቆና ውስጥ የነበሩ ሀገራት ነፃ መውጣት መቻላቸው ነው። የዓድዋ ድል የፓን አፍሪካኒዝም እሳቤን በነ ማርክስ ጋርቬይና በነ ፓትሪስ ሉሙምባ ልብ ውስጥ የተከለ መሆኑም እንዲሁ፤ ይህም ከነፃነት በኋላ የአፍሪካ ሀገራት የኢትዮጵያን ውለታ ለመግለጽ እንዲረዳቸው በብሔራዊ ሰንደቅ-ዓላማቸው ላይ የኢትዮጵያን ባንዲራ ቀለማት በተለያየ አኳኋንና አገላለጽ እየተጠቀሙበትም ይገኛሉ።

የዓድዋ ድል በርካታ የአፍሪካ ሃገራት በገዛ ክንዳቸው ታግለው ከቅኝ ግዛት ባርነት ተላቀው ነፃነታቸውን እንዲያውጁ ካስቻላቸውም በኋላ፤ በወቅቱ በአህጉሪቱ ካዛብላንካና ሞኖሮቪያ እየተባሉ በሚጠሩ የፖለቲካ ኃይሎች መካከል ያለው ልዩነት ተወግዶ በአንድነት እንዲቆሙ ያስቻለም ነው። በሁለት ጎራ ተሰልፈው የነበሩ ሀገራትና የፖለቲካ ኃይሎች በግዜው የኢትዮጵያ የወጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት አቶ ከተማ ይፍሩን ጨምሮ ባልደረቦቻቸው በአሕጉሪቱ ተዘዋውረው በፈጸሙት ዲፕሎማሲያዊ የማግባባት ሥራ በ32 ሀገራት ይሁንታና እውቅና የአፍሪካ ኅብረት በአዲስ አበባ መቀመጫውን አድርጎ እንዲመሠረትም ሆኗል።

የዓድዋ ድል ዘመናትን ተሻግሮ ከአንደኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ ማግስት፤ ኢትዮጵያ በሉዓላዊ ሀገራት ይሁንታ የተመሠረተው ሊግ ኦፍ ኔሽን ብቸኛዋ አፍሪካዊት መሥራች አባል ሀገር ሆና እ.ኤ.አ በ1923 እንድትገባ አስችሏታል። ከዓድዋ ድል በኋላ በተደረገ ድርድርና ስምምነት ጣሊያን በአዲስ አበባ በመጀመሪያ ኤምባሲዋን መክፈቷን ተከትሎ ሌሎችም የሷን ፈለግ ተከትለው መክፈት በመቻላቸው ሀገሪቱ በዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ታሪክ ቀደምትና ጥንታዊት ሆና ገና በመውጣት ብሔራዊ ጥቅሞቿን ማስከበር እንድትችልም አድርጓታል።

ኢትዮጵያውያን፣ ልክ እንደ ዓድዋ ጀግኖች ሁሉ እንደ አንድ ልብ መካሪና ቃል ተናጋሪ በአንድነት ከተግዳሮቶች ሁሉ በላይ ሆነው ለአንዲት ውድ ሀገር ሁለተናዊ ክብር መቆም ሲቻላቸውና ተጠባብቀው በተመሳሳይ የእግር እርምጃ በተጓዙባቸው ግዜያት ሁሉ፤ መንገዳቸው አጭር አስቸጋሪውም በእጅጉ ቀሏቸው እንደነበር ዓድዋን ጨምሮ ለሀገር ቀጣይነት የተደረጉ የሕልውና ትግሎች፤ በሕይወት መስዋዕትነት የተገኙ ድሎች ሕያውና ዘላለማዊ ምስክሮች ሆነው ዛሬም ይታያሉ።

መገፋፋትን በማስወገድ ለሀገር በቀል ገንቢ እሴቶቻችንና ሃይማኖቶቻችን ታምነን በጠበቀ ወንድማዊ መቻቻል ዘወትር በአንድነት መቆም ሲቻለን ብሔራዊ፣ ቀጣናዊና አሕጉራዊ እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ በዲፕሎማሲና የኢኮኖሚ ትብብር መስኮች ጥቅሞቻችንን ከማስከበር የሚያግደን እንደማይኖር በሀገረ መንግሥት ግንባታ ሂደት ያሳለፍናቸው የታሪክ ምዕራፎችና ድሎች ለቀጣይ ጉዟችን ማስረጃና/አቅም የሚሆኑን ናቸው።

እንደ ዓድዋ ድል ያሉ፣ ለሀገር ሁለንተናዊ ግንባታ የሚበጁ አሰባሳቢ ዘመኑን መዋጀት የሚችሉ አካታች ሃሳቦችን በማዋለድ፤ ድህነትና ኋላ ቀርነት ተወግዶ በሁሉም ረገድ ሀገሪቱ የተሳካ ሽግግር እንድታደርግና ብሔራዊ ክብሯ እንዲጠበቅ ማስቻል ከትውልዱ በነብስ ወከፍ በተሠማራበት ሁሉ የሚጠበቅ ኃላፊነት መሆኑ የሚያጠያይቅ አይሆንም።

አባቶች "ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው" እንዲሉ፣ የሀገሪቱን መልካም የማይወዱ ኃይሎች ከሚያደርጓቸው ተለዋዋጭ አጀንዳ ተኮር የፕሮፓጋንዳ ዘመቻዎች በመነጠል፤ በውስጥ እውነትን ከምንጩ በማረጋገጥና ሕዝባዊ አንድነትን በማጽናት በምንገኝበት ቀጣና ብሔራዊ ጥቅሞቻችንን ማረጋገጥ እንዳንችል ጎረቤቶቻችን በማስተባበር የውክልና ጦርነት የከፈቱብንን ታሪካዊ ጠላቶቻችንን በጋራ መመከት እንደሚኖርብን የቀጠናችን ተለዋዋጭ ሁኔታ ያመላክታል።

በምንገኝበት ከቀይ ባሕር እስከ ኤደን ባሕረ ሰላጤ ባለው ቀጣና የምሥራቅና የምዕራብ አውሮፓ ሀገራትን ጨምሮ የመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት ወታደራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ብልጫ ለመውሰድ የቀጣናውን ተጎራባች ሀገራት ብሔራዊ ጥቅም ባላከበረ መልኩ እያደረጉ ባለው ፉክክር በአካባቢው አዳዲስ የፀጥታ ስጋቶች እያጋጠሙ ይገኛሉ።

ኢትዮጵያ ከ30 ዓመታት በፊት የራሷን ባሕር፣ የባሕር ኃይልና ወደቦች በባለቤትነት ስታስተዳድር የነበረች ሀገር ብትሆንም በውስጥ በሀገር ብሔራዊ ጥቅም ላይ በወቅቱ በነበሩ የፖለቲካ ኃይሎች በተፈጸመ ታሪክ የማይረሳው ሴራና ከውጭ ታሪካዊ ጠላቶቻችንን ጨምሮ ሌሎችም ባደረጉት ጫና ሀገሪቱ ለበርካታ ዓመታት ከባሕሩ ከሚገኝ ጥቅምና ከቀይ ባሕር ፖለቲካ እንድትገለል ተደርጋለች።

ከሃገር ክብርና ብሔራዊ ጥቅም የሚበልጥ አይኖርምና የዲፕሎማሲና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ባለሙያዎች እንዲሁም ፖለቲከኞች፤ በጋራና በተናጠል መክረው ሀገሪቱ አስቀድሞ ወደ ነበረችበት የቀይ ባሕር ቀጣና ተመልሳ በሁሉም ረገድ ብሔራዊ ጥቅሞቿን ማስከበር የምትችል እንድትሆን እስካሁን ባለው ሀገሪቱ በቀጣናው ስትከተል ከነበረው የዲፕሎማሲ አካሄድ የተለየ አዳዲስ የፖሊሲ አማራጮችን ለመንግሥት ግብዓት አድርገው ሊያቀርቡ እንደሚገባ በበርካቶቻችን ይታመናል።

በቀጣናው የኃይል ብልጫን ለመውሰድ እየተደረጉ ባሉ ፉክክሮች ሳቢያ በአካባቢው ዘወትር ተለዋዋጭና አዳዲስ ክስተቶች ሲያጋጥሙ እየተመለከትን እንገኛለን። ይህንን ተከትሎ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅሞቿን በሚገባት ልክ ዳግም ለማስከበር እንዲቻላት አዳዲስ የዲፕሎማሲና ልዩ ልዩ የፖሊሲ አማራጮችን ተግባራዊ ማድረግ እንደሚያሻት የቀጣናው ነባራዊ ሁኔታ ከማመላከትም ባለፈ አስገዳጅ ይሆንባታል።

በዓለም የዲፕሎማሲና የኢኮኖሚ መድረክ ላይም ተደማጭነታችንን ጨምሮ ብሔራዊ ጥቅሞቻችንን በሚፈለገው ልክ ለማጎልበት፤ ከመንግሥትና ግለሰቦች ቅራኔ ባለፈ እንደ ዓድዋ ጀግኖች ሁሉ ኃይል ማሰባሰብ የሚያሻን ግዜ ላይ የምንገኝ መሆናችንን በተደጋጋሚ እየተደረገብን ያለው ዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ ጫና እንድንሰባሰብ የሚያደርገን ነው።

ሰላምን ለማጽናት ብሎም በሕዝቦች መካከል የነበረው ወንድማማችነት በይበልጥ እንዲጎለብት፤ የሀገርን ሉዓላዊነትና ቀጣይነት ባከበረ መልኩ በሁሉም ረገድ በሚስተዋሉ ችግሮቻችን ዙሪያ ሐቀኛ ውይይቶችን በማድረግ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ማስቀመጥ፣ ሕዝባዊ አንድነታችንን በማጠናከር ቀጣይ ጉዟችንን ቀላል እንደሚያደርግልን ይታመናል።

አሁን ባለንበት 21ኛው ክፍለ ዘመን ከማንኛውም የኃይል አካሄድ በተቃራኒው በውይይት ብቻ ልዩነቶችን በማጥበብ የመፍትሔ አማራጭ አሳቦችን ማዋጣት ለሀገር ብሔራዊ ጥቅምና ክብር መረጋገጥ ከቃል በላይ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለማድረግ ከሚወዱ ዜጎች ሁሉ የሚጠበቅ ነው። ‹ወንድሜ አንተ ትብስ› በሚል መርሕ መደማመጥ የሰፈነበት ውይይት በማድረግ የማናሸንፈው ጠላትና የማንፈታው ቋጠሮም የለም። ከውይይት በተቃራኒ ችግሮቻችንን ለመፍታት የሄድንባቸው ርቀቶች ከቂምና ቁርሾ ውጪ አንድም ያተረፉልን መልካም ነገር እንደሌሌ ከረጅም ዘመን የሀገረ መንግሥት ታሪካችን ልንማር ይገባል።

ዜና

# መድን ፈንድ የ2 ነጥብ 8 ቢሊዮን ብር የአረቦን ክፍያ ሰበሰበ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በተያዘው በጀት ዓመት የሁለት ነጥብ ስምንት ቢሊዮን ብር የአረቦን ክፍያ መሰብሰቡንና የኢትዮጵያ የተቀማጭ ገንዘብ መድን ፈንድ አስታወቀ፡፡ በጀት ዓመቱ መጨረሻ ስድስት ቢሊዮን ብር የአረቦን ክፍያ ለመሰብሰብ አቅዷል።

የመድን ፈንዱ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ደሳለኝ አምባው (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ ሁሉም በሥራ ላይ ያሉ የንግድ ባንኮችና አነስተኛ የፋይናስ ተቋማት በአስገዳጅነት የፈንዱ አባል ሆነዋል፡፡ አባል ተቋማቱ ከአጠቃላይ ተቀማጫቸው ላይ ዜሮ ነጥብ ሦስት በመቶ ዓመታዊ የአረቦን ክፍያ ይከፍላሉ፡፡ በዚህም በተያዘው በጀት ዓመት የመጀመሪያ ስድስት ወራት ሁለት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር የአረቦን ክፍያ ተሰብስቧል፡፡

እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻም ስድስት ቢሊዮን ብር የአረቦን ክፍያ ለመሰብሰብ ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን አመልክተው፤ የፈንዱ ዋና ዓላማ በባንኮችና በአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት ላሉ አነስተኛ አስቀማጮች ዋስትና መስጠት መሆኑን አስረድተዋል።

ዶክተር ደሳለኝ እንደጠቆሙት፤ የመድን ፈንዱ መኖር አስቀማጮች እምነት እንዲኖራቸው ያደርጋል፤ ይህም ለፋይናንሸያል ሥርዓቱ መረጋጋት ጉልህ አስተዋፅዖ ያበረክታል፡፡



ደሳለኝ አምባው (ዶ/ር)

የኢትዮጵያ የተቀማጭ ገንዘብ መድን ፈንድ አሁን ባለው አሠራር ዋስትና የሚሰጠው እስከ 100 ሺህ ብር ላሉ ዝቅተኛ አስቀማጮች መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህም በ2013 ዓ.ም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንቡ ሲፀድቅ በተደረገው ጥናት ከ95 በመቶ በላይ ቆጣቢዎች ገንዘባቸው እስከ 100 ሺህ ብር መሆኑን መነሻ በማድረግ የተወሰነ ነው ብለዋል፡፡ ይሁን እንጂ ወደፊት የሚኖሩ ነባራዊ ሁኔታዎችን ታሳቢ አድርጎ ማሻሻያ ሊደረግበት እንደሚችል ጠቁመዋል።

ዝቅተኛ ቆጣቢዎች ላይ ትኩረት የተደረገው አንድ ፋይናንስ ተቋም ላይ ጉዳት ቢደርስ በከፍተኛ ደረጃ ተጎጂ የሚሆኑትና በቀላሉ ለማገገም አዳጋች የሚሆንባቸው ዝቅተኛ ቆጣቢዎች መሆናቸው ታሳቢ ተደርጎ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

ፈንዱ የተቋቋመው አሁን ላይ ችግር የገጠመው የፋይናንስ ተቋም ኖሮ ሳይሆን ወደፊት ችግር ቢያጋጥም ቀድሞ መፍትሔ ለማስቀመጥ ታስቦ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

ተቋሙን ለማጠናከር መንግሥት የ200 ሚሊዮን ብር መነሻ ካፒታል መፍቀዱን ገልጸው፤ ከዚህ ውስጥ 50 ሚሊዮን ብሩ በመለቀቁ ጥቅም ላይ መዋሉን ተናግረዋል።

በቀጣይነትም ፈንዱን ለማጠናከር መንግሥት ከሚያደርገው ድጋፍ ባለፈ ከሁሉም ባለድርሻ አካላትና አጋሮች ጋር በትብብር እንደሚሠራ ዶክተር ደሳለኝ ጨምረው ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያ የተቀማጭ ገንዘብ መድን ፈንድ በማቋቋም በዓለም ላይ 148ኛ ሀገር መሆኗን ከተቋሙ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

## ክልሉ በልማትና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንደእርሳቸው ገለፃ፤ ክልሉ እንደተመሠረተ ዋና ተደርገውና ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ከተሠሩ ሥራዎች መካከል አመራር ማደራጀት ሥራ ሲሆን፤ ክልሉ ካሉት ሰባት ዞኖችና ሦስት ልዩ ወረዳዎች የሚመጡ አመራሮችን መለየት፣ ማደራጀት፣ ወደ ሥራ የማስገባት ሥራዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ተሠርቷል፡፡ በዚህም ከ4ሺህ 500 ያላነሱ አመራሮችን በክልል ደረጃ እንዲሁም የዞን፣ የልዩ ወረዳዎችና ከተሞች ሹማምንቶችንም የመመደብ ሥራ ደረጃ በደረጃ ተከናውኗል፡፡ በተጨማሪም በክልሉ ከ120 ሺህ በላይ የመንግሥት ሠራተኞችን በተሟላ መንገድ ወደ ሥራ ማስገባት ተችሏል፡፡

ክልሉ ሰባት ክላስተሮችን በማደራጀት ፍትሐዊ የልማት ሥራዎች እንዲሠሩ የተደረገ መሆኑን ጠቅሰው፤ በዚህም መሠረት ሆሳዕና የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር መቀመጫና የአስተዳደር ሥራዎች የሚከናወንባቸው ተቋማት መገኛ፤ ቡታጅራ የኢኮኖሚ ክላስተር፣ ወልቂጤ የመሠረተ ልማት ቢሮዎችና ምክር ቤት የሚገኝባት፣ ሃላባ የፍትሕ ተቋማት መቀመጫ፣ ዱራሜ የግብርና ሥራዎች ማዕከል፤ ወራቤ ማኅበራዊ ግልጋሎቶች ክላስተር እንዲሆኑ በመደረጉ ሁሉም ልማት እንዲመጣ በኃላፊነት እንዲሠራ ማድረጉን አመልክተዋል፡፡ ከዚህም ባሻገር ፍትሐዊ "ክላስተሮቹን የማደራጀት ሥራዎችን የመጀመሪያውና ፈታኙ ሥራችን ነበር፤ ግን ደግሞ በአጭር ጊዜ ያሳካነው ሥራ ነበር" ብለዋል፡፡

የሕዝብ መድረክ በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች በማዘጋጀት ከሕዝቡ በተነሱ ሃሳቦች ላይ በመንተራስ ለሁለት ጊዜ የመቶ ቀን እቅድ ማዘጋጀቱን ርዕሰ መስተዳደሩ ጠቅሰው፤ በዚህም ውጤታማ የሚባሉ ሥራዎችን መከወን መቻሉን ጠቁመዋል፡፡ "በክልላችን በርካታ ሥራዎች ያሉ ቢሆንም ቅድሚያ ሰጥተን ስድስት ሥራዎችን አውጥተናል፤ የመጀመሪያው ሥራ የፀጥታና ሠላም ሥራ ሲሆን በዋናነት በማረቆና መስቃን እንዲሁም ጉራጌና ቀቤና ማኅበረሰብ መካከል የግጭት መንስኤ የሆኑ ችግሮቹን በመለየት ከምንጫቸው የማድረቅ ሥራችን በስኬት የሚመዘገብ ነው" ብለዋል፡፡

እንደ አቶ እንደሻው ማብራሪያ በሁለተኛ ደረጃ ትኩረት የተሰጠው ሥራ ግብርና ሲሆን በዋናነት እንደሀገር እየተተገበረ ባለው የሌማት ትሩፋት መርሐ ግብር በሁሉም የክልሉ አካባቢዎች የበጋ መስኖ ስንዴ ልማትን ጨምሮ የወተት፣ የዶሮ፣ የንብ፣ የአቦካዶ፣ የሙዝና ሌሎች የፍራፍሬ እንዲሁም አትክልት መንደሮችን በመፍጠር ምርታማነት በከፍተኛ ደረጃ ጎልብቷል፡፡ ይህም የክልሉ ሕዝብ በምግብ እህል ራሱን እንዲችል የማድረጉ ውጥን እውን እንዲሆን ከማገዙም ባሻገር የነዋሪውን የገቢ አቅም ለማሳደግና ለወጣቶች የሥራ እድል በመፍጠር ረገድ ተጨባጭ ውጤት አምጥቷል፡፡

በተጨማሪም የክልሉን ገቢ የሚያሳድጉ የገቢ አሳባሰብ ሥርዓቱን የማዘመንና የማጠናከር ሥራ መሠራቱን ጠቁመዋል፡፡ እንዲሁም የትምህርት ጥራትን የሚያረጋግጡ፤ የጤና አገልግሎትን ተደራሽ የሚያደርጉ መርሐ ግብሮች፤ የገበያ ልማትና ኢንቨስትመንት ሥራዎች ትኩረት ተሰጥቷቸው እየተከናወኑ መሆናችውን ርዕሰ መስተዳደሩ አመልክተዋል፡፡

በተጓዳኝም በግብረ - ኃይል እየተመሩ በመከናወን ባሉት የመንገድ፣ የኤሌክትሪክ ኃይልና ውሃ መሠረተ ልማቶች ለክልሉ ሕዝብ እፎይታ እየሰጡ ስለመሆኑ አብራርተዋል፡፡ በመሆኑም በቀጣይም በክልሉ መንግሥት የተያዙ የልማት ትልሞች ሙሉ በሙሉ እውን እንዲሆኑ ሕዝቡ ድጋፉን አጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ አቅርበዋል፡፡

## ‹‹ከመከላከያ ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ከጦር ሥነ ሥርዓት ውጭ የሆኑ ወታደሮችን በሕግ እንዲጠየቁ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን በመከላከያ ሠራዊቱ ላይ የተነዛው ፕሮፖጋንዳ ይህን ያላገናዘበ መሆኑን አውስተዋል፡፡

ዓለም አቀፍ ማኅበረሰቡም በመከላከያ ሠራዊቱ ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ዘምቷል ያሉት ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ፤"ስለ እናት ምድር" ፊልም ሙሉ ለሙሉ ባይሆንም የመከላከያ ሠራዊቱን ሥነ ሥርዓትና ሐቅን ያሳያል፡፡ ከሀገር ውጭም በሎስ አንጀለስ ለሕዝብ በማሳየት ውጤት ተገኝቶበታል ብለዋል፡፡

መከላከያ ሠራዊት የብልጽግና ፓርቲ ሠራዊት አይደለም ያሉት የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታማዦር ሹም፤ ሠራዊቱን የሚያዘው ሕገ መንግስቱ በመሆኑ በሕዝብ በምርጫ የተመረጠ መንግሥትን ሠራዊቱ

## ለስምንት ዓመታት ያለማቋረጥ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

"በዚያም ወቅት የግድቡን ግዙፍነት ከተመለከትኩ በኋላ ግንባታው እስኪጠናቀቅ ድረስ ቦንድ ለመግዛት ቃል ገባሁ" የሚሉት አቶ ኪሮስ፤ የግድቡ ግንባታ ከተጀመረበት አንስቶ እስከ 2013 ዓ.ም ድረስ ያለማቋረጥ በደመወዛቸው ቦንድ ሲገዙ ቆይተዋል።

በተከታታይ ያለማቋረጥ ለ102 ወራት ቦንድ ገዝተዋል። ለግድቡ ቦንድ መግዛት ሲጀምሩ የወር ደመወዛቸው ሁለት ሺህ ብር ነበር። ከዚህም ግማሹን ማለትም አንድ ሺህ ብሩን ለዓባይ ግድብ ቦንድ ይገዙበት እንደነበር ያስታውሳሉ፡፡

የግድቡ ግንባታን ስፍራው ድረስ ሄደው ማየታቸው ጽናት እንደሆናቸው የሚናገሩት አቶ ኪሮስ፤ "የወር ደመወዜ ሲጨመርም የቦንድ ግዢውን መጠንም ጨምሬያለሁ ይላሉ፡፡ ይህንን የማደርገው ተርፎኝ አይደለም። ካለኝ ላይ የተወሰነው ገቢዬ ለሀገር ልማት እንዲውል በማሰብ ነው" ሲሉም ይገልጻሉ። እስካሁን ድረስም በጥቅሉ የ180 ሺህ ብር ቦንድ መግዛታቸውንም ተናግረዋል።

በዓል ሲደርስ ቀደም ሲል ፍየል የሚገዛ ከሆነ አሁን ደግሞ ዶሮ ገዝቼ አሳልፋለሁ። የምግብ ፍጆታን በመቆጠብ ገንዘቡን ለቦንድ ግዢ አውለዋለሁ ። ይህም ግድቡ እንዲጠናቀቅ ካለኝ ፍላጎት የመነጨ ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜም የግድቡ ግንባታ እየተጠናቀቀ በመሆኑ መደሰታቸውን ገልጸዋል።

የዓባይ ግድብ የኢትዮጵያ ሀብት፣ ጥላ እና መብራት ነው። ሁሉም ሰው በግድቡ ግንባታ ላይ በገንዘብ፣ በጉልበትና በእውቀት አስተዋፅዖ ዐሻራውን ማሳረፉንም ይናገራሉ። የግድቡ ግንባታ ሲጠናቀቅ ከኢትዮጵያ አልፎ ለጎረቤት ሀገራት ብርሃን ይሆናል። ይህም ለኢትዮጵያውያን ኩራት ነው ብለዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ የሰሜኑ ጦርነት እስከ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በየወሩ ያለማቋረጥ ቦንድ ሲገዙ ቆይተዋል። በጦርነቱ ወቅት ባንኮች ዝግ በመሆናቸው ለአራት ዓመት ቦንድ መግዛት አልቻሉም። "ይህ ሁኔታ ባይፈጠር ኖሮ ቦንድ መግዛቴን አላቋርጥም ነበር። አሁንም ቢሆን ለግድቡ ድጋፍ ለማድረግ ሁሌም ዝግጁ ነኝ" ይላሉ።

የግድብ ግንባታ መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም የመሠረት ድንጋይ ተጥሎ እንደተጀመረ የሚታወስ ሲሆን፤ የግንባታው 13ኛው ዓመት ሲታሰብ እስካሁን በዚህ ላይ የላቀ አስተዋፅዖ የነበራቸውን የምናመሰግንበት ይሆናል፡፡ ይህም በደማቅ ሥነ-ሥርዓቶች እንደሚከበር ይጠበቃል።

## በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሠሩ ተሽከርካሪዎችን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ በርካታ የነዳጅ መኪኖች ወደሀገር እንዳይገቡ መከልከላቸውም ተመላክቷል፡፡

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ በርኦ ሀሰን በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሀገሪቱን የታዳሽ ኃይል አቅም መጠቀም የሚችል የትራንስፖርት ዘርፉ ተግባራዊ ለማድረግ እየተሠራ ነው፡፡ በተለይ በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሠሩ ተሽከርካሪዎችን ቁጥር ለመጨመር ዕቅድ ተይዞ ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡

እንደ አቶ በርኦ ገለጻ፤ ከለውጡ ወዲህ መንግሥት የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ላይ ባደረገው የቀረጥ ማበረታቻና በርካታ ተሽከርካሪዎች ወደ ሀገር እየገቡ ነው።

በአሁኑ ጊዜም ከውጭ የገቡና በሀገር ውስጥ የተገጣጠሙ አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙ በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሠሩ ተሽከርካሪዎች ቁጥር ከ100 ሺህ በላይ መድረሳቸውን ተናግረዋል፡፡

መንግሥት ያደረገው የቀረጥ ማበረታቻ የባለሀብቱ ተነሳሽነትና የሀገሪቷን የታዳሽ ኃይል አቅርቦት ለማሳደግ እንዲሁም የአየር ብክለትን ለመቀነስ የሚደረገውን ጥረት ለመደገፍ እንደሚረዳም ተናግረዋል።

በሀገሪቱ ያለው የታዳሽ ኃይል አቅም ሰፊ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ያለውን የታዳሽ ኃይል በአግባቡ የሚጠቀም፣ በማኅበረሰቡ ጤናና በአካባቢ ብክለት ላይ ጉዳት የማያስከትል አረንጓዴ ትራንስፖርት በ10 ዓመቱ ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ እየሠራን ነው ብለዋል፡፡

በ10 ዓመት ውስጥ 439 ሺህ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች እና ሁለት ሺህ 335 የኃይል መሙያ ማዕከል ይኖራሉ ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ይህን ዕቅድ ለማሳካት ከሀገር ውስጥና ከውጭ ሀገራት ኩባንያዎች ጋር በጥምረት ሥራዎች እየተከናወኑ እንደሚገኙ አስረድተዋል።

ሀገሪቱ በዓመት የምታወጣውን አንድ ነጥብ አራት ቢሊዮን ዶላር የነዳጅ ወጪ ለመቀነስ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን በሀገር ውስጥ ለመገጣጠምና ከውጭ ሀገራት በስፋት ለማስገባት በትኩረት እየተሠራ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

በርካታ የነዳጅ መኪኖች ከውጭ እንዳይገቡ ተከልክለዋል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ከባድ የኢንዱስትሪ ማሽነሪዎች ማለትም ለግብርና ግብዓት፣ ለውኃ ቁፋሮና ለሌሎች መሰል አገልግሎቶች የሚውሉ መኪኖች አለመከልከላቸውን ገልጸዋል፡፡

በቀጣይም ከነዳጅ ወደ ኤሌክትሪክ ተቀይረው አገልግሎት እየሰጡ ያሉ የተሽከርካሪ አይነቶችን በመለየት ወደ ሀገር እንዲገቡ ይደረጋል ሲሉ አመልክተዋል፡፡

የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች የትራንስፖርት ዘርፉን ከነዳጅ ጥገኝነት በማላቀቅ ለነዳጅ ግዢ የሚወጣውን የውጭ ምንዛሪ ለመቀነስ ይረዳል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ዘርፉ በኢኮኖሚያዊ ዕድገት ላይ ያለው አስተዋፅዖ ከፍተኛ በመሆኑ ሚኒስቴሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ለግል ዘርፉ እያደረገ መሆኑን ገልጸዋል።

በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሠሩ ተሽከርካሪዎች ከኢኮኖሚ ጠቀሜታና ከአየር ብክለት መከላከል ባለፈ የድምፅ ብክለትን ለማስቀረትና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማፋጠን የሚረዱ መሆናቸውን አስገንዝበዋል፡፡

በነዳጅ የሚሠሩ ተሽከርካሪዎች በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ከሚያሳድሩት የኢኮኖሚ ጫና በተጨማሪም ለሕገወጥ ገበያ፣ ለአየርና ለድምፅ ብክለት ምክንያት መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡

# የኮንጎና ኮርያ ዘማቹ ጀግና

ሰላማዊት ውቤ

ወታደር ላቀው ኪዳኔ ይባላሉ። ስለ ዓደዋ አውርተው አይጠግቡም። አያቶቻቸው የዓድዋ ዘማቾች በመሆናቸው ደግሞ ፍቅሩና ስሜቱ የተለየ ነው። «ክተት ሰራዊት ምታ ነጋሪት የሚለውን የእምዬ ምኒልክን ጥሪ ሰምቶ ከአራቱም የሀገሪቱ መአዘናት እየተጠራራ የዘመተው ሁሉም ኢትዮጵያዊ ነው። እከሌ ዘምቷል፤ እከሌ አልዘመተም ለሚል ወሬ አይመችም» ሲሉም ይገልጻሉ።

ወታደር ላቀው ስለ ዓድዋ ጦርነት፤ ስለተገኘው ድል፣ ስለ ጀግኖች ኢትዮጵያዊያን ጀግንነት ታሪኩን ለሌሎች መንገር ያስደስታቸዋል። እርሳቸው የዘመቱበትን የኮንጎና ኮርያውን ጦርነት የሚያወጉት እንኳን ስለ ዓድዋው ጦርነት ብዙ ካስረዱ በኋላ ነው። በጨማታቸው መካከል ስለዓደዋ ሳያነሱ አያልፉም። ታሪኩንም ከአያቶቻቸውና ከአባታቸው ስለሰሙ ጠንቅቀው ያውቃሉ።

«ለአንዲት ኢትዮጵያ ሲሉ ጀግኖች ኢትዮጵያውያን ደማቸውን አፍስሰዋል፣ አጥንታቸውን ከስክሰዋል፣ ህይወጣቸውንም ሰጥተዋል» የሚሉት ወታደር ላቀው፤ ድሉ እጅግ ደማቅ፤አንፀባራቂና በጭቆና ስር ለነበሩት አገራት በሙሉ ብርሃን ያሳየ መሆኑንም ያብራራሉ። ድሉ «መከራን፣ ጭቆናን፣ ተገዢነትን ማሸነፍ ይቻላል፤ ነፃ መውጣት ይቻላል» የሚል አስተምህሮ ዓደዋ ተራሮች ላይ ለዘላለም እንዲቀረጽ ስለማድረጉ ፤ከሁሉም በላይ የዓድዋ ድልን ልዩና ሰርክም አዲስ የሚያደርገው መለያ ስለመሆኑ አበክረው ያስገነዝባሉ።

ሀገር ተወራለች፣ ዳር ድንበር ተጥሷል በማለት ሸማግሌ፣ አሮጊት፣ ወጣቱም ሆነ ጎልማሳው የሀገሩን ዳር ድንበርና ነፃነት ለማስከበር የተመመበት ስለመሆኑ በመረጃ እያስደገፉ ያነሳሉ። በአንድነት ተመው ግማሽ ቀን ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ጦርነቱን በድል መወጣት እንደቻሉም ይናገራሉ። ዓድዋ ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካውያን ጭምር ትልቅ ኩራት እንደሆነ ደጋግመው ይናገራሉ።

ስለዓደዋ ጦርነትና ስለተገኘው ድል አውርተው የማይጠግቡት ወታደር ላቀው፤ታሪካቸውን ለመስማት በዙሪያቸው ሰዎች ሲሰበሰቡ በጣም ይደሰታሉ። በተለይም ወታቶች በትእግስት ሲያዳምጧቸው እንደሚደሰቱ ይገልጻሉ። አንዳንዶችም ታሪክ አዋቂነታቸውንና ለትውልድም ለማስተላለፍ የሚያደርጉትን ጥረት ያደንቁላቸዋል።

እኛም ባገኘናቸው ጊዜ በወጣቶች ተከበው ያለፈውን ታሪክ ሲያወሩላቸው ነበር።ከእኛም ጋር ወግ የጀመሩት እንዲሁ ስለ ዓድዋ ታሪክ በማውሳት ነው። ታሪኩን ደግመው ለእኛ ሲያወሩ ወጣቶቹ እንደገና እንደአዲስ ነበር በትኩረት ይሰሟቸው የነበረው። ወታደር ላቀው እርሳቸውም ታሪኩን ለሌላው ሲነግሩ በስሜት ውስጥ ሆነው ነው። ታሪኩን ሲያወሩም ከ126 አመት በፊት የተፈፀመ አይመስልም። በወጋቸው መካከልም ዓይናቸውን ጨፍነው ረዘም ላለ ሰአት በተመስጠ ይቆያሉ። ታሪኩን እንዲህ በተመስጦነና በወኔ ሲያወሩ የ80 አመት የእድሜ ባለፀጋ አይመስሉም።

በዙሪያቸው ሆነው የስሟቸው የነበሩ ወጣቶችም በወኔያቸው እየተደነቁ ነበር የሚያዩዋቸው። መገረማችንን ለመግለጽ ስንተያይ ወታደር ላቀው ድንገት ከእንቅልፉ እንደባነነ ሰው የጨፈኑትን ዓይናቸውን ገልጠውና ተነቃቅተው ..የሚገርማችሁ ስምምነቱ ስውር ደባ ያለው መሆኑ እኮ ነው..ሲሉም በሰፊው የጀመሩልንን የዓደዋ ጦርነት ወግ ቀጠሉ። በውሉ አንቀፅ 17 የጣሊያንኛ ቅጅ መሠረት ኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነቷን የምታደርገው በጣሊያን በኩል እንደሆነ የሚያስገድድ መሆኑንም አነሱልን። ይሄም ኢትዮጵያ በተዘዋዋሪ በጣሊያን ሞግዚት የምትተዳደር የሚያደርጋት በመሆኑ ውሎ ሳያድር የስምምነቱ አንቀፅ 17 ውዝግብ ስለማስነሳቱም አከሉልን።

ስለ ጦርነቱ መንስኤ በሰፊው እየዘረዘሩ ያስረዱን ገብተዋል። የአንቀጽ 17ቱ መዘዝ በ1887 ዓ.ም በወርሀ መስከረም በገበያ ቀን ቅዳሜ አፄ ምኒልክ ታሪካዊውን የ «ወረ ኢሉን » ክተት አዋጅ «...አገርንና ሃይማኖት



ወታደር ላቀው ኪዳኔ

**እሳቸው ባያጋጥማቸውም አንዳንድ ባልደረቦቻቸው በእረፍት ጊዜያቸውና በሥራ ምክንያት ኮንጎ ውስጥ ያሉ የተለያዩ አካባቢዎችን የማየት ዕድሉ ነበራቸው።እሳቸው የዘመቻ ግዳጃቸውን አጠናቅቀው የተመለሱት ከዛችው ከተመደቡባት ሌዎፓልድቪል ሳይወጡ ነው**

የሚያጠፉ ጠላት ባሕር ተሻግሮ መጥቷል። እኔም የአገሬ ሰው መድከሙን አይቼ ብታገሰውም፤ እያለፍ እንደ ፍልፈል መሬት ይቆፍር ጀመር፤ አሁን ግን በእግዚአብሔር እርዳታ አገሬን አሳልፌ አልሰጠውም።ያገሬ ሰው ጉልበት ያለህ ተከተለኝ፤ ጉልበት የሌለህ በጸሎትህ እርዳኝ ፤ ...» ሲሉ ማወጃቸውን አጫውተውናል።

እንዲህም ሆኖ አፄ ምኒልክ ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት ከጦርነት ጥፋት እንጂ ልማት እንደማይተርፍ በመገንዘብ ወራሪው የጣሊያን ጦር ከግዛታቸው ለቆ እንዲወጣ ጠይቀዋል፤ ግን ቀና መልስ አላገኙም። ወራረሪው አሻፈረኝ ከማለቱ ባሻገር በዕብሪት የማይሆን ቅድመ ሁኔታ በመደርደር እሳቸውንና ሀገራቸውን ለማስፈራራት ሞክሯል። ወራሪው በእብሪትና በድፍረት ይደረድራቸው ከነበሩት ውስጥም የአፄምኒልክ ጦር ትጥቅ እንዲፈታ፣ ራስ መንገሻ እንዲታሰሩ፣ መላውን ትግሬን እንዲያስረክብ እና የጣሊያንን የበላይነት እንዲቀበል የጠየቀበት ይጠቀሳልም ይላሉ። እንደ ወታደሩ ገለፃ በዚህም ጦርነቱ አይቀሬ መሆኑ ተረጋገጠ። አፄ ምኒልክ ክተት ሰራዊት ምታ ነጋሪት አዋጁም ለመታወጅ በቃ። - - -አዋጁን ተከትሎ በአፄ ምኒልክ አዝማችነት፣ ከመላው አገሪቱ በከተቱት መኳንንትና መሳፍንት ባለሟልነት ከ100 ሺህ በላይ ወዶ ገብ የገበሬ ጦር እና 29 ሺ ፈረሰኞች በኢትዮጵያዊ አንድነት፣ ጀግንነት፣ ቆራጥነት፣ አልበገር ባይነት፣ ዳር ድንበሩን ፣ ሉዓላዊነቱን ሊያስከብር ቀፎው እንደተነካ ንብ ወደ ሰሜን መትመሙንም አብራርተውልናል ወታደር ኪዳኔ ላቀው። የተመመው ደግሞ የጎርጊስን ታቦት ይዞም ነበር። እንዳከሉልን ታድያ ወራሪው ጣሊያን የመጀመሪያውን የሽንፈት ጽዋ ተከናነበ።

በሁለት ሰዓት ውጊያ አምባላጌ ላይ ነበር ፋሽስቱ የሽንፈት ጽዋውን የተከናነበው። ንጉሰ ነገስት ሚኒልክ ከነሠራዊታቸው ወደ ሰሜን መትመማቸውን ተከትሎ የፋሽስት ጣሊያን ሰራዊት ወደ መሀል ትግሬ እንዲንቀሳቀስ ትዕዛዝ ሰጠ።የአምባላጌው አኩሪ ድል ኢትዮጵያውያን በጣሊያን ላይ የተቀዳጁት የመጀመሪያው ታላቅ ፋና ወጊ ድል መሆኑም በፍጥነት በዓለም ናኘ።

ኢትዮጵያ በብልሁና በመለኛው አፄ ምኒልክ መሪነት የተቀዳጀችው የዓደዋ ድል ከወታደራዊ ስኬቱ በላይ ሃይማኖታዊ፤ ስነ ልቦናዊና ፖለቲካዊ ፋይዳው እጅግ የጎላ ለመሆን መቻሉንም ወታደር ላቀው ኪዳኔ አውግተውናል። ኢትዮጵያውያን የውጭ ኃይልን ድል መንሳት እንደሚችሉ ያረጋገጡበት፤ የአፄ ምኒልክን ጦር የውጊያሞራል ያነቃቃ ከመሆኑ ባሻገር በአገር ውስጥም ሆነ በውጭም የንጉሡ ክብር፣ ከፍ ያለ ተቀባይነት እንዲያገኝ አስችሏል። የአፄ ምኒልክ ጦር ግስጋሴውን ቀጥሎ መቀሌን ተቆጣጠረ። ይሄን ተከትሎ ስብሀትና ሀጎስ የተባሉ ለጣሊያን ያደሩ ባንዳዎች ከድተው ለንጉሡ መግባባታቸው ለወራሪው አስደንጋጭ መርዶ ነበር። የንጉሡ ጦር በወርሀ የካቲት እኩሌታ ለዓድዋ ጥቃት ዝግጁ ሆነ። የጣሊያንና የኢትዮጵያን ጦር ወዲህና ማዶ ተፋጠጠ። የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም በተካሄደ ጦርነት የፋሽስቱ የጦር መሪውና ሌሎችም ጄኔራሎች ጦር ተሸነፈ። ሸሸ። ወደ 11ሺህ የሚጠጋ የጣሊያን ጦር ሙት፣ ቁስለኛ፣ ምርኮኛ ሆነ ፤

እኝህ በአደዋ ወኔ የተቃኙ ጀግና ወታደር ኪዳኔ ላቀው እንዳወጉን የዓደዋ ድል ኢትዮጵያ በጦርነት አውዶች በመሳተፍ ጭምር የሌሎች ሀገራትን ነፃነት በማስከበሩ ረገድ ታማኒነት እንድታገኝ አድርጓል። ወታደር ኪዳኔ ላቀው በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጥያቄ መሠረት ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ በ1951 ወደ ኮርያ እንዲዘምቱ ጥሪ ካቀረበችላቸው የቃኘው ሻለቃ ጦር ሠራዊት አባላት መካከል አንዱ ለመሆን የበቁት በዚሁ መልኩ ኢትዮጵያ ተመራጭ በመሆኗ እንደሆነም በመጠቆም ነው ወደ ራሳቸው የጀግንነት ገድል የተሸጋገሩት።

ወታደር ላቀው ከኮርያ ዘመቻ መልስ በቀጥታ ደግሞ ባልበረደ ወኔ ወደ ኮንጎ ለመዝመት የበቁ ጀግና ወታደርም ነበሩ። የ87 ዓመቱ ወታደር ላቀው እንደሚያስታውሱት ያኔ ኮርያ ሲዘምቱ ታላቅ ወንድማቸው ሙሉነህ ላቀውም አብረዋቸው ነበሩ። ስሙ በታላቅና ታናሽነት ይጠራ እንጂ ዕድሜያቸው ብዙም ርቀት አልነበረው። ኮርያ ሲዘምቱ ታላቃቸው የ17 እሳቸው ደግሞ የ15 ዓመት ዕድሜ ታዳጊዎች ነበሩ።

ሁለቱም በክቡር ዘበኛ ውስጥ ተቀጥረው ብዙም ሳይቆዩ ነው የቃኘው ሻለቃ ጦር ሠራዊት አባል በመሆን ሰላም ለማስከበር ወደ ኮርያ የዘመቱት። አባታቸውም ለረጅም ጊዜም በውትድርና ሙያ አገልግለዋል። እሳቸውና ወንድማቸው ግን በአባታቸው በቤት ውስጥ ጥብቅ የሆነ ወታደራዊ ስነስርዓት እንዲተገብሩ ተደርገው ከማደጋቸውና፤ በአካባቢውም የአባታቸውን ጀግንነት የሚመስል ወኔ ታንፀባርቃላችሁ ከመባላቸው ውጭ ልጆች በመሆናቸው ስለ ውትድርና ሙያ በጥልቀት የሚያውቁት ብዙም ዕውቀት አልነበራቸውም። በተለይ ኮርያ ሲዘምቱ ስለውጊያ የነበራቸው ዕውቀት አልነበረም።

አሁን አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ "የኢትዮጵያ ኮርያ ዘማቾች ብሔራዊ ፓርክ ተብሎ በሚጠራው ፊት ለፊት ባለውና ‹‹ዘበኛ ሰፈር››እየተባለ በሚጠራው ሰፈር ውስጥ ቀኑን ሙሉ ያሳልፉት የነበረው ኳስ በመጫወት እንደነበርም ያወሳሉ። ታድያ አንድ ቀን አባታቸው ከዚሁ ኳስ ሜዳ መጡና ሁለቱንም ወደ ከቡር ዘበኛ ወስደው አስረከቧቸው። ኳስ ጨዋታው በዚሁ ተቋጨ።ሥራ መቀጠራቸውን ሁሉ ያወቁት ይሄን አድርጉ ፤ይሄን አድርጉ የሚል ትዕዛዝ ሲሰጣቸውና ወታደራዊ ስልጠና ለመውሰድ ዝግጅት እንዲያደርጉ ሲነገራቸው ነበር።

የወንድማቸውን ለጊዜው እኛ ስንጠይቃቸው ትዝ ባይላቸውም ሥራውን ሲቀጠሩ እሳቸው የሦስተኛ ክፍል ደረጃ የቀለም ትምህርት እንደነበራቸውም

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# የኮንጎና ኮርያ...

ከ6ኛ ገጽ የዞረ

ያወሳሉ። እናም ክቡር ዘበኛ በሬዲዮ ኦፕሬተር ሙያ አሰለጠናቸውና እዛው ክቡር ዘበኛ ውስጥ መሥራት ጀመሩ።አሁን ሲያስቡት እንደሚመስላቸው አባታቸው ታናሽና ታላቅ የሆኑትን ልጆቻቸውን ከማስተማር ይልቅ ገና በታዳጊነታቸው ወደ ክቡር ዘበኛ ወስደው ያስቀጠሯቸው ደሞዛቸው 18 ብር ብቻ በመሆኑ የሚያስተምሩበት እጅ አጠሯቸው ሊሆን ይችላል።የያኔ 18 ብር የወታደር ደሞዝ ምንም እንኳን ኑሮ ርካሽ በመሆኑ ይበቃል ቢባልም ቤት ኪራይ ለመክፈል ፤ለቀለብ፤ የነሱን ተከታይ ትንንሽ ልጆች ለማስተማር በፍፁም የሚያስችል አልነበረም። በዚህ ላይ ከ18 ብሩም የሚቆራረጥ ነበር። ከተቆራረጠ በኋላም እንደገና በየጊዜው ለዚህ ለዚህ ተብሎ የሚዋጣ ገንዘብ በመኖሩ አባታቸው ቤተሰቡን ለማስተዳደር ተቸግረው እንደነበር ያስታውሳሉ። ልጆቻቸው የጀግንነት ወኔያቸውን እንዲወርሱላቸው አስበው ሊሆን እንደሚችልም ይገምታሉ።

የክቡር ዘበኛ ቅጥር የመሆናቸው ምክንያት ያም ሆነ ይህ ተረጋግጦ ባይታወቅም ታናሽና ታላቅ ወንድማማቾቹ እ.ኤ.አ በ1951 ወደ ኮርያ ዘመቱ።የዘመቱት ወታደራዊ ግዳጅ ተብሎ ብቻ ስለተጫነባቸው ብቻ ሳይሆን በሙሉ ፈቃደኝነት ነበር። ወንድማቸውም ሆኑ እሳቸው ለዘመቻው መመልመላቸው ጮቤ እስኪረግጡ አስደስቷቸው እንደነበር ያስታውሳሉ። በእርግጥ ደቡብ ኮርያን የመርዳት ተግባሩ የተቀደሰ ነው ባይ ናቸው። ከኢትዮጵያ ውጪ ያለ አገር የማየት አጋጣሚውም በራሱ እንደ ታዳጊ ወጣት የሚፈልጉት ነበር።በዚህ ሁሉ ምክንያት በወኔ ነው የዘመቱት። እንዲውም የያኔ ስሜታቸውን አሁን ላይ ሲያስቡት በቀጥታ የአባታቸውን የጀግንነት ወኔ በመውረሳቸው የተፈጠረ ነው ብለው ያምናሉ። ወታደር ላቀው ገና ከኢትዮጵያ ሲነሱ ከነበረው ጀምሮም የነበረውን የዘመቻ ሂደቱን አጫውተውናል።

ታድያ ጀግናው ወታደር እንዳወጉን እሳቸው የከባድ መሣርያ ሻምበል ከሆነው አራተኛ ሻምበል፤ታላቅ ወንድማቸው ሙሉነህ ኪዳኔ ደግሞ የደረጃ ጦር ከነበረው ሦስተኛው ሻምበል ተቀላቅለው ነው ወደ ኮርያ የዘመቱት።እሳቸው የነበሩበት የመትረየስ የ100 የሬዴዮ መገናኛ ኦፕሬተሮችን የያዘም ነበር።ይሄ እሳቸው የነበሩበት የሙቶ ለብቻው 36 ወታደሮችን አቅፎም የያዘ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ጠቅላይ ሰፈር የ100 አለ ፤የ100 81 የሚባልም ነበር። ከባድ አዳፍኔ የሙቶና በቀጥታ የሚተኮስ መሣርያ የሚያስተናግድ 75 የሚባልም ነበር። ታድያ የሻምበሉ አዛዥ ሻምበል ፀጋዬ ጣሰው ሲሆኑ የእሳቸው አለቃ ደግሞ መኮንን ወልዴ ይባላሉ። ሁሉንም አጠቃሎ የያዘው ደግሞ የቃኘው ሻለቃ ጦር ይባላል።

እናም ከዚሁ ቀድመው ገና በታዳጊነት ዕድሜያቸው በመዝመት ከተሰለፉበት የኮርያ ጦርነት ጀምረው በአጭሩ እንዳወጉን ወታደር ላቀው የዘመቻ ኮሪያ ጉዞ በየዙሩ ነው የተካሄደው። ዙሮቹ እስከ አራት ይደርሳሉ። ታድያ እሳቸውና ታላቅ ወንድማቸው የመጀመርያው ጦር ከዘመተ ብዙ ዘግይተው ነበር ወደ ዘመቻ የሄዱት።በዚህ ወቅት ተጋግሎ የነበረው ጦርነትም እየተቀዛቀዘ መጥቶ ወደ ማብቂያው እየተቃረበ ነው ማለት በሚያስችልበት ደረጃ ደርሶም ነበር ቢባል የማያስደፍር አይሆንም። በተለይ በመጀመርያውና በሁለተኛው ዙር ወደ ኮርያ የዘመቱት ኢትዮጵያዊያን ብዙ መስእዋትነት የተከፈለበት የጦርነት ውጊያ ላይ ተሳትፈዋል።

ግግር በረዶ ላይ የተቀበሩ ፈንጂዎች ከማምከን ጀምሮ በደፈጣና በሽምቅ ውጊያ በከፍተኛ ወኔ ተሳትፈዋል። ተሰውተዋል። በሁለተኛው ዙር የተጓዘውና ‹ቲሾ›በተሰኘው ከፍተኛ በረዷማ ተራራ ላይ በተደረገው ውጊያ ሁሉ በመሳተፍ የላቀ መስዕዋትነት ከፍለዋል። በጦርነቱ ማብቂያ ከአሜሪካ ወገን ሆነው ከተዋጉት ሃያ አንድ ሀገራት መካከል ሁሉም በኮሙኒስቶች እጅ የወደቁ ምርኮኛ እስረኞች የነበራቸው ሲሆኑ ኢትዮጵያ አንድም ምርኮኛ እስረኛ ያልነበራት ብቸኛ አገር የመሆኗ ምስጥርም ይሄው የሰራዊቱ ብቃትና በወኔ የመሳተፍ ጉዳይ ነው ብለው ያምናሉ።ብዙዎች የሚሰውት የተሰውትን ጓዶቻቸውን ተሸክመው ለማዳን ሲሉ እንደነበረምና ጀግንነታቸው እዚህ ድረስ የዘለቀ እንደሆነም ያክላሉ።

ታድያ ወደራሳቸው የጦርነት ዘመቻ ጉዞ መለስ ብለው ወታደሩ እንዳጫወቱን ከአዲስ አበባ ሲንቀሳቀሱ መነሻቸው የነበረው ጃንሜዳ ነበር። እዚህ የመጡት ማክ በሚባል ወታደራዊ መኪና ነው ።ከጃንሜዳ ደግሞ በባቡር ወደ ጅቡቲ አመሩ። አሁን የቀናቶቹን ቁጥር ባያስታውሱትም ከጅቡቲ ከ20 ቀናት በላይ ተጉዘው ነበር የኮሪያ ባህር በር ፑዛን የገቡት።

ቀድሞ ቢነገራቸውም ኮርያ ሲደርሱ እንዳረጋገጡት ሰሜን ኮሪያ ደቡብ ኮሪያን በመውረሯ ነው የኢትዮጵያውያኑ እገዛ ያስፈለገው። በአጭሩ ደቡብ ኮርያን መርዳት ነበር የዘመቻው ዓላማ ።ታድያ በወቅቱ ወንድማቸውና እሳቸው የተለያዩት ኮርያ ባህር በር ፑዛን ሲደርሱ ነበር።ታላቃቸው በሽምቅና ደፈጣ ውጊያ ለመሳተፍ በሚያስችለው ቡድን ተቀላቅለው ሲሄዱ እሳቸው በበኩላቸው በፑዛን ለተወሰነ ቀን አረፉና በመገናኛ ሬዴዮ ኦፕሬተር ሙያቸው ወደ ሌላ ቦታ በመሄድ ግዳጃቸውን ለመወጣት በቁ።

በኮንጎ ዘመቻ የተሳተፉት ደግሞ ከዚህ ከኮርያ ዘመቻ መልስ ነው።ታላቅ ወንድማቸው ከዓመታት ቆይታ በኋላ ከኮርያ ዘመቻ በሠላም ወደ ኢትዮጵያ ቢመለሱም በኮንጎ ዘመቻ አልተሳተፉም። እሳቸው ኮንጎ የዘመቱት ከኮርያ ዘመቻ መልስ ብዙ ራሳቸውን በትምህርት መለወጥ የሚያስችል ተግባር ሲከውኑ ቆይተው ነበር።ክቡር ዘበኛን በቅጥር ሲቀላቀሉ የትምህርት ደረጃቸውን ለማሻሻል ጥረት በማድረግ በሬዲዮ ቴክኒሻል ሙያ በዲፕሎማ ተመርቀዋል።

ከዚህ ሁሉ በኋላ ነው ዳግመኛ በኮንጎ ዘመቻ ሊሳተፉ የቻሉት። ወታደር ላቀው እዚህ ሲሳተፉም ወኔያቸው አልበረደም።በኮርያው ዘመቻ፤ ከዘመቻው ቀደም ብሎ የወሰዱት የስምንት ወር ያህል ወታደራዊ ስልጠና ከወታደሩ አባታቸው ከወረሱት የጀግንነት ዕውቀት ጋር ተዳምሮ ለኮንጎው ዘመቻ በጥሩ ሁኔታ መቅረብ የሚያስችል ዝግጅት አስታጥቋቸውም ነበር። ይሄኔ ታድያ ወታደር ላቀው በዕድሜም ቢሆን ጎልብተዋል፡፤ አስተሳሰባቸውም የዚህኑ ያህል ጨምሯል።

እዚህም ዘመቻ ሲሄዱ ከአዲስ አበባ ኢትዮጵያ የተነሱት ከተመሳሳይ ቦታ ነው።ጅቡቲ ድረስም በመርከብ ወደ ኮንጎ መጓዛቸውን ያስታውሳሉ። ከመርከብ ተራግፈው ኮንጎ ሲገቡ ያረፉባት ቦታ ትዝ ባትላቸውም ከዚህች ሥፍራ ተነስተው ወደ ኮንጎ ዋና ከተማ ሌዎፓልድቪል መጓዛቸውን ያወሳሉ። ይሄ ከተማ ቀደም ብሎ ኮንጎ ኪንሻንሳ አሁን ደግሞ ኮንጎ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ በመባል የተሰየመው ነው።እዚህ ከባድ የሚባል ጦርነት ባይኖርም አልፎ አልፎ በእርስ በእርስ ግጭት የሚቀሰቀሱና ወደ ከባድ ጦርነት ሊያመሩ የሚችሉ ችግሮች እንደነበሩ ይገልጻሉ።

አንዴ እንዴውም ይሄን የመሰለ ግጭት ተቀስቅሶ እሳቸውን ጨምሮ በሥፍራው የነበሩት ወታደሮች ግጭቱን በመቆጣጠር አብርደው ከተማይቱን ከጥፋት ያዳኑበት ሁኔታም እንደነበረ ያወሳሉ። ታድያ እዚህ ለእያንዳንዳቸው ድንኳን ተሰጥቷቸው ከዓመት በላይ ቆይተዋል። ሁለቱም ሀገራት ላይ በተሳተፉበት ዘመቻ እንደታዘቡት ፍራፍሬና አትክልት በደንብ በመኖሩ የሚበላ ነገር ችግር የለም። የታሸጉ ምግቦች በተለይም ሥጋ ነክ የሚቀርብላቸው ቢሆንም የፓስታና ሩዝ የምግብ አይነቶች፣ አትክልትና ፍራፍሬ ነበር የሚያዘወትሩት። እሳቸው ባያጋጥማቸውም አንዳንድ ባልደረቦቻቸው በእረፍት ጊዜያቸውና በሥራ ምክንያት



ኮንጎ ውስጥ ያሉ የተለያዩ አካባቢዎችን የማየት ዕድሉ ነበራቸው።እሳቸው የዘመቻ ግዳጃቸውን አጠናቅቀው የተመለሱት ከዛችው ከተመደቡባት ሌዎፓልድቪል ሳይወጡ ነው። ወንድማማቾቹ እነ መንግስቱ ነዋይና ግርማሜ ነዋይ በአፄ ኃይለስላሴ ላይ ክቡር ዘበኛ በስፋት የተሳተፈበት የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ሲያደርጉ እሳቸው እዚህች ከተማ ነበሩ። ዜናውንም እዚሁ ሆነው ነው የሰሙት። መኮንኖቹ በሙሉ ታዲያ አፄ ኃይለስላሴን የሚቃወሙና የ18 ብር ደሞዝ መሻሻል አለበት የሚል ሀሳብ የሚያራምዱ ነበሩና ይሄን የሰሙ ሰሞን በር የሚከፍቱት ሁሉ በእግራቸው ነበር። እነሱ በበኩላቸው በተለይ የመገናኛ ሬዴዮ ኦፕሬተር ክፍሉ ለአፄ ኃይለስላሴ የሚያዝንበት ሁኔታ ነበር።

ወታደሩ በዚህ ሁኔታ ግዳጃቸውን ጨርሰው ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ የክቡር ዘበኛ ቤት እንደ ፊቱ አልሆነላቸውም። የኮንጎ ዘማቾችና በመፈንቅለ መንግሥቱ ምክንያት ብዙ ሰዎች ተቀይረዋል። ስለዚህ በሬዴዮ ኦፕሬተር ሙያቸው ያገኙትን ዲፕሎማ ይዘው ፐሊፕስ ሬዴዮና ቴሌቪዥን ካምፓኒ ተቀጠሩ። ከ18 ብር ወደ 1ሺህ 200 ብር ያደገ ለውጥ ማየት በራሱ ለእሳቸው አስደሳች ነበር።

በዚህ ላይ የራሳቸው መኪና ተሰጥቷቸው በየሰው ቤት በመላካቸው እየዞሩ ሬዴዮና ቴሌቪዥን ይሰራሉ። እዚህ ካንፓኒ ለ17 ዓመታት ሰርተው ነው ጡረታ የወጡት። በዚሁ መካከል ትዳር መስርተው ለ17 ዓመት ቆይተዋል፡፤ ሆኖም የእግዚአብሄር ፈቃድ ሳይሆን ቀርቶ ልጅ ማፍራት አልቻሉም። እና በ17ዓመታቸው በቃሽኝ በቃኸኝ ተባብለው በሰላም ተለያዩ። እሳቸው ከትዳር ውጪ የወለዷቸው ሁለት ሴቶች ልጆች አሏቸው። ቢሆንም ኮርያ በመዝመታቸው የተባበሩት መንግሥታት ከሰጣቸው ከፍተኛ ብር በ2ሺህ ብር በገዙት 900 ካሬ ቦታ ላይ የተገነባ ቤት ልጆቻቸው ዶክመንቱን ከሳቸው በመውሰድ በማያውቁት ሁኔታ በራሳቸው ስም ስላዛወሩባቸው ከ300 ብር ጡረታ ውጪ ምንም ሌላ ገቢ የላቸውም። ልጆቹ በአራት ወርና ቆይቶ አንድ ሺህ ብር ሁለት ሺህ ብር በአካወንታቸው ያስገቡላቸዋል። አሁን ላይ ፍቺ ከፈፀሙ በኋላ ካገቧቸው ባለቤታቸው ጋር ጀሞ ኮሚናል ቤት ከሦስት ሺህ ብር በላይ ተከራይተው ነው ሕይወታቸውን እየገፉ የሚገኙት። 300 ብሩን የጡረታ አበላቸውን ጨምረው የቤት ኪራይና የቀለብ ወጪዎቻቸውን ለመደጎም በ87 ዓመታቸው አቅም ኖሯቸው የሚሰሩት ሥራ ባይኖርም የኮርያ መንግሥት አፍንጮ በር ናይጄሪያ ኤምባሲ አጠገብ የሚገኘውና “የኢትዮጵያ ኮርያ ዘማቾች ብሔራዊ ፓርክ “ተብሎ የተሰየመው ማህበር ጥሎ አልጣላቸውም። ይዘው የሚንቀሳቀሱትንና ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ልግዛ ቢባል ከ10ሺህ ብር በላይ የሚጠየቅበትን ከዘራ ከመስጠት ጀምሮ በተለያየ ነገር እየደገፋቸው ይገኛል። ግን በቂና ቋሚ ስላልሆነ እየተቸገሩ ነው።

አሁን ላይ እሳቸው በሕይወት ቢቆዩም አብረዋቸው ኮርያ እና ኮንጎ የዘመቱት አብዛኞቹ በህይወት አለመኖራቸውን ነው የገለጹት። በህይወት ያሉትም ጥቂቶቹም ቢሆኑ በአስቸጋሪ የኑሮ ሁኔታ ውስጥ ነው የሚገኙት። በተለይ ኮንጎ የዘመቱት ማህበር ባለመመስረታቸው ስለሌላቸው ሕይወታቸውን እንኳን የሚያቆዩበት ዕድል ሳይኖር አስታዋሽ አጥተው በመጠለያና በምግብ እንኳን በመቸገር ይሰቃያሉ። እንዲህ ለሀገር ውለታ የዋሉ ጀግኖችን በመንከባከብ ውለታቸውን መመለስ ይጠበቃል።

ኢኮኖሚ

# ባህልና ቱሪዝም

## በዲፕሎማሲና ዓለም አቀፍ ግንኙነት- የኢትዮጵያን ቱሪዝም የማሳደግ ጥረት

**ዳግም ከበደ**



ቱሪዝም በዓለም ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ እድገት እንዲመዘገብ አስተዋፆ ከሚያበረክቱ ዋና ዋና ዘርፎች መካከል አንደኛው ነው። በአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ገቢ /ጂዲፒ/ ሶስተኛ ደረጃ ላይ መቀመጡን የዓለም የቱሪዝም ድርጅት (UNWTO) ጥናት ይጠቁማል። 10 በመቶ የሚሆነው የስራ እድልና 30 በመቶ የሚሆነው የወጪ ንግድ የሚፈጠረውም በዚሁ ዘርፍ ምክንያት እንደሆነ ጥናቱ ይጠቁማል።

ቱሪዝም የዓለማችንን የኢኮኖሚ እድገት ከማፋጠኑም ባሻገር ሁሉንም በእኩልነት ለማካተትና የጋራ እድገት ለማስመዝገብ የሚያስችል አማራጭ እንደሚፈጥርም ይሄው የድርጅቱ ጥናት ያመለክታል። በዚህም ሴቶችን፣ ወጣቶችን፣ ልዩ ትኩረት የሚሹ (በአካል ጉዳትና በመሳሰሉት) ዜጎችና የተለያየ የሙያ ዘርፍ እና ክህሎት ያዳበሩ ባለሙያዎችን የሚያሳትፍ አካታች እድገት (inclusive growth) የሚያመጣ ዘርፍ ነው።

ለዘላቂ ልማት ግቦች መሳካት ዋንኛው ምሰሶ የአየር ንብረት ለውጥን በኃላፊነት መከላከል እንደሆነ ይገለፃል። በዚህ ረገድም እንደ ዓለም አቀፉ የቱሪዝም ድርጅት መረጃ ዘርፉ ከሚፈጥራቸው በጎ ተፅዕኖዎች ውስጥ አንዱ አየር ንብረት እንዲጠበቅና ተፈጥሮ እንዳይራቆት ማድረግ መሆኑን ይጠቁማል። በዚህ ሂደት ውስጥ የተፈጥሮ ቱሪዝምን በማበረታታት፣ በዓለም ቅርስነት በመመዝገብ፣ እንክብካቤ እንዲደረግ ብሎም የተፈጥሮ ሚዛን እንዲጠበቅ አዎንታዊ ድርሻ ይወስዳል።

በዛሬው ርእሳችን በስፋት የምንዳስሰው ሌላኛው የቱሪዝም አዎንታዊ ተፅእኖ በዓለም አቀፍ ገፅታ ግንባታ፣ ትብብርና ዲፕሎማሲ ላይ ያበረከተውን አስተዋፆ ነው። ዘርፉ ሀገራት ያላቸውን የተፈጥሮ፣ ታሪክ፣ ባህል እና ልዩ ልዩ የመስህብ እሴቶች በትብብር ለመጠበቅና ለማሳደግ እንዲችሉ በር ከፋች መሆኑ የዓለም የቱሪዝም ድርጅት ጥናት ያመለክታል።

ኢትዮጵያ ከዚህ ግዙፍ ዘርፍ ተጠቃሚ ለመሆን ልዩ ትኩረት መስጠቷን መንግሥት ይገልጻል፡፡ በዚህም ቱሪዝም በአጠቃላይ የ ሀገር ውስጥ ምርት እድገት (GDP) ላይ ከፍተኛ ድርሻ ካላቸው ዋና ዋና የኢኮኖሚ ምሰሶዎች (ግብርና፣ ኢንዱስትሪ፣ ማእድንና አይሲቲ) ውስጥ አንዱ ሆኖ እየተሰራበት ነው።

በዚህም በመዳረሻ ልማት፣ በቅርስ ጥገና፣ በገበያ ልማትና መስህቦችን በማስተዋወቅ ረገድ አመርቂ ውጤት እየተመዘገበ መሆኑን የቱሪዝም ሚኒስቴር መረጃ ያመለክታል። በጥቂት ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያን ቱሪዝም አቅጣጫ የቀየሩ ታላላቅ የመዳረሻ ልማት ግንባታዎች ስኬትም የዚሁ ጉዞ አካል ስለመሆናቸው በተደጋጋሚ ሲገለፅ ይደመጣል።

ኢትዮጵያ ያላትን እምቅ አቅም ለመጠቀምና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተፅእኖው ከፍ ካለው የቱሪዝም ዘርፍ ድርሻ ለመውሰድ ከሚያስችሏት እርምጃዎች ውስጥ ዋንኛው ዓለም አቀፍ አጋርነት፣ ትብብር እንዲሁም የቴክኖሎጂ ሽግግር እንደሆነ ይጠቀሳል። በዚህ ረገድ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ እየተመዘገቡ ያሉ ለውጦች መኖራቸውን የቱሪዝም ሚኒስቴር የህዝብ ግንኙነት ክፍል መሪ ስራ አስፈፃሚ አቶ ዓለማየሁ ጌታቸው ይናገራሉ። ሚኒስቴር መስሪያቤቱ ቱሪዝምን በሚመለከት ለማምጣት የታሰበውን ስር ነቀል ለውጥ የሚያግዙ ዲፕሎማሲያዊ ስራዎች ከተለያዩ አገራት ጋር እየተሰራ መሆኑንም ያመለክታሉ።

በያዝነው ዓመት ከልዩ ልዩ አገራት ጋር በቱሪዝም ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት የተሻሉ ውጤቶች መመዝገባቸውንም የሚናገሩት አቶ አለማየሁ ጌታቸው፤ በልምድና ተሞክሮ ማጋራት፣ በትብብር በመስራትና በቴክኖሎጂ ሽግግር ዙሪያ ስምምነቶች እንደተደረጉም ይገልፃሉ። በቅርቡም ሚኒስትሯ አምባሳደር ናንሲሴ ጫሊ በቼክ ሪፐብሊክ ያደረጉትን የሁለት ቀናት ግንኙነት ያነሳሉ። በዚህ የሁለትዮሽ ዲፕሎማሲያዊ የቱሪዝም ግንኙነት ጥረት ውስጥ የተገኙትን ውጤቶችም በዝርዝር ይገልፃሉ።

‹‹አምባሳደር ናሲሴ ጫሊ በቼክ ሪፐብሊክ የሁለት ቀናት የስራ ጉብኝት አድርገዋል›› የሚሉት መሪ ስራ አስፈፃሚው ጉብኝቱ በኢትዮጵያ እና በቼክ መካከል እየተጠናከረ የመጣውን የሁለትዮሽ ግንኙነት በቱሪዝም ዘርፍም ለማጠናከር ያለመ መሆኑን መግለጻቸውን ይናገራሉ። ሚኒስትሯ በቆይታቸውም ከቼክ ሪፐብሊክ የባህል ሚኒስትር ሚስተር ማርቲን ባታ ጋር ውይይት ማድረጋቸውን ጠቅሰው፤ የሁለቱ ሀገራት ጠቅላይ ሚኒስትሮች የተወያዩባቸውን አጀንዳዎች ወደ ተግባር ለመቀየር ስምምነት ላይ መድረሳቸውን ያስረዳሉ። በዚህም ብሔራዊ ሙዚየሞቻችን መካከል ያለውን ትብብር ማጠናከር እንደሚገባ በማመላከት በአፈፃፀሙ ላይ ዝርዝር ውይይት ማድረጋቸውን ተናግረዋል።

መሪ ሥራ አስፈጻሚው እንደሚሉት፤ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቱ በዋናነት ኢትዮጵያ በዘርፉ የተሻለ እድገት ካስመዘገቡና የተሻለ የአሰራር ሥርዓት ከዘረጉ ሀገራት ጋር በትብብር መስራት እንድትችል መንገድ መጥረግ መሆኑን በማንሳት የሚኒስትሯ የቼክ ሪፐብሎክ ጉዞም ይህንን ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ያብራራሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ ከዚህ መነሻ ቼክ ሪፐብሊክ ያላት ብሄራዊ ሙዚየም ከዓለም ምርጥ ሙዚየሞች መካከል አንዱ ሲሆን፣ 206 አመት እድሜ ያለው ፣ከ20 ሚልዮን በላይ የሙዚየም ስብስቦችን የያዘ በዓመትም ከአንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ጎብኝዎች በላይ የሚጎበኙት ድንቅ ሙዚየም ነው፡፡ ሚኒስትሯ የሀገሪቱ ቱሪዝምና ብሄራዊ ሙዚየም አደረጃጀት ከቼክ ሪፐብሊክ ምርጥ ተሞክሮ ለመጋራት ከብሄራዊ ሙዚየም ዳይሬክተር ጀነራል ሚስተር ሚካኤል ሉከስ ጋር ውይይት ማድረጋቸውን አቶ አለማየሁ ተናግረዋል።

‹‹የመሪዎቹን ውይይት ተከትሎ በኢትዮጵያ እና በቼክ ሪፐብሊክ ብሔራዊ ሙዚየሞች መካከል የመግባቢያ ስምምነት ተፈርሟል›› የሚሉት መሪ ስራ አስፈፃሚው፤ ይህንን ስምምነት መሬት ላይ ለማውረድ ያለመ ተጨማሪ ውይይትና ስምምነት በቱሪዝም ሚኒስትሯ አማካኝነት መደረጉን ይናገራሉ። በስምምነቱ መሰረት በአቅም ግንባታ መስክ፣ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ሙዚየም ለማዘመን በሚደረገው ጥረት እንዲሁም የተለያዩ የሙዝየም ስብስቦችን በጊዜያዊ ኤግዚቢሽን መልክ በልውውጥ በየሀገራቱ ለማሳየትና አብሮ ለመስራት መግባባት ላይ መደረሱን ይገልፃሉ። በተጨማሪም ሚኒስትሯ በዲቩር ክራሎቭ ሳፋሪ ፓርክ የሥራ ጉብኝትና ውይይት ማድረጋቸውንም አቶ አለማየሁ አስታውቀዋል።

ፓርኩ በአፍሪካ ብቻ የሚገኙትን በተለይ ዘራቸዉ የጠፋና እየጠፋ ባለ የዱር እንስሳት ዙሪያ አተኩሮ የሚሰራና ሳይንሳዊ ጥናት የሚያደርግ ሲሆን በሳፋሪው ከ2000 በላይ የዱር እንስሳት ያሉትና በዓመትም እስከ ስድስት መቶ ሺህ ሰዎች የሚጎበኙት ፓርክ ነው።

ከፓርኩ ኃላፊዎች ጋር በተደረገው ውይይት ሁለቱን ሀገሮች የበለጠ ለማስተሳሰር እንዲቻል በዱር እንስሳት ጥበቃና እንክብካቤ፣ በዘርፉ የሚደረግ ጥናት እንዲሁም ለአደጋ ለተጋለጡ የዱር እንስሳት መጠለያ ለማቋቋም በሚቻልበት ሁኔታ አብሮ ለመስራት ተስማምተዋል። ይህም በቀጣይ ከዱር እንስሳት ባለስልጣን ጋር በሚፈረም የመግባቢያ ስምምነት ወደ ስራ የሚገባ እንደሚሆን የህዝብ ግንኙነት ክፍል መሪ ሥራ አስፈፃሚው አስረድተዋል።

ኢትዮጵያ በቱሪዝም ዲፕሎማሲ በያዝነው ዓመት ውጤታማ ግንኙነት መፍጠር እንደቻለች የሚናገሩት መሪ ሥራ አስፈፃሚው፣ ተጨማሪ ማስረጃዎችን ይጠቅሳሉ። በዚህም የጆርዳን የቱሪዝም ሚኒስትር መከራም ሙስጠፋን በሀገር ውስጥ በመቀበል ሁለቱ ሀገራት በቱሪዝም ዘርፍ ያላቸውን ትብብር ለማጠናከር

> **ኢትዮጵያ ከዚህ ግዙፍ ዘርፍ ተጠቃሚ ለመሆን ልዩ ትኩረት መስጠቷን መንግሥት ይገልጻል፡፡ በዚህም ቱሪዝም በአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት እድገት (GDP) ላይ ከፍተኛ ድርሻ ካላቸው ዋና ዋና የኢኮኖሚ ምሰሶዎች (ግብርና፣ ኢንዱስትሪ፣ ማእድንና አይሲቲ) ውስጥ አንዱ ሆኖ እየተሰራበት ነው**

እና የልምድ ልውውጥ ማድረግ በሚችሉባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ከአምባሳደር ናንሲሴ ጫሊ ጋር መወያየታቸውን ይናገራሉ። በተለይም በቱሪዝም ኢንቨስትመንት፣ በፕሮሞሽን፣ በቅርስ ጥበቃ እና በጤና ቱሪዝም ላይ በጋራ ለመስራት ስምምነት ላይ መደረሱን ያስረዳሉ።

ሚኒስትሩ በኢትዮጵያ በነበራቸው ቆይታ በሀይማኖት ቱሪዝም እና ጤና ቱሪዝም ላይ በጋራ ለመስራት የሚያስችሉ ውይይቶችን ከተለያዩ ተቋማት ኃላፊዎች ጋር ማድረጋቸውንም መጥቀሳቸውን ገልጸው፣ በከተማዋ ያሉ የተለያዩ የቱሪስት መዳረሻዎችን እንዲጎበኙ ማድረግ መቻሉንም ያነሳሉ።

መሪ ሥራ አስፈጻሚው ጆርዳንና ኢትዮጵያ ለበርካታ ዓመታት የዘለቀ ጠንካራ ወዳጅነት ያላቸው ሀገራት መሆናቸውን ለሁለት ቀን በኢትዮጵያ ቆይታ ያደረጉት ሚኒስትሩ መናገራቸውን አንስተው፤ አጋርነትን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስ የቱሪዝም ዘርፍ አንዱ መሆኑን መናገራቸውን አስታውቀዋል፡፡ ሀገራቸው ከኢትዮጵያ ጋር ለመስራት ቁርጠኛ መሆኗን መግለጻቸውንም አስታውቀዋል። ከጆርዳንና ከቼክ ሪፐብሊክ ጋር የቱሪዝም ዘርፍን በተመለከተ ከተደረገው ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ባሻገር በያዝነው ዓመት ሌሎች ተጨማሪ የሁለት እዮሽ ስምምነቶች መደረጋቸውን የሚገልፁት መሪ ሥራ አስፈጻሚው፤ ለእዚህም ከቱርክ ጋር የተደረገውን ስምምነት እንደ ምሳሌነት ያነሳሉ።

የሕዝብ ግንኙነት መሪ ሥራ አስፈጻሚው፤ አምባሳደር ናንሲሴ ጫሊ ከቱር ከመጣው የልኡካን ቡድን ጋርም በጽህፈት ቤታቸው መወያየታቸውን አስታውሰው፤ የቱርክ ባለሀብቶች ወደ ኢትዮጵያ መጥተው በቱሪዝም ዘርፍ ኢንቨስት እንዲያደርጉ መጋበዛቸውን ገልጸዋል። የቡድኑ አባላትም በአቅም ግንባታ፣ በጤና ቱሪዝም፣ ቪላ ቱሪስት ማረፊያ ቦታዎች ላይ የዘርፉን ልምዳቸውን ማካፈልና የልምድ ልውውጥ የማደረግ ፍላጎት እንዳላቸው መግለጻቸውን ተናግረዋል።

ከቱርክ በተጨማሪ ዘንድሮ ከልዩ ልዩ አገራት ጋር ቱሪዝምን መሰረት ያደረጉ በርካታ ስምምነቶችና ትብብሮች መደረጋቸውን በመጥቀስም፣ የኢትዮጵያን ቱሪዝም በዓለም አቀፍ ደረጃ ለማሳደግ የጎላ ድርሻ እንዳላቸው አስታውቀዋል።

የኢትዮጵያ መንግሥት ከ10 አንዱን የሥራ እድል የመፍጠር አቅም ያለው የቱሪዝም ዘርፍ በኢኮኖሚው ላይ ጉልህ ተፅእኖ እንዲኖረው ትኩረት ሰጥቶት እየሰራበት መሆኑ ይታወቃል። በተለይ የአዳዲስ መዳረሻ ልማት ትግበራዎች ባለፉት አራትና አምስት ዓመታት ውስጥ በስፋት ተከናውነዋል። በዚህም እንደ ወንጪ፣ ጎርጎራ፣ ሃላላ ኬላ እና መሰል በተፈጥሮ ቱሪዝም ላይ ያተኮሩ አዳዲስ መዳረሻዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን የቱሪስት ፍሰት ወደ ኢትዮጵያ የመሳብ አቅም እንዳላቸው ታምኖበታል። ይሁን እንጂ ከቱሪዝም መሰረተ ልማት ግንባታው ጎን ለጎን የኢትዮጵያን የቱሪዝም ሀብቶችና መልካም እድሎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ማስተዋወቅ አስፈላጊ መሆኑን ባለሙያዎች ይመክራሉ።

አቶ ጌትነት ይግዛው በቱሪዝም ሚኒስቴር የኮንቬንሽን ቢሮ መሪ ስራ አስፈፃሚ ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት፤ መንግሥት በሁለትዮሽ ግንኙነት ፣ በባለብዙ የዲፕሎማሲ መድረኮች በመገኘት እንዲሁም በዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ የኢትዮጵያን የቱሪዝም ሀብቶች በማስተዋወቅና የቱሪስት ፍሰቱን ለማሳደግ ስትራቴጂ ቀርፆ መስራት እንዳለበት ይናገራሉ። በዚህ ጥረት ውስጥ የግል ዘርፉን በባለቤትነት ሊያሳትፍ እንደሚገባም ያስገነዝባሉ።

በኢትዮጵያ ውስጥ ከ500 በላይ ቱር ካምፓኒዎች፣ ከ700 በላይ ሆቴሎች እንዲሁም በርካታ የቱሪዝም ምርት አቅራቢዎች መኖራቸውን የጠቀሱት አቶ ጌትነት፤ እነዚህ ባለድርሻዎች የበኩላቸውን ተፅእኖ ማሳረፍ የሚችሉበት አደረጃጀት መፍጠር ቢቻል በቱሪዝም ፕሮሞሽንና ዲፕሎማሲ ሥራ ላይ ጉልህ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ገልጸውልናል።

ሚኒስትሯ አምባሳደር ናንሲሴ ጫሊ በቼክ ቆይታቸው ከሀገሪቱ የቱሪዝምና የሙዚየም ባለስልጣናት ጋር መክረዋል

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

## ሁስቱ ራሶች



ራስ መኮንን ወልደሚካኤል

**ዋለልኝ አየለ**

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በወታደርነት፣ በግዛት አስተዳዳሪነት፣ በዲፕሎማትነት... በአጠቃላይ ለሀገራቸው ሕይወታቸውን የገበሩ ብዙ ጀግኖች አሉ። እነዚህንም ጀግኖች የጀግንነት ታሪክ የፈጸሙበትን፣ የተወለዱበትን ወይም በተፈጥሮ ሞትም ሆነ በጀግንነት ሲዋጉ መስዋዕት የሆኑበትን ቀን ምክንያት በማድረግ ታሪካቸውን እናስታውሳለን። በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን ወታደር፣ ግዛት አስተዳዳሪ እና ዲፕሎማት የሆኑትን ራስ መኮንን እና በጀግንነታቸው በሁሉም ልብ ዘንድ የሚታወሱት አጼ ቴዎድሮስ የሚፈሯቸውን ራስ ዳርጌን እናስታውሳለን።

ከዚያ በፊት ግን እንደተለመደው ሌሎች የዚህ ሳምንት ክስተቶችን እናስታውስ።

ከአራት ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መጋቢት 9 ቀን 2012 ዓ.ም በ60 ዓመታት ወርቃማ የኢትዮጵያ ቆይታቸው ከ60 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ሕይወት የሰጡት አንጋፋዋ የፅንስና የማህጸን ስፔሻሊስት ሐኪም ዶክተር ኤሊኖር ካትሪን ሐምሊን አረፉ። በዚህ ውለታቸው በኢትዮጵያ ውስጥ በብዙዎች ዘንድ ሲታወሱ ይኖራሉ። የዶክተር ካትሪን ሐምሌንን ዝርዝር ታሪክ ከዚህ በፊት በሳምንቱን በታሪክ እና በሌሎች ዓምዶቻችን ጭምር በዝርዝር አይተናል።

ከ78 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መጋቢት 11 ቀን 1938 ዓ.ም ለሺህ ዘመናት የኖረውን ንጉሣዊ ሥርዓት በመቃወም፣ የተማሪዎችን ንቅናቄ በመፍጠርና አብዮት በማስጀመር፣ የብሄር ፖለቲካን በማቀንቀን የሚታወቀው ዋለልኝ መኮንን ተወለደ። ዋለልኝ፤ የብሄር ፖለቲካን በሚደግፉ ወገኖች የብሔሮችን መብት አስከብሯል በሚል የሚደነቅ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያን በብሔር በመከፋፈል ለሀገራዊ ቀውስ ምክንያት ሆኗል በሚል ከፍተኛ ወቀሳና ውግዘት ይደርስበታል። በምሁራን እና በአንዳንድ ፖለቲከኞች ደግሞ «ዋለልኝን አልተረዱትም» የሚል ክርክር አለ። ያም ሆነ ይህ ዋለልኝ መኮንን በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በተለይም የብሄር ፖለቲካን በማቀንቀን በደጋፊዎቹም በወቃሾቹም ሲታወስ ይኖራል።

ከ50 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት የካቲት 11 ቀን 1966 ዓ.ም በየካቲት ወር ተጀምሮ የነበረው አብዮት ተቀጣጥሎ መምህራን የሥራ ማቆም አድማ አደረጉ። ይህ አድማ የተማሪዎችን እና የሥራ አጥ ወጣቶችን ድጋፍ በማግኘቱ ወዲያውኑ ወደ አመጽ እና ሁከት ተሸጋገረ። የዘውዳዊውን ሥርዓት እድሜ አፋጥነው ካሳጠሩት ክስተቶች አንዱ ይኸው አድማ ነበር።

ከ52 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መጋቢት 12 ቀን 1964 ዓ.ም በአትሌትነት ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያዊ አንድነትን በማቀንቀን እና በብዙ የማህበራዊና ሀገራዊ እንቅስቃሴዎች የምትታወቀው ደራርቱ ቱሉ ተወለደች።

Marcus, Menelik II, የመርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ፣ ዕለታዊ የታሪክ ድርጊት እና የ20ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ መጻሕፍትን እንዲሁም የተለያዩ ድረ ገጾችን ዋቢ አድርገን በዝርዝር ወደምናየው የሁለቱ ራሶች ታሪክ ስንሄድ በመጀመሪያ የራስ መኮንንን እናገኛለን።

የሸዋ ንጉሥ የነበሩት የንጉሥ ሳህለሥላሴ የልጅ ልጅ ናቸው። የንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አፄ ምኒልክ የአክስት ልጅ ናቸው። እኚህ ሰው የግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ አባት ልዑል ራስ መኮንን ወልደሚካኤል ናቸው።

የዚህ ሳምንት ክስተት የሆኑት ራስ መኮንን ወልደሚካኤል ያረፉት ከ118 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መጋቢት 13 ቀን 1898 ዓ.ም ነበር።

ልዑል ራስ መኮንን ወልደሚካኤል የተወለዱት ግንቦት 1 ቀን 1844 ዓ.ም በሸዋ ግዛት አፄ፣ ጎላ ወረዳ፣ ደረፎ ማርያም በሚባል ሥፍራ ነው። ገና በወጣትነታቸው ወደ ምኒልክ ቤተ መንግሥት ሄደው ከአጎታቸው ልጅ ከንጉሥ ምኒልክ (በኋላ ንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አፄ ምኒልክ) ጋር ተዋውቀው ቤተሰባዊ ዝምድናቸውን አጸኑ።

በፀባያቸው ታጋሽና አስተዋይ እንደነበሩ የሚነገርላቸው ልዑል ራስ መኮንን ከንጉሥ ምኒልክ ጋር ጠንካራ ወዳጆች በመሆን እንደ አባትና ልጅ ይተያዩ ጀመር። የሐረርጌን ግዛት በሚገባ በማስተዳደር ለንጉሥ ምኒልክ ሀገር የማቅናት ተግባር ብርቱ አጋዥ ሆኑ። ከቤተ መንግሥት ባለሟልነት ተነስተው በዘመኑ ከንጉሥ በመቀጠል ከፍተኛ ለሆነው የ«ራስ» ማዕረግም በቁ።

ልዑል ራስ መኮንን የአጼ ምኒልክ ተወካይ በመሆን ሁለት ጊዜ ወደ አውሮፓ ሀገራት ተጉዘዋል። ወደ ኢጣሊያ በሄዱ ጊዜም የኢጣሊያ ጋዜጦች የውጫሌ ውልን ምክንያት በማድረግ ኢትዮጵያ በኢጣሊያ መንግሥት ጥገኝነት ስር እንዳለች አድርገው የሚጽፉትን ጽሑፍ በመመልከታቸው ራስ መኮንን ተቃውሟቸውን ለኢጣሊያ መንግሥት ከነገሩ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው የውሉን መበላሸት ለአጼ ምኒልክም አሳውቀዋል።

የውጫሌ ውል ያስከተለው የትርጉም ለውጥ መፍትሄው ጦርነት ሲሆንም ልዑል ራስ መኮንን ሠራዊታቸውን ይዘው ከአምባላጌ እስከ ዓድዋ በተደረጉት ውጊያዎች ላይ በመሳተፍ ታሪክ የማይዘነጋው ታላቅ ጀግንነታቸውን አስመስክረዋል። ልዑል ራስ መኮንን ከቤተ መንግሥት ባለሟልነት ጀምረው በወታደርነት፣ በጦር መሪነት፣ በግዛት አስተዳዳሪነትና በዲፕሎማትነት በፈጸሟቸው አኩሪ ተግባራት ምክንያት ንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አጼ ምኒልክ የዙፋናቸው ወራሽ እንደሚያደርጓቸውም ይወራ ነበር።

ነገር ግን ምኒልክ ያሰቡት ሳይሆን ቀረና ልዑል ራስ መኮንን መጋቢት 13 ቀን 1898 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። ሞታቸው በንጉሰ ነገሥቱ ቤተ መንግሥት (አዲስ አበባ) በተሰማ ጊዜም ከፍተኛ ሀዘን ሆነ። ንጉሥ ንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አፄ ምኒልክም አምርረው አለቀሱ። በወቅቱም ይህንን የተመለከቱ ሰዎች እንዲህ ብለው ገጠሙ።

«ዋ! አጤ ምኒልክ እግዚአብሔር ያጥናዎ፣
በየበሩ ቋሚ ከልካይ ሞተብዎ።
ሲታሰር አየነው ብረቱ ሲመታ፣
ምን ዋስ አገኘና ሐረርጌ ተፈታ።
ጃንሆይ ምኒልክ ጠጉራቸው ሳሳና በራ ገለጣቸው፣
እንግዲህ ንጉሡ ምን ራስ አላቸው።»

ከአልቃሾቹ መካከል አንደኛው ደግሞ የልዑል ራስ መኮንንን ደግነት ለማስታወስ እንዲህ ብሎ ሙሾ አወረደ።

**«ስልከኛው ሲያረዳ ነገር ተሳሳተው፣**

*መኮንን አይደለም ድሀ ነው የሞተው።»*

ተብሎላቸዋል። «እንግዲህ ንጉሡ ምን ራስ አላቸው!» የሚለው ሰምና ወርቅ ያለው መሆኑ ነው። ራስ መኮንን ከውጫሌ ውል ጀምሮ እስከ ዓድዋ ጦርነት ድረስ የነበራቸው ዲፕሎማሲያዊ ጥበብ እና የጦር ጀግንነት ለአጼ ምኒልክ ትልቅ ቦታ ነበረው። ስለዚህ አጼ ምኒልክ የራስነት ማዕረግ ያለው አንድ ትልቅ ሰው አጡ ማለት ነው።

ዲፕሎማቱ፣ የግዛት አስተዳዳሪውና ወታደሩ ራስ መኮንንም እነሆ በታሪክ ሲታወሱ ይኖራሉ።

## በአጼ ቴዎድሮስ የተፈሩት ራስ ዳርጌ

**ዋለልኝ አየለ**



ራስ ዳርጌ ሳህለሥላሴ

የንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አጤ ምኒልክ አጎት የሆኑትና በጀግንነታቸው ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስን ጭምር ያስጨነቁትና ያስደነቁት ርዕሰ መኳንንት ራስ ዳርጌ ሳህለሥላሴ ያረፉት ከ124 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት መጋቢት 15 ቀን 1892 ዓ.ም ነበር።

ራስ ዳርጌ ሳህለሥላሴ የሸዋው ንጉሥ የንጉሥ ሳህለሥላሴ ወሰን ሰገድ ልጅ ናቸው። ራስ ዳርጌ የደጃዝማች አስፋው፣ የደጃዝማች ደስታ፣ የፊታውራሪ ሸዋረገድ፣ የወይዘሮ ትሰሜ፣ የወይዘሮ አስካለ፣ የወይዘሮ ፀሐየወርቅ እና የልጅ ጉግሳ አባት ናቸው። ወይዘሮ ትሰሜ ዳርጌ የልዑል ራስ ካሣ ኃይሉ እናት ናቸው።

ራስ ዳርጌ ሳህለሥላሴ የንጉሥ ኃይለመለኮት ሳህለሥላሴ (የንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አጤ ምኒልክ አባት ማለት ነው) ወንድም ናቸው። በ1822 ዓ.ም ሸዋ ውስጥ የተወለዱት ራስ ዳርጌ ሳህለሥላሴ፣ የልጅነት ጊዜያቸውን በአንኮበርና በአንጎለላ አሳልፈው ወደ ጎንደር ተጉዘው በነበሩበት ወቅት በሰላይነት ተጠርጥረው ታስረው ነበር።

ይሁን እንጂ ራስ ዳርጌ ንፁህነታቸው ታውቆ ነፃ ከወጡ በኋላ በመልካም ጠባያቸውና በጦር ሜዳ ጀግንነታቸው በንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አጤ ቴዎድሮስ ዘንድ ተወዳጅነትን አተረፉ። በዚህም ምክንያት ንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አጤ ቴዎድሮስ ራስ ዳርጌን «ዳሩ»፣ «ዳርዬ» እያሉ ይጠሯቸው ነበር።

የርዕሰ መኳንንት ራስ ዳርጌ ሳህለሥላሴ ጀግንነት ንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አጤ ቴዎድሮስን ጭምር ያስጨነቀ ነበር። በንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አጤ ቴዎድሮስ ጊዜ ሸዋን ይገዙ የነበሩት መርዕድ አዝማች ኃይሌ ንጉሰ ነገሥቱን በመክዳት ተጠርጥረው ታስረው ነበር።

ዳግማዊ አጤ ቴዎድሮስም አቤቶ ዳርጌን የሸዋ ገዢ አድርገው እንደሾሙ ተናገሩ፤ ነገር ግን ዳግማዊ አጤ ቴዎድሮስ የራስ ዳርጌን የጦር ሰፈር ሲመለከቱት በጣም የደመቀና የተደራጀ ስለነበር በጣም ተጨነቁ። ንጉሰ ነገሥቱም አቤቶ ዳርጌን አስጠርተው «ዳሩዬ ፈራሁህ! በጥንድ ጦር የሚስተውን ኃይሌን ሽሬ በነጠላ ጦር ደርበህ ሁለት ሰው የምትገለውን አንተን በሸዋ ላይ አልሾምም» ብለው በግልጽ ነገሯቸው። ራስ ዳርጌም የመከፋትና የቅሬታ ምልክት ሳያሳዩና ሳይከፉ «እሺ» ብለው ዳግማዊ አጤ ቴዎድሮስን በትህትና እጅ ነሱ።

ልጅ ምኒልክ (በኋላ ንጉሥ ምኒልክ፣ ከዚያም ንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አጤ ምኒልክ) ከመቅደላ አምልጠው ሸዋ በገቡና በአባታቸው ዙፋን በተቀመጡ ጊዜም፣ ራስ ዳርጌ ወደ ትውልድ አካባቢያቸው ወደ ሸዋ ተመልሰው ከምኒልክ ጋር ተገናኙ። ምኒልክም ሸዋ ገብተው በአባቶቻቸው አልጋ ተተክተው የሸዋ ንጉሥ ሆነው ነበርና ራስ ዳርጌ እንደመጡ «እርስዎ ቀጥታ የንጉሥ ሳህለሥላሴ ልጅ ስለሆኑ ንጉሥነቴን ልተውልዎ» ብለው ጠየቋቸው።

ራስ ዳርጌም «አይሆንም! አባታችን ሳህለሥላሴ አልጋቸውን አውርሰው የሞቱት በቀጥታ ለአንተ አባት ለንጉሥ ኃይለመለኮት ነው፤ አሁንም የነጋሲነት መስመሩ በዚያው ባንተ በኩል ነው መቀጠል ያለበት» ብለው ንግሥናውን እንደማይፈልጉ ተናገሩ። ከዚያ በኋላም ራስ ዳርጌና ንጉሰ ነገሥት ምኒልክ እንደአባትና ልጅ ሆነው ከ30 ዓመታት በላይ ዓመታት ኖሩ።

ርዕሰ መኳንንት ራስ ዳርጌ ሳህለሥላሴ የተለያዩ አካባቢዎችን በማቅናትና በማስተዳደር ስራ ውስጥ የላቀ ድርሻ ነበራቸው። ከእነዚህ አካባቢዎች መካከል አርሲ እና ሰላሌና አካባቢው ይጠቀሳሉ። ንጉሰ ነገሥት አጤ ዮሐንስ 4ኛ እና ንጉሥ ምኒልክ በተቀያየሙ ጊዜም አስታራቂ ሽማግሌ ሆነው ያገለገሉት ርዕሰ መኳንንት ራስ ዳርጌ ሳህለሥላሴ ነበሩ። ንጉሰ ነገሥት አጤ ዮሐንስ 4ኛ እና ንጉሥ ምኒልክ ደብዳቤ የሚጻጻፉት በርዕሰ መኳንንት ራስ ዳርጌ ሳህለሥላሴ በኩል ነበር። ደጃዝማች መሸሻ ሰይፉ በሸፈቱ ጊዜም ተቆጭው፣ አስማሚውና መካሪው ርዕሰ መኳንንት ራስ ዳርጌ ሳህለሥላሴ ነበሩ።

በዓድዋ ጦርነት ወቅትም ንጉሰ ነገሥት ዳግማዊ አጤ ምኒልክ ለጦርነቱ ወደ ዓድዋ በተጓዙበት ወቅት የንጉሰ ነገሥቱን ቦታ ተክተው ዙፋኑን የጠበቁትና አገር ያስተዳደሩት ርዕሰ መኳንንት ራስ ዳርጌ ሳህለሥላሴ ነበሩ።

በመልካም ጠባያቸው፣ በታማኝነታቸው፣ በበጎ አሳቢነታቸውና በጦር ጀግንነታቸው የሚታወቁት ርዕሰ መኳንንት ራስ ዳርጌ ሳህለሥላሴ መጋቢት 15 ቀን 1892 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተው ሥርዓተ ቀብራቸውም በደብረ ሊባኖስ ገዳም ተፈጽሟል።

ከላይ ያየናቸው ሁለቱ ራሶች (ራስ መኮንን እና ራስ ዳርጌ) ሁለቱም የዚህ ሳምንት ተዘካሪ ናቸው። እንደመገጣጠም ሆኖ ሁለቱም የንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ቤተሰቦች ናቸው። ሁለቱም በአንድ ወር ውስጥ ለዚያውም በአንድ ሳምንት ውስጥ ነው ያረፉት። እነሆ ይህንንም ታሪክ ያስታውሰዋል።


ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

## “ራሴን ሸንግዬ የምጽፍ አይደለሁም”

-ገጣሚ ኤፍሬም ስዩም

ቤዛ እሸቱ



እንደ ክፍለሀገር ልጅ የቆሎ ተማሪ ሆኖ አኩፋዳ ይዞ በእንተ ስለማርያም እያለ ቤት ለቤት ባይዞርም ድቁናን ተቀብሏል።ከመዲናችን አዲስ አበባ፣ ኮልፌ ተገኝተህ እንዴት መንፈሳዊ ሕይወት አማለልህ? ሲባል በልበ ሙሉነት “እንዲያውም መንፈሳዊነት የሚበረታው የአዲስ አበባ ልጅ ላይ ነው። በማለት ይመልሳል።ለዓለም አቀፍ መረጃዎችና እውቀቶች የአዲስ አበባ ሰው ቅርብ ነው፤ ግድ ስለሚሰጠውም የተለያዩ ዓለማዊ መጻሕፍትን ያነባል፤ ዓለም ምን እያደረገ ነው፤ ወዴትስ እያመራች ነው? የሚለውን ከተለያዩ ምንጮች እውቀት ለማካበት ይጥራል።የነበረና ያለን፤ የበፊቱና የአሁኑን እውቀት ለማዛመድና አንድ ለማድረግ ከሚተጉት ውስጥ በቅድሚያ የአዲስ አበባ ልጅ ነው።ለቤተክርስቲያን ቅርብነቱ የተፈጠረው እዛ ውስጥ ስለሆንኩና አዲስ አበባ የርህራሄ ልብ በመሆኗም ይሆናል ይላል።

ከስሙ በፊት ገጣሚ፣ ደራሲ፤ እንዲሁም ባለቅኔ የተሰኙ መጠሪያዎችን የያዘው ኤፍሬም ሥዩም የዛሬው የዝነኞች ገጽ እንግዳችን ነው።ግጥም እንደሚጽፍ እሱም ሳይገባው የሱን መክሊት ቀድመው የተረዱት እናቱ ማሜ አግደው ናቸው።ከዕለታት አንድ ቀን በሬድዮ ይተላለፍ የነበረን ግጥም ሰምተው እንደጨረሱ ተማሪው ልጃቸው ኤፍሬም ወደ ቤት ዘለቀ።እናት የታያቸው ታይቷቸዋልና ለምን አትጽፍም? አሉ።ግራ ተጋብቶ “ምንድነው የምጽፈው?” አለ፤ “ከመምጣትህ አስቀድሞ በሬድዮ ግጥም እየሰማሁ ነበርና አንተን ሳይህ እንዲህ አይነት ነገር መጻፍ የምትችል ይመስለኛል!” ብለው “እችላለሁ!!!። ብሎ ከመነሳቱ በፊት “ትችላለህ!!!። በማለት የሞራል ስንቅ አስታጠቁት።ከዛ ሲያብሰለስል ቆይቶ እጁን ከወረቀት ጋር ለማገናኘት ድፍረት አገኘ።ቤተክርስቲያን ውስጥ ከመንፈሳዊ አገልግሎት በተጓዳኝ በሥነ-ጽሁፍ አገልግሏል።በቤተክርስቲያን ድቁናም ከመቀበልና ከታላላቅ አባቶች ሥር ቁጭ ብሎ ከመማር ባለፈ ከቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ዩኒቨርሲቲ መንፈሳዊ እውቀትን ገብይቷል።

ለመጀመሪያ ጊዜ በፑሽኪን አዳራሽ በርካታ ሰዎች በተገኙበት “ማን ነው ሼክስፒር፣ እኛም አለን ብዕር” የተሰኘ ግጥም አቀረበ።የበሰለ የግጥም ሥራውን ለታዳሚ ጀባ ለማለት ብዙም ጊዜ አልፈጀም።በፑሽኪን መድረክ ለሁለተኛ ጊዜ ያቀረበው ፍቅር ላይ ያተኮረው ግጥሙ “ሀራሴቦን” ይሰኛል።

**ሀራሴቦን**

**እንደሀራሴቦን ቆሳ ነፍሴ በፍቅርሽ ተቃጥላ**

**ለዘር ንባብ እንዳይነድፈኝ አንድ እንዲሆን ሁለት ገላ**

**አለች እስከዛሬ አንችን ብላ ሳንችው ምላ**

**ትንሹ አካሌ ወርዝቶ ሲታደስ ለመኖር**

**ከወይንሽ ጠጥቶ ነይ እንሂድ ይላል**

**አንችን ብቻ ሽቶ አንችን ተመኝቶ .....**

**የተሰኘ ግጥሙ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሕዝብ ጋር ባስተዋወቀው “ሶልያና። የተሰኘ የግጥም ሲዲው ላይ የተካተተና “አሁንም ድረስ የምወደው። የሚለው ግጥሙ ነው።**

**ሶልያና**

**እኔን ከወንበር ላይ ቀን ያየሁት እንባ**

**ቀን ያየሁት ደባ እንቅልፍ አሳጥቶኝ**

**ወረቀት ላይ ወስዶኝ**

**እሷን ካልጋችን ላይ እንቅልፍ አሸኮርምሟት**

**ቀን ያየችው ሁሉ በቅዠት አልፎላት**

**እኔ ከቃላት ጋር ጦርነት ገጥሜ**

**በሰው ልጆች ጭንቀት እጅግ ተዳክሜ**

**በሌሊት ጭንቀቴ የቀን ስቃይ ሳበርድ**

**ከደጋው ሃሳቤ በረሀ ስሰደድ**

**እንባን በፊደላት ፊደልን በቃላት**

**ቃላትን በሃሳብ ወረቀት ላይ ልወልድ**

**ወረቀት ላይ ጽፌ ወረቀቱን ስቀድ ...**

ከላይ በከፊል የሰፈረው ሶልያና የተሰኘው ግጥም አሁን ድረስ በርካቶች ገጣሚ ኤፍሬምን ሲያስቡ ወደ አዕምሮአቸው የሚመጣውና የመጀመሪያ የግጥም ሲዲው መጠሪያ የሆነው ስራው ነው።ግጥሙ ከወጣ ረዥም ዓመታትን ቢያስቆጥርም አሁን ድረስ ኤፍሬምና ሶልያናን መነጠል የማይታሰብ ይመስላል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፣ እየተቀዛቀዘ የመጣውን በሙሉ ባንድ የማቀናበር ስራ ጥቂቶች እየደፈሩ የመጡ ቢሆንም፤ ገጣሚ ኤፍሬም ግን ሁለተኛ የግጥም ሲዲውን ሲያወጣ በሙዚቃ ቅንብሩ አበጋዝ ሺዎታ፣ ሄኖክ ተመስገን፣ ጆርጋ መስፍን፣ ግርማ ይፍራሸዋ ከተሳተፉት ባለሙያዎች መካከል ተጠቃሽ ናቸው።

እነዚህ ለአንድ ኮንሰርት በርካታ ብሮች የሚከፈላቸውን ሰዎች ማሳተፍ እንዴት አሰብከው? ላልነው ጥያቄ ሲመልስ፤ ባለሙያዎቹ ወዳጆቹና አክባሪዎቹ ስለሆኑ እሱም በተመሳሳይ የእነሱን ሙዚቃ ቅንብርና የሙዚቃ አጨዋወት የሚወድ በመሆኑ እንደሆነ ይገልጻል።ብዙም የኮንሰርት ሰው ባይሆንም ጃዝ ሙዚቃ ላይና ኮንሰርቶች ላይ ከላይ የተጠሩት ሥሞች ካሉ ይገኛል።ሙዚቃና ቃል ሲዋሀድ ምን ይፈጠራል? በሚል “ሙዚቃል። የሚል የሥነ-ጽሁፍ ስታይል ለመፍጠር ያመጣውን ሃሳብ ስለወደዱት አብረው መስራታቸውን ይናገራል።እነዚህን ሰዎች በገንዘብ አቅምና በሌላ ከተተመኑ አይነኬ ሰዎች ናቸው። ግን እነሱም ከገንዘብና ከጥቅሙ በላይ ለኪነ-ጥበብና ለአዲስ ፈጠራ ራሳቸውን የሰጡ በመሆናቸው ሃሳቡን ለመቀበል ሩቅ አለመሆናቸውን ይናገራል።ለዛም አዲስ ሙከራን ለመመኮር በጋራ እንደሰሩ ያስረዳል።

ኤፍሬም ግጥምንማ እሱ ያንብባት የሚያሰኝ የተለየ የሚያምር ቅላጼ አለው።እንዴት ነው አነባበብ ትለማመዳለህ ወይ? ሲባል የጻፍኩትን ነገር አውቀዋለሁ መልሱ ነው።የጻፈው ግጥም ምን አይነት ስሜት አለው? ይረብሻል፤ ያስደስታል፤ ያሳዝናል፤ ያስለቅሳል፤ ያስከፋል የሚለውን ያውቀዋልና ስሜቱን ተከትሎ አድማጭን ይዞ ይጓዛል።“ራሴን ሸንግዬ የምጽፍ አይደለሁም፤ የአዳራሽ ጭብጨባም ሆነ ሆይታ ይዞኝ የሚሄድም አይደለሁም።ምክንያቱም ሥነ-ግጥም ትልቅ ተሰጥኦ ስለሆነ ሽንገላ አያስፈልገውም።ሰው ይሄን ይፈልጋል፤ እያሉ ሲቀባጥሩ መኖር ራስ ምታት ነው።” የሚለው ገጣሚው አሁን ብዙ ራስ ምታት የሆኑ ግጥሞችን እየሰማ መሆኑንም ይናገራል።“ይቅርታ አድርጊልኝና። ከሚል ትህትና ጋር ሰዎች ያልተነኩበትን ግጥም እያቀረቡ መሆኑን ይናገራል።

ሰዎች ባልተነኩበት ግጥም ሰውን ለመዳሰስ እየሞከሩ መሆኑን በማንሳት መጀመሪያ ራስ መነካት ይቀድማል ይላል።ለአብነትም ቲክቲቶክ ላይ የሚነበቡ ግጥሞችን በማንሳት ዛሬ ማታ ምን ላቅርብ ተብለው የሚቀርቡ መሆናቸውን ይናገራል።ሥነ-ጽሁፍ እንደዚህ አለመሆኑንና ያልኖሩትን፤ ያላፈቀሩትን ያላዘኑበትን “በምን ልዘን? ተብሎ እንባ ይቀማል እንዴ?። ሲል ይጠይቃል።እሱ ግን የሚሰራውን ስለሚያውቅ የጻፈው ከምን ተነስቶ እንደሆነ ስሜቱን ስለሚያውቀውና ሳይሸነግል እራሱን ስለሆነ ቆንጆ አድርጎ ማንበቡ የመጣው ከዛ ሊሆን እንደሚችል ይገምታል።እሱ የሚጽፈው የነካውን ነገር ሲኖር መሆኑን ይናገራል።እሱ ከመጻፉ አስቀድሞ የሚሰሙት ድምጾች ስሜት ያነሳሳቸው ናቸው ወይስ እውነተኞች ናቸው በሚል ግራ ቀኝ ማየት እሞክራለሁ እንጂ በታየውና በተወራው ሁሉ አይጽፍም።የሱ ምልከታና መነካት ላይ ሲደርስ “አለመጻፍ አልችልም። ይላል፤ ያ አንዱ የማልቀሻ ወይም ደስታውን የመግለጫ መንገድ ነውና።

የመጀመሪያውና ገጣሚ ኤፍሬም ሥዩም የሚለውን ሥም ከሕዝብ ጋር ያስተዋወቀው ሶልያና የግጥም ሲዲን ጨምሮ በርካታ ሥራዎቹ በማህበራዊ ድረ-ገጾች ተለቀው በርካታ ተመልካችን አግኝተዋል።ሆኖም እሱ ጋር ምንም የደረሰ ነገር እንደሌለና አብዛኞቹ ከመድረክ የተወሰዱ መሆኑን ይናገራል።በሀገራችን “ማጅራት መቺ። መንገድ ላይ የቆመ ብቻ እንደሆነ እንደሚታሰብ በማንሳት የሰውን ፈጠራ ሳያስፈቅዱ የሚወስዱትም “ማጅራት መቺ። መሆናቸውን ይናገራል።የሱን ብቻ ሳይሆን የብዙ የጥበብ ሰዎችን ሀብት ዝም ብሎ እየከመረ የሚሄድ ሰው ፈጣሪ በዚህ በኩል የሌለ ይመስለዋል የሚለው ኤፍሬም፣ ይሄም አንዱ ሌብነት ነው ባይ ነው።እንዲህ አይነት ሰዎችም የእምነት ተቋማት እንደሚሄዱና ሃይማኖታዊ ሥርዓትን እንደሚከውኑ፤ ነገር ግን የሚሰሩት ሥራ ሌብነት እንደማይመስላቸው በማንሳት ግን የሚሰሩት ማጅራት መምታት ነው ይላል።

አብዛኛዎቹ ማህበራዊ ሚድያዎች ላይ የሚገኙት የሱ ሥራዎች እሱ ሥራዎቹን ቲክቶክ ላይ ማቅረብ ከመጀመሩ በፊት በማጅራት መችዎች የተጫኑ ናቸው ይላል።ተስፋ አያስቆርጥህም ወይ? ሲባል “እኔ በማጅራት መቺ ተስፋ አልቆርጥም።ጠባሳ መልሶ መሻሩ አይቀርም፤ ምናልባትም የኔም ስንፍና ሊኖርበት ይችላል።” እሱ በማህበራዊ ሚድያው በበቂ ስላልተንቀሳቀሰ በር ከፍቶላቸው ሊሆን እንደሚችል ይገምታል።ግን እሱ የጽሁፍ ሰው ነውና አብዛኛውን ጊዜ የሚሰጠውም ሆነ መስጠት የሚፈልገው ለሥነ-ጽሑፍ ነው።በተቃራኒው ማህበራዊ ሚድያው የሚሆንላቸውና የሚያሯሩጡ ሰዎች አሉ ይላል።አንዳንዶቹ ቢመጡም ሸፍጠኞች እየሆኑ እንደሚተዋቸውና የሱም የተወሰኑ ድክመቶች ጠቅሞአቸው ሊሆን ስለሚችል ተስፋ እንደማይቆርጥ ይናገራል።

“ሶልያና።ን እና “የብርሀን ክንፎች።ን በሲዲ ካሳተመ በኋላ ፊቱን ወደ መጻሕፍት መለሰ።“ፍቅር እዚህ ቦታ ፈገግ ብሎ ነበር” የተሰኘ መጽሐፉን ለአንባቢዎች እንካችሁ አለ።የግጥም ውጤቶቹን በትረካ ይሁን ወይስ መለስ ብሎ ለመወሰን ወሳኞቹ ሥራዎቹ መሆናቸውን ይናገራል። ለአብነትም ከመጀመሪያዎቹ ሁለቱ የግጥም ሲዲዎች በተለየ ሦስተኛው ላይ ያወጣው “ፍቅር እዚህ ቦታ ፈገግ ብሎ ነበር። የተሰኘው የግጥም መጽሐፍ የድምጽ መሆን እንደማይችል ይናገራል።መጽሐፉ ተጀምሮ እስኪያልቅ ያለ ታሪክ በመሆኑ በመጽሐፍ ከመውጣት ውጪ የተሻለ አማራጭ እንደሌለው ይናገራል።በቀጣይ ያወጣውን “የይሁዳ ድልድይ” ዝርው ሥራ ወይም ዝርግ ግጥም በማለት ይገልጸዋል። ተዋነይም በዛው መልክ በመጽሐፍ ለህትመት በቃ።

“ተዋነይ ብሉእ የግእዝ ቅኔያት” ከቀደምት የኢትዮጵያ ነገስታትና ሊቃውንት ጥናታዊ የግእዝ ሥራዎች በትርጉም የቀረቡበት ሥራው ነው።በሀገራችን የቤተክህነት ቋንቋ ብቻ ወደ መሆን የተሸጋገረው የግእዝ ቋንቋን ለመተርጎም ያነሳሳውን ምክንያት ሲያስረዳ የባለቅኔ አንዱ ሚና የተረሳውን ማስታወስ ነው የሚለው ገጣሚ ኤፍሬም፤ ታሪክ በቅርጽ፣ በፊደል ማቆየት ይቻላል። ስለዚህ የእሱ ሃሳቦች ፊደሎች ላይ ስላሉ የተሰራው እንኳን ቢጠፉ በደንብ ማሳየት ስለሚገባ የተረሱትን ለማስታወስ፤ ሊጠፉ ያሉትን እንዳይጠፉ ለማድረግ ከአንድ ደራሲና ባለቅኔ የሚጠበቅ በመሆኑ የግእዝን ቋንቋ ወደ ሕዝቡ እንዲደርስ በመፈለግ የሠራው መሆኑንና በቀጣይም እንደሚሰራ ይናገራል።የግእዝ ቋንቋ ባይሞትም የሞት አፋፍ ላይ ያለ ቋንቋ ነው፤ ሆኖም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እስካለች ግእዝ አይሞትም የሚለው ገጣሚ ኤፍሬም፤ የዚህ ምክንያቱ የቤተክርስቲያኗ አብዛኛው አገልግሎቶች ከግእዝ ጋር የተገናኙ ስለሆኑ ሲሆን፤ ቋንቋውም የቤተክህነት ቋንቋ ብቻ ወደ መሆን ተሻግሯል።እንደ ቋንቋ ከፍ እንዲል እሱ እንደ ጀመረው ቢኬድ የበለጠ ማድረግ እንደሚቻል ያምናል።

ኑ ግርግዳ እናፍርስ፣ የአዋጁ ጊዜ፣ እያሉ የሱ ሥራዎች ቀጥለዋል።ግጥም ይገጥማል፤ ወጎች ይጽፋል፤ ልቦለድ ይደርሳል።“ወደ የትኛው ታደላለህ?። ሲባል ግን ሁሉም የየራሱ መገለጫ እንዳለውና ሁሉንም እንደየአመጣጡ እቀበላለሁ ይላል።“ሁሉንም ብወደውም በተለይ ባለቅኔነቴን እወደዋለሁ። ይላል።በቀጣይም በዚህ በመቀጠል የሚያወጣው “ሚልኪና ቡና” የተሰኘ ጥናታዊ (ኤክስፐርመንታል) ሥራ እንዳለውና እሱን ካሳተመ በኋላ ጥናታዊና ረዘም ያሉ፣ መንፈሳዊ ፍልስፍና እሳቤዎች ላይ የሚያተኩሩ የሱን አተያይ ሊያሳዩ የሚችሉ እስከ ሦስት ጥራዝ የሚደርሱ ያለቁ ሥራዎች እንዳሉና በቀጣይ መሰል ጥናት ውስጥ አተኩሮ የሚሰራ መሆኑን ያስረዳል።አሁን የህትመት ብርሀን ሊያይ የተሰናዳው “ሚልኪና ቡና” የግጥም መድብል ሲሆን በጣም እንደለፋበትም ይናገራል።መጽሀፉ ከሦስት ዓመት በፊት ሊወጣ ማተሚያ ቤት ገብቶ የነበረ ቢሆንም በራሱ ኪሳራ ህትመቱ እንዲቋረጥ ማድረጉን ያስረዳል።ሀገር እርስ በእርስ ጦርነት በገጠመችበት ወቅት መጽሀፍ አውጥቼ ይህን መጽሀፍ አንብቡ የምልበት ሕሊና ስላልነበረኝና አጠቃላይ እንደ ሕዝብ እብደት ውስጥ የነበርንበትና ማን ጤነኛ ማን ደህና እንደሆነ የማይለይበት ጊዜ ስለነበር እንዳይታተም አድርጌዋለሁ ይላል።

በቀጣይም ግማሾቹን ዝም ብዬ በማልፋቸው፤ ግማሾቹን ቀን ሲደርስ በምናገራቸው ባላቸው እክሎችና እንቅፋቶች የተነሳ እስካሁን ሳይታተም መቆየቱንና በቅርብ የሕትመት ብርሃን ለማየት ከእስራቱ ተፈቶ ወደ ህዝብ ይቀርባል ብዬ አስባለሁ፤ ሌላ እንቅፋት ካልመጣ ይላል።የመጽሀፍ ህትመት ዋጋ መወደድን በተመለከተ አስቀድሞ ሥም ከያዙ ደራሲዎች በላይ አዲስ የሚመጡ ልጆች ከኛ በላይ ይፈተናሉ ይላል።ሥም ያላቸው ደራሲዎች የፈለከውን ሥራ አምጣና እናሳትም የሚሉ አሳታሚዎች እንዳሉ በማንሳት፤ አቅም ኖሯቸው መጽሀፍ እየፈለጉና በዚህ ህይወት ውስጥ እራሳቸውን እያሳደጉ ያሉና በብዙ ማንበብ ውስጥ የሚተጉ የሚያውቃቸው አዳዲስ ጸሀፍት መኖራቸውን ያነሳል።ጀማሪዎቹ በራሳቸው እንዳያሳትሙ ዋጋው አይቻልም፤ ነጋዴዎቹም ቢያከስረኝስ ይሄንን ልጅ አላውቀውም በሚል ቀመር ሥም ስለሌላቸው እንደሚጎዱ ያነሳል።ከዚህ ቀደም አምስት ሺህ መጻሕፍት 75ሺህ ብር ማሳተሙን በማስታወስ ለመጽሐፍ ሕትመት ትልቁ ያወጣው ወጪ ተዋነይን ሲያሳትም ጥራቱን በጠበቀ 80 ግራም ወረቀት 120ሺህ ብር ነበር።አሁን ግን ለህትመት ብቻ በሚልየን እየተጠየቀ መሆኑን በቁጭት ያነሳል።

በኢትዮጵያዊነቱ ኩራትና ደስታ፣ ትልቅነት እየተሰማው አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር ከፍሎ መጽሐፍ የሚታተምበት ሀገር አባል በመሆኑና እንደዚህ አይነት ሸፍጥ የሚሰሩ አሳታሚዎች ባሉበት ውስጥ በመደመሬ አዝናለሁ ይላል።በዚህ ከቀጠለ በቀጣይ የሚነበቡ መፃህፍት ብቻ ሳይሆን በእጅ የሚዳሰስ ወረቀት የሚኖርበት ሀገር ላይሆን መቻሉ ስጋቱ ነው።ይሄ ጉዳይ ቆም ተብሎ ሊጤንበት ይገባል የሚለው ገጣሚው፤ ሕዝብ የሚሰራው በጥበብ ነው፤ ጥበብ የሌለው ሀገር አያድግም፤ የትምም አይደርስም።በሰለጠኑት ሀገራት ላይ ለጥበብ ሥራዎች ትልቅ ክብር እንዳላቸው ያነሳል።ይህ የሆነው ለጥበቡ ትልቅ ቦታ ስለሚሰጡና በዛ በኩል ስለመጡ መሆኑን በማንሳት እንደጥቅምም እነዚህ በብዙ ሚልየን ዶላር የሚያመጡና ብዙ የሀገር ትርፍ ያላቸው ናቸው።በሀገራችንም በውጭ ቋንቋዎች እየተተረጎሙ የሚታተሙ ሥራዎች ብቅ ብቅ ማለት ጀምረው እንደነበር በማንሳት የውጭ ጸሐፍትን የሚገዳደሩ ጸሐፍት እንዳሉና ሲበረታቱ ለሀገርም የተሻለ እንደሚሆን በማንሳት ይሄ ምሬት መቀረፍ አለበት ይላል።አንድ መጽሀፍ አምስት ሺህ ኮፒ በሚሊዮን ብር፤ ከዛ አንባቢ ጋር ሲደርስ ትንሹ ብር 450 ወይም 500 ብር ስለሚሆን መግዛት የሚችለው የሕብረተሰብ ክፍል እራሱ ይገደባል።ይህ ሁሉ እየሆነ አንባቢው ክብር ይገባዋል የሚለው ደራሲው አንባቢው የራሱን ፍቅር እየገለጸና እየታገለ፣ እየገዛ መሆኑን ይናገራል።

ከሥነ-ጽሑፍ አይነቶች መንፈሳዊ ፍልስፍና (ሪሊጂየስ ፊሎሶፊ) ያላቸው ምርጫዎቹ መሆናቸውን ይናገራል።ሆኖም ሌሎችንም መጻህፍት ያነባል።ሙዚቃ ይሰማል። በተለይ ጃዝ ምርጫው ነው።ጃዝ ሙዚቃ ያለበት ስፍራ መገኛው ነው።በዛም ከበርካታ የጃዝ ተጫዋቾች ጋር ወዳጅነት መስርቷል።ከመሰሎቹ ሰዎች ይልቅ እሱን የማይመስሉ ሰዎችን ማግኘት፣ መቅረብ፣ መጠየቅ ያስደስተዋል።እርስ በእርስ የሚኖራቸው ልምድ ልውውጥ እራሴንም፣ ያኛውንም ወገን ያሳድጋል ይላል።ቡና ቀኑን የሚጀምርበት፤ ቀኑን ሙሉ እየደጋገመ የሚጠጣው ተወዳጅ መጠጡ ነው።

# ዓለም አቀፍ

## ታጣቂዎች የሙዚቃ አዳራሽ ውስጥ በከፈቱት ተኩስ 60 ሰዎች ተገደሉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ታጣቂዎች በሞስኮ አቅራቢያ በሚገኘው ታዋቂው የክሮከስ አዳራሽ ላይ ተኩስ ከፍተው ቢያንስ 60 ሰዎች ሲገድሉ፣ 100 ሰዎች መቁሰላቸውን የሩሲያ የደኅንነት አገልግሎት አስታወቀ።

ቢያንስ አራት ወታደራዊ የደንብ ልብስ የለበሱ ታጣቂዎች የበርካቶችን ሕይወት በቀጠፈው ጥቃት ውስጥ መሳተፋቸውም ተገልጿል።

ክራስኖጎርክስ ተብሎ በሚታወቀው ስፍራ በሚገኘው የክሮከስ አዳራሽ የሮክ የሙዚቃ ዝግጅት ሊቀርብ በነበረበትም ወቅት በአዳራሹ ታጣቂዎች ገብተው ተኩስ እንደከፈቱና መድረክ ላይም መውጣታቸው ተነግሯል።

ፒክኒክ የተሰኘው ታዋቂው የሮክ ባንድ ሙዚቃን ለመታደም ስድስት ሺህ የሚሆኑ ሩሲያውያን በክሮከስ ሲቲ ሆል ተገኝተው ነበር። ጥቃቱ የተከፈተውም ባንዱ ወደ መድረክ ከመምጣቱ ከደቂቃዎች በፊት እንደሆነ አንድ የዐይን እማኝ ተናግሯል።



የፒክኒክ ባንድ አባላት ምንም አይነት ጉዳት አልደረሰባቸውም። አብዛኛው የአዳራሹ ህንጻ በእሳት የተቃጠለ ሲሆን፤ የተወሰነው ጣራው ተደርምሶ ወድቋል።

ከተገደሉት መካከል ሕጻናት ይገኙበታል የተባለ ሲሆን፣ የሩሲያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ድርጊቱ “የሽብር ጥቃት ነው” ሲል አውግዟል።

የአሜሪካ ባለሥልጣናት በበኩላቸው አይኤስ ሩሲያን ለማጥቃት እንደሚፈልግ የሚያሳይ መረጃ ማግኘታቸውን ለቢቢሲ የአሜሪካ አጋር ሲቢኤስ ተናግረዋል።

ይህንንም አስመልክቶ ዋይት ሐውስ በሞስኮ “ሕዝብ በሚበዛባቸው ስፍራዎች” ላይ ያነጣጠረ ጥቃት ሊደርስ እንደሚችል በዚህ ወር መጀመሪያ ላይ ሩሲያን አስጠንቅቃ እንደነበረ ተገልጿል።

የሩሲያ ብሔራዊ ዘብ (ናሽናል ጋርድ) ጥቃት ፈጻሚዎቹን አድኖ ለመያዝ በስፍራው የተሰማሩ ልዩ ኃይሎች እንዳሉት ገልጿል። የሩሲያ ከፍተኛ ባለስልጣናትም ጥቃቱ ወደተፈጸመበት ክራስኖጎርስክ አካባቢ አምርተዋል።

ከሁለት ሳምንታት በፊት በሩሲያ የሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ ዜጎቹ በርካታ ሰዎች በሚሰባሰቡባቸው ሕዝባዊ ስፍራዎች እንዳይሄዱ ማስጠንቀቂያ አስተላልፎ ነበር።

በዚህም ማስጠንቀቂያው ላይ “ጽንፈኞች በሞስኮ ሕዝብ በሚሰባሰቡባቸው ስፍራዎችን የጥቃት ዒላማ ለማድረግ ዕቅድ አላቸው” የሚል ሪፖርትን እየተከታተልኩ ነው ብሎ ነበር።

ኤምባሲው አርብ ምሽት ባወጣው መግለጫ ጥቃቱ ወደደረሰበት ስፍራ ዜጎቹ ዝር እንዳይሉም ምክሩን አስተላልፏል።

## በሊቢያ የስደተኞች የጅምላ መቃብር መገኘቱን የመንግሥታቱ ድርጅት አስታወቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ሊቢያ ውስጥ ቢያንስ የ65 ስደተኞችን አስከሬኖች ያያዘ የጅምላ መቃብር መገኘቱን ዓለም አቀፉ የፍልሰተኞች ድርጅት (አይኦኤም) አስታወቀ።

ስደተኞቹ የሞቱበትን ሁኔታ እና የየት አገር ዜጎች ስለመሆናቸው እስካሁን የታወቀ ነገር እንደሌለ ድርጅቱ ገልጾ፣ ነገር ግን በሊቢያ በረሃ በኩል ወደ ሜዲትራኒያን ባሕር በድብቅ ሲወሰዱ ሳይሞቱ እንደማይቀሩ ይታመናል።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አንድ አካል የሆነው ዓለም አቀፉ የፍልሰተኞች ድርጅት በተገኘው የጅምላ መቃብር “በጥልቅ መደንገጡን” ገልጿል።

የስደተኞቹ የጅምላ መቃብር የተገኘው በደቡብ-ምዕራብ የሊቢያ ክፍል ውስጥ ሲሆን፣ አገሪቱም የጅምላ መቃብሩን በተመለከተ ምርመራ እያካሄደች መሆኗን አይኦኤም ገልጿል።

የአይኦኤም ቃል አቀባይ እንዳሉት “በእያንዳንዱ ስደተኛ ላይ የሚደርስ ደብዛ መጥፋት ወይም ሞት በቤተሰቦች ላይ የሚደርስን ሐዘን ከመወከሉ ባሻገር ስላጋጠማቸው ሰቆቃ ለማወቅ ያለው ጥረትም ሌላው አሳዛኝ ሁኔታ ነው” ብለዋል።

አክለውም አስፈላጊው እርምጃ ባለመወሰዱ ይህ ክስተት እየጨመረ ያለው የሰዎች ሞት እና ስደተኞች ያሉበት የሚረብሽ ሁኔታ ማስረጃ ነው ሲሉ በስደተኞች ላይ እየደረሰ ያለውን ሁኔታ ገልጸዋል።

መቀመጫውን ስዊትዘርላንድ ጄኔቭ ያደረገው ዓለም አቀፉ የፍልሰተኞች ድርጅት በጀምላ መቃብር የተገኙትን ስደተኞች አስከሬኖች በተገቢው ሁኔታ እንዲለዩ ለማድረግ የሊቢያ ባለሥልጣናት እና የመንግሥታቱ ድርጅት ተቋማት አስፈላጊውን እንዲያደርጉ ጠይቋል።

የአሁኑ ከስልሳ በላይ ስደተኞች የተቀበሩበት የጅምላ መቃብር የተገኘው፣ ከሊቢያ ባሕር ዳርቻ በትንሽዬ ጀልባ ተነስተው ሜዲትራኒያን ባሕርን ሲያቋርጡ በደረሰባቸው አደጋ ቢያንስ 60 ስደተኞች መሞታቸው ከታወቀ በኋላ ነው።




## የግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ
### ቁጥር ሞቬኢኢ/ግጨሰ/02/2016

❖ በመከላከያ ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የሞተር ቬይክልስ ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ እየሰራ ላለው የተለያዩ የብረት ለበስ የተሽከርካሪዎች የኦቨርሆሊንግና የምርት ስራ የሚውሉ የተለያዩ ግብዓቶችና ለቢሮ ስራ አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ እቃዎች በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል።

❖ ኢንዱስትሪው መግዛት የሚፈልጋቸው ግብዓቶችና እቃዎች ዝርዝር ፡፡

| ተ.ቁ | የሎት ማጣቀሻ | የእቃው ዓይነት | መግለጫ |
|---|---|---|---|
| 1 | ሎት 1 | Electrical Spare Parts | ብዛት በዝርዝር ዋናው ሰነድ ላይ ይገኛል |
| 2 | ሎት 2 | Mechanical Spare Parts | |
| 3 | ሎት 3 | Welding Work Equipment | |
| 4 | ሎት 4 | Hand Tools | |
| 5 | ሎት 5 | Machine Tools | |
| 6 | ሎት 6 | Raw Materials For Painting Work | |
| 7 | ሎት 7 | Oils and Lubricants | |
| 8 | ሎት 8 | የፅሕፈት (Stationary) እቃዎች | |
| 9 | ሎት 9 | የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች | |
| 10 | ሎት 10 | የደሕንነት መጠበቂያ እቃዎች (Safety Materials) | |
| 11 | ሎት 11 | የጽዳት እቃዎች | |
| 12 | ሎት 12 | ኮምፒውተርና የኮምፒውተር መለዋወጫዎች | |
| 13 | ሎት 13 | የሳኒተሪ ዕቃዎች | |

ተጫራቾች ከዚህ በታች የተመለከቱትን ነጥቦች በማሟላት ቀርበው መወዳደር ይችላሉ፡፡

1. ማንኛውም ተጫራች አግባብነት ያለው በ2016 ዓ.ም የታደሰ ንግድ ፈቃድ ያላቸውና የወቅቱን ግብር የከፈሉ መሆን አለበት፡
2. የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይ (VAT) የተመዘገቡና (Tin No) ያላቸው መሆን አለበት፡፡
3. ተጫራቾች የሚያቀርቡትን የማወዳደሪያ ሰነዳቸውን በማያሻማ ሁኔታ መግለፅና ሙሉ አድራሻቸውን መጥቀስ ይኖርባቸዋል።
4. ተጫራቾች የሚያቀርቡት ዋጋ ከዋናው ሰነድ ጋር በተያያዘው የዋጋ ማቅረቢያ ሰንጠረዥ መሰረት በጥራት ሞልተው ማቅረብ ያለባቸው ሲሆን በዋጋ ማቅረቢያ ሰንጠረዡ መግለጫ ላይ በተቀመጠው መሰረት በናሙና (Per Sample) የተባሉትን የሚያቀርቡትን እቃ የራሳቸውን ናሙና (Sample) ወይም ኢንዱስትሪው ያዘጋጀነውን ናሙና ዋጋ ሞልተው ከማስገባታቸው በፊት ማየት ወይም ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
5. ተጫራቾች በሎቱ በቀረቡት ዕቃዎች ላይ ለመወዳደር በዘርፉ ስራ ወይም ንግድ ላይ ስለመሰማራታቸው ህጋዊ ማስረጃ ማቅረብ ያለባቸው ሲሆን ከዚህ ውጪ ተወዳድረው ቢገኙ ያስገቡት መወዳደሪያና ዋጋ ተቀባይነት አይኖረውም።
6. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ የመጫረቻውን ጠቅላላ ዋጋ 2% (CPO) ማስያዝ ይኖርባቸዋል 2% (CPO) ያላስያዘ ተጫራች ከጨረታው ውጪ ይደረጋል፡፡
7. በጨረታው ተሸናፊ የሆኑ ተጫራቾች 2% የጨረታ ማስከበሪያ (CPO) ዋስትና የጨረታ አሸናፊው እንደታወቀ ተመላሽ ይደረግላቸዋል።
8. የጨረታውን አካሄድ ለማዛባት የሚሞክሩ ተጫራቾች ከጨረታው ውጪ ይሆናሉ፤ ለወደፊትም በኢንዱስትሪው ጨረታ አይሳተፉም ያስያዙትም የጨረታ ማስከበሪያ ይወረሳል።
9. በጨረታው አሸናፊ የሆኑ ተጫራች ከኢንዱስትሪው ጋር የሥራ አፈፃፀም ውል መፈራረም አለባቸው ውል ካልፈረሙ ያስያዙት 2% (CPO) ተወርሶ ለኢንዱስትሪው ገቢ ይደረጋል።
10. ተጫራቾች የሚያቀርቡት ዋጋ በግልፅ በኢትዮጵያ ብር ነጠላ ዋጋና ጠቅላላ ዋጋ በዝርዝር ማስፈር አለባቸው፡ በዋጋው ላይ ማንኛውም ታክስና ተጨማሪ እሴት ታክስ ያካተተ መሆኑና አለመሆኑ መገለፅ አለበት፡፡
11. በነጠላ ዋጋና በጠቅላላ ዋጋ መካከል ልዩነት ቢኖር ነጠላ ዋጋ ተቀባይነት እንዲኖረው ተደርጎ በነጠላ ዋጋው ተመስርቶ ጠቅላላ ዋጋው ይታረማል፡፡
12. ተጫራቾች የመወዳደሪያ ሰነዳቸውን በኢንዱስትሪው ቅጥር ግቢ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል የጨረታ ሳጥኑ ከሚዘጋበት ሰዓት በኋላ የሚቀርብ የጨረታ ሰነድ ተቀባይነት የለውም፡፡
13. ተጫራቾች የዋጋ ማቅረቢያቸውን በሁለት ቅጅዎች ማቅረብ አለባቸው አንደኛው ቅጅ ላይ “ዋና” በሁለተኛው ቅጅ ላይ ኮፒ የሚል ምልክት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ በሁለቱ መካከል ያለመጣጣም ቢፈጠር “ዋና” ተብሎ ምልክት የተደረገበት ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡
14. ማንኛውም ተጫራቾች በሚያቀርቡት የጨረታ ሰነድ ላይ የተጫራቹ ወይም የሕጋዊ ወኪሉ ስም ፊርማና የድርጅቱ ማህተም መስፈር አለበት፡፡
15. በሌላ ተጫራች ላይ ተመስርቶ ዋጋ መስጠት አይቻልም፡፡
16. ከዚህ በላይ በቀረበው ዝርዝር መሠረት በግንባር ቀርበው ዝርዝር መረጃ የያዘ የተጫራቾች መመሪያ እና የዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ የማይመለስ 400.00 ብር (አራት መቶ ብር ) በመክፈል ሰነዱን መግዛት ይችላሉ፤
17. ጨረታው ለተወዳዳሪዎች ክፍት ሆኖ የሚቆይበት ጊዜ የግልፅ ጨረታ ጥሪ ማስታወቂያው በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ ለተከታታይ 15 (አስራ አምስት) የመንግስት የስራ ቀናት ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት እስከ 11፡00 ሰዓት የስራ መውጫ ባሉት ሰአቶች ሲሆን ጨረታው በ16ኛው (በአስራ ስድስተኛው) ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ታሽጎ ተጫራቾች/ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በዚያኑ ቀን ከቀኑ 4፡30 ሰዓት የጨረታ ሰነዱን በገዙበት ተቋም በሚገኘው መሰብሰቢያ አዳራሽ ይከፈታል፡፡እንዲሁም ተጫራቾች በራሳቸው ምርጫ ጨረታው በሚከፈትበት ጊዜ ሳይገኙ ቢቀሩ የጨረታውን መከፈት አያስተጓጉልም፤
18.ኢንዱስትሪው ያወጣውን የጨረታ ሰነድ ሳይገዛ የተወዳደረ ማንኛውም ተጫራች ከተገኘ ከውድድሩ ውጪ ይደረጋል፡፡
19, አሸናፊ ተጫራቾች ውል ሲፈራረሙ የውል ማስከበሪያ ዋስትና (Perfomance Bond) ያሸነፉበትን ጠቅላላ ዋጋ 10% (አስር ከመቶ) በተመሰከረለት የባንክ ክፍያ ማዘዣ (CPO) ማቅረብ ይኖርባቸዋል እንዲሁም ውል ከተፈራረሙ በኋላ ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ወዲያውኑ ይለቀቅላቸዋል፤
20. ተጫራቾች የመወዳደሪያ ሰነዱን በመከላከያ ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን በሞተር ቬይክልስ ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ቢሮፍቱ ማግኘት ይችላሉ፡፡
21.ተጨማሪ ማብራሪያ ካስፈለገ ስልክ ቁጥር (0967618382 / 0913787642/ 0936656577) ደውሎ መጠየቅ ይቻላል፤
22. ኢንዱስትሪው ጨረታውን የተሻለ መንገድ ካገኘ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፤

**የመከላከያ ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ ኮርፖሬሽን የሞተር ቬይክልስ ኢንጂነሪንግ ኢንዱስትሪ**

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞኼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## የሁቲዎች ጥቃት በሀገራችን የኤክስፖርት ንግድ ላይ ይዞት የመጣው ስጋት

በቀይ ባሕር በተቀሰቀሰው ጅኦፖለቲካዊ ቀውስ ሳቢያ እንደ ቡና ያሉ የውጭ ምርቶችን ወደ ውጭ ለመላክ አዳጋች በመሆኑ ላኪዎችና በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ቡና አምራቾች ላይ አደጋ ደቅኗል። የአዲስ ፎርቹን ጸሐፊ አክሳህ ኢታሎ በዚያ ሰሞኑ ባስነበበን መጣጥፍ ለኢኮኖሚው ከመርግ የከበደ መርዶ አርድቶናል። ወደብና ባሕር አልባ መሆናችን ሳያንስ በቀይ ባሕር ኮሽ ባለ ቁጥር ህልውናችንና ኢኮኖሚያችን ምን ያህል ለአደጋ እንደሚያጋልጥ ያመላከተ ነው። የሁቲ አማጽያን በቀይ ባሕር ላይ በሚፈጽሙት ተደጋጋሚ ጥቃት የተነሳ የጭነት መርከቦች በዚህ መስመር መቅዘፍ ቀንሰዋል አልያም ከእነ አካቴው አቁመዋል።

የሁቲዎችን ጥቃት በመሸሽ በደቡባዊ አፍሪካ ኬፕ ኦፍ ጉድ ሆፕ ዙሪያ ጥምጥም ለመጓዝ በመገደዳቸው የጭነትና የዋስትና ዋጋ እጅግ አሻቅቧል። ንሯል። በዚህ የተነሳ ቡና ተቀባይ ሀገራት ፊታቸውን ወደ ብራዚል በማዞራቸው ከ3ሚሊዮን ኪ.ግ በላይ ቡና በጅቡቲ ወደብ ተከማችቶ ይገኛል።የቀይ ባሕር ጉዳይ በቅርቡ መፍትሔ አግኝቶ መውጣት ካልቻለ የቡና ላኪዎችና በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ቡና አምራች ገበሬዎች ህይወት ላይ የከፋ ችግር ያስከትላል። በጦርነት፣ በማዕቀብና በብድር እጦት ክፉኛ የውጭ ምንዛሬ እጥረት ገጥሞት እየተፍገመገመ ላለ ኢኮኖሚ አንደኛ የውጭ ምንዛሬ ማግኛ የሆነው የቡና ኤክስፖርት ላይ የገጠመው ከባድ ፈተና ኢኮኖሚውን ከድጡ ወደ ማጡ ይከተዋል።

ኢኮኖሚው በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል በተቀሰቀሰው ጦርነት ሀገራችን ከአግዋ ተጠቃሚነት በመውጣቷ፤ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት በመቀዛቀዙ እና ቱሪዝም በብርቱ መዳከሙ ሳያንስ በአማራና ኦሮሚያ ክልል የተቀሰቀሰው ጦርነት ደግሞ በእንቅርት ላይ ቆረቆር እንዲሉ ሆኗል።የኑሮ ውድነቱም በሰዓታት ጣራ እየነካ ዜጎችን በእጅጉ እያማረረ ባለበት ነው እንግዲህ የኤክስፖርት ንግዳችን ቅርቃር ውስጥ የገባው። በዋጋ ግሽበቱና እሱን ተከትሎ በመጣው የኑሮ ውድነት የዜጎች የሸመታ አቅም መዳከሙና መቀዛቀዙ ኢኮኖሚውን ታማሚ አድርጎታል። በአራዶች ቋንቋ አየሩ ተመቷል።ገቢ ቀንሷል።ሀገራዊ ቁጠባው እጅ አጥሮታል። በዚህ ቀውጢ ሰዓት ነው ኤክስፖርታችን ደግሞ ያልተጠበቀ ፈተና ውስጥ የገባው።

ወሳኝ የሆነውና ከዓለም ንግድ እስከ 15 በመቶ ይተላለፍበት የነበረው ቀይ ባሕር በሁቲ አማጽያን ተደጋጋሚ ጥቃትና እገታ የተነሳ በመስተጓጎሉ የኢትዮጵያን የውጭ ንግድ አደጋ ላይ ጥሎታል። ወደ ውጭ የሚላኩ ምርቶችን የጫኑ ተሽከርካሪዎች በወደቦች ለወራት መቆማቸው ሳያንስ ግዙፍ የጭነት መርከቦች በቀይ ባሕር መቅዘፍ ማቆማቸው በሀገራችን የወጭም ሆነ የገቢ ንግድ ላይ ከባድ ሳንካ ፈጥሯል።ግዙፉን የጭነት መርከብ ኩባንያ ሜርስክን እንኳ በአብነት ብንወስድ 600 የጭነት መርከቦቹ በቀይ ባሕር መቅዘፍ በማቆማቸው ከ30ሺህ በላይ ኮንቴነሮች በወደቦች እንዲከማቹ አስገድዷል።

ለዚህ ነው በሜርስክ የኢትዮጵያ ወኪል ዳኔል ዘሚካኤል መርከቦቻችን ለአደጋ በመጋለጣቸው በቀይ ባሕር በኩል የምናደርገውን ጉዞ ለማቆም ተገደናል።የሀገራችን ላኪዎችና የሎጅስቲክስ ኩባንያዎች ምርቶቻቸውን በሕንድ ውቅያኖስ አድርገው ወደ አውሮፓ ለመላክ የሞምባሳንና የላሙ ወደቦችን ለመጠቀም ተገደዋል።ይህ ደግሞ በቀይ ባሕር በጥቂት ሳምንታት ይጓጓዝ የነበረን ምርት ቢያንስ ወር ስለሚፈጅበት የማጓጓዣ ወጪውን ስለሚያንረው ከሌሎች ጋር ለመወዳደር አዳጋች አድርጎታል። ወደ መካከለኛው ምሥራቅ የሚላኩ ምርቶችንም በአረቢያን ወሽመጥ በኩል ማጓጓዝ ግድ ሆኗል።

የኢትዮጵያ ቡና እና ሻይ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ዶ/ር አዱኛ ደበላ የተከሰተው ችግር የሀገራችንን የቡና ዘርፍ ክፉኛ ይጎዳዋል ብለውሰግተዋል።የባለስልጣኑ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሻፊ ኡመር በበኩላቸው፤ የኬንያን ወደቦች በአማራጭነት ለመጠቀም የዳሰሳ ጥናት እየተካሄደ ቢሆንም የወደቦቹ አቅም ውስን መሆኑና ተጨማሪ ወጪ የሚጠይቅ መሆኑ ሌላው ፈተና ነው ይላሉ። የኬንያ ወደቦች የጭነት አቅም በኮንቴነር 28 ቶን ወይም 280 ኩንታል መሆኑ ቡናን ለመጫን የሚያስፈልገው፤ የጭነት መስፈርት የሚያሟላ አለመሆናቸው ሌላው ፈተና ነው። ስለሆነም አዋጭነታቸው ገና አለመረጋገጡ ችግሩን አሳሳቢ አድርጎታል።

የተከሰተው የሎጂስቲክስ ችግር የሀገራችንን ዋና የኤክስፖርት ምርት ቡናን ወደ አውሮፓና መካከለኛው ምሥራቅ እንዳንልክ አድርጎናል። ተቀባይ ኩባንያዎች ፊታቸውን ወደ ብራዚል ካዞሩ ደግሞ ደንበኞቻችንን ልናጣ ነው። ደንበኞች አንዴ ከእጅ ከወጡ ደግሞ መልሶ ማግኘት ፈተና ነው። ቡናን ወደ ውጭ የሚልኩት አቶ ዘላለም እሸቱ ከዚህ በፊት በአማካኝ እስከ 26 ሚሊዮን ዶላር የሚያወጣ ቡና ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ይልኩ እንደነበር አስታውሰው አሁን ግን የገዙትን ቡና ለመላክ መቸገራቸውን ለ"አዲስ ፎርቹን" ይናገራሉ።10ሺህ አባላት ያሉት የኢትዮጵያ ቡና ማህበር ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ሰይድ ሁሴን፤መንግሥት በቡና ኤክስፖርት ላይ ላጋጠመው ችግር አፋጣኝ መፍትሔ የማይሰጥ ከሆነ ሌላ መላ ይገኝለታል ብለው ተስፋ እንደማያደርጉ ለጋዜጣው ገልጸዋል።

ዘጠኝ እቃ ጫኝ መርከቦች እንዳሉት የሚታወቀው የኢትዮጵያ የመርከብና የሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ በሪሶ አማሎ በበኩላቸው፤ አጋር የጭነት መርከብ ኩባንያዎች በቀይ ባህር መቅዘፍ በማቆማቸው የድርጅታቸው አገልግሎት መስተጓጎሉን አስታውሰው፤ ችግሩን ለማቃለል ጥረት እየተደረገ መሆኑን አስታውቀዋል። 70ሺህ ቡና አምራች ገበሬዎችን በአባልነት ያቀፈው የሲዳማ የኅብረት ሥራ ዩኒየን ዋና ሥራ አስኪያጅ ጸጋዬ አኔቦ፤ላለፉት ሁለት ወራት ወደ ውጭ ለመላክ ጅቡቲ ወደብ ያደረስነው 3800 ኩንታል ቡና በዚያ እንደተቀመጠ ነው። በአየር እንዳናጓጉዝ የጭነት ዋጋው ከመርከብ 25 እጥፍ ይበልጣል። ይወደዳል። የምናደርገው ግራ ገብቶን ተቀምጠናል ይሉናል።

የቀድሞው የቡናና ሻይ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ሳኒ ረዲ በዚህ ፈታኝ ወቅት ከትርፍ ይልቅ ደንበኞችን ላለማጣት ጥረት ሊደረግ ይገባል ሲሉ ያሳስባሉ።የቡና ኤክስፖርት ስትራቴጂንም እንደነባራዊ ሁኔታው መከለስና መቃኘት ያሻል። ደንበኛ አንዴ ከእጅ ካመለጠ መልሶ ማግኘት ያዳግታል ሲሉ አስጠንቅቀዋል።የኢትዮጵያ ቡና በዓለም ገበያ የሶስት በመቶ ድርሻ ብቻ ያለው ሲሆን፤ የቬትናምና የብራዚል ድርሻ ግን እጅግ ከፍ ያለነው። ድርሻችን ከፍ እንዲል ምርታማነትን ማሳደግ ላይ ጥረቶች ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል።

በሌላ በኩል የቡና ባለሙያዎችና የዘርፉ አንቀሳቃሾች እንደገለጹት፤ በ1980ዎቹ መጨረሻ የቡና ምርትና ግብይት ሒደት ለቀቅ ቢደረግም ከፖሊሲ አንጻር ግን ይህ ነው የሚባል መሠረታዊ ለውጥ ስላልታየበት በዓለም ገበያ ለሚከሰቱ አሉታዊ ተጽዕኖዎች በተደጋጋሚ ተጋላጭ መሆኑን ይናገራሉ። በዚህ ሁሉ ተግዳሮት ውስጥ ሆኖም የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን ምርታማነትን ለማሳደግና ተጨማሪ መዳረሻ ገበያን ለማግኘት እየሰራ ሲሆን በዓለም ገበያ ተፈላጊ የሆነውን ቡና በምታመርተው ይርጋ ጨፌም የምርምርና የልማት ኢንስቲትዩት ተከፍቷል።

በሀገራችን ቡና ወደ 6 ሚሊዮን ለሚጠጉ ዜጎች የሥራ ዕድል ሲፈጥር፤ወደ ውጭ ከሚላኩ ምርቶች ደግሞ ሲሶውን ይይዛል። ባለፈው ዓመት 1.3 ቢሊዮን ዶላር ገቢ አስገኝቷል። ቡና በብዛት የሚመረተው በተወሰኑ አካባቢዎች ብቻ መሆኑ ምርታማነቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጥሯል። ኦሮሚያ 59፣የደቡብ ምእራብ 15፣ሲዳማ ክልል 7 በመቶ ቀሪው ድርሻ የተለያዩ ክልሎች ነው።

አቶ ዳዊት ባደግ የዘላለም እሸቱ ቡና ላኪ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ዋና ሥራ አስኪያጅ፤ከጊዜ ወደ ጊዜ የገበያ ውድድሩ እየከበደ ዓለም አቀፍ ዋጋው ደግሞ እየቀነሰ መሆኑ ሳያንስ ፍላጎቱም እየተቀዛቀዘ መሆኑ በአምራቾችና በላኪዎች ዘንድ ስጋት እየጎነቆለ ይገኛል ይሉናል። በዚህ ላይ የአውሮፖ የመድን ኩባንያዎች በቀይ ባሕር በተፈጠረው ቀውስ የተነሳ ይሰጡት የነበረውን ዋስትና በመቀነሳቸው ቡና ላኪዎችና ተቀባዮች ግራ ተጋብተዋል።

የሆነው ሆነና ሁቲዎች እነማን ናቸው?ሁቲዎች የየመን ታጣቂ ቡድን ሲሆኑ፤ መሰረታቸውም ዛይዲስ በመባል የሚታወቅ የሀገሪቱ የሺዓ ሙስሊም ነው። በአውሮፓውያኑ 1990ዎቹ ሲቋቋሙ የወቅቱ ፕሬዚዳንት የነበሩት አሊ አብደላህ ሳሌህ አገዛዝ የተንሰራፋውን ሙስና ለመዋጋት በሚል ነበር። ስማቸውንም የወሰዱት ከንቅናቄው መስራች ከሆኑት ሁሴን አል ሁቲ ነው። ራሳቸውንም 'አንሳር አላህ' ወይም "የአምላክ ደጋፊዎች" ብለው ይጠራሉ። በአሜሪካ መሪነት ምዕራባውያኑ ኢራቅን መውረራቸውንም ተከትሎ ሁቲዎች "አምላክ ታላቅ ነው፣ ሞት ለአሜሪካ፣ ሞት ለእስራኤል። እርግማን ለአይሁዶች፣ ድል ለእስልምና' የሚል መፈክርን ማሰማት ጀመሩ።

እስራኤል፣ አሜሪካ እና ሰፊውን ምዕራባዊ ክፍል የሚቃወም እና በኢራን የሚመራው 'አክሲስ ኦፍ ሬዚስታንስ ጥምረት' መሆናቸውንም አስታወቁ። ከሁቲ በተጨማሪ ሐማስ እና ሂዝቦላህ የዚህ ጥምረት አካል ናቸው።ሁቲዎች በአሁኑ ወቅት በባህረ ሰላጤው ወደ እስራኤል የሚያቀኑትን መርከቦች ላይ ጥቃት እየፈጸሙ ያሉበትንም ምክንያት በአውሮፓ የሰላም ኢንስቲትዩት የየመን ተንታኝ ሂሻም አል ኦምሴ ያስረዳሉ።"በአሁኑ ወቅት ከኢምፔሪያሊስቶች ጋር እየተዋጉ ነው፤ የእስላም ሀገራት ጠላቶች ጋር እየተዋጉ ነው" የሚሉት ምሁሩ "ይህም ከመሰረታቸው ጋር የሚጣጣም" እንደሆነም ያስረዳሉ።

ሁቲዎች በመጀመሪያ ላይ ከፍተኛ የፖለቲካ ጥንካሬ ማግኘት የቻሉት ፕሬዚዳንት አሊ አብደላህ ሳሌህን በተኩት በፕሬዚዳንት አብድራቡህ ማንሱር ሃዲ ላይ በተነሱበት ወቅት ነው። ይህም በአውሮፓውያኑ 2014 ነው። ከቀድሞው ጠላታቸው እና ከስልጣን ከተነሱት ፕሬዚዳንት ሳሌህ ጋር ስምምነት ላይ ከደረሱ በኋላም እሳቸውን ወደ ስልጣን ለመመለስ አስበው ነበር። በቀጣዩ ዓመትም በየመን ሰሜናዊ ክፍል የሚገኘውን የሳዓዳ ግዛትን ተቆጣጠሩ። ይህም ዋና ከተማዋን ሰንዓን መቆጣጠር ያስቻላቸው ሲሆን ፕሬዚዳንት ሃዲንም ወደ ውጭ እንዲሰደዱ አስገደዷቸው።የየመን ጎረቤት የሆነችው ሳዑዲ አረቢያ ወታደራዊ ጣልቃ በመግባት ፕሬዚዳንት ሃዲን ወደ ስልጣን መለሰች እንዲሁም የሁቲዎችን ኃይልም ለማሸነፍ ሞከረች።ሳዑዲ በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች እና ባህሬንም ትደገፍ ነበር።ሆኖም ሁቲዎች የተሰነዘረባቸውን ጥቃት በመመከት ይዞታቸውን ማስፋት ቀጠሉ።

በአውሮፓውያኑ 2017 የቀድሞው ፕሬዚዳንት አሊ አብዱላህ ሳሌህ ወደ ሳዑዲ ጎራ ለመቀላቀል ሲሞክሩም በሁቲ ታጣቂዎች ተገደሉ። የሁቲ አማጺያን በሊባኖስ ውስጥ የሚገኘው የሺአው ታጣቂ ቡድን ሄዝቦላህ ጋር ጥብቅ ቁርኝት አላቸው። ሄዝቦላህም ለሁቲ አማጽያን ከአውሮፓውያኑ 2014 ጀምሮም ሰፊ ወታደራዊ ስልጠናዎችን እየሰጣቸው መሆኑን ሽብርተኝነትን የሚዋጋው 'ዘ ኮምባቲንግ ቴሬሪዚም ሴንተር' የተሰኘው የአሜሪካው የምርምር ተቋም አስታውቋል። ሁቲዎች ኢራንን በአጋርነት የሚያይዋት ሲሆን ሳዑዲ አረቢያም ደግሞ የጋራ ጠላታቸው ናት። ኢራን ለሁቲ አማጺያን የጦር መሳሪያ ታቀርባለች በሚል በተደጋጋሚ ብትከሰስም ታስተባብላለች።


ሁቲዎች በአውሮፓውያኑ 2017 በሳዑዲ መዲና ሪያድ ላይ ያስወነጨፉትን ባለስቲክ ሚሳኤል ያቀረበችው ኢራን ናት በማለት አሜሪካ እና ሳዑዲያ አረቢያ ይከሳሉ። በተጨማሪም በአውሮፓውያኑ 2019 ሁቲዎች የሳዑዲ ነዳጅ ማምረቻዎችን ለማጥቃት የተጠቀሙባቸውን የክሩዝ ሚሳኤሎች እና ድሮኖችን (ሰው አልባ አውሮፕላኖችን) የሰጠችው ኢራን እንደሆነች ይወሳል።ሁቲዎች መቼ በዚህ ሊቆሙ በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ የአጭር ርቀት ሚሳኤሎችን ወደ ሳዑዲ አረቢያ ያስወነጨፉ ሲሆን በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች ኢላማዎችም ላይ ጥቃት ሰንዝረዋል። እነዚህን መሳሪያዎች ለሁቲ አማጽያን ማቅረብ የተባበሩት መንግሥታት በኢራን ላይ የጣለውን የጦር መሳሪያ እገዳን የሚጥስ ቢሆንም ኢራን በጭራሽ ክሱን አትቀበለውም።

በዓለም አቀፍ ዕውቅና የተሰጠው መንግሥት የፕሬዚዳንቱ አመራር ምክር ቤት ነው። ፕሬዚዳንት አብዱራቡህ ማንሱር ሃዲ በአውሮፓውያኑ 2022 ስልጣናቸውን ለምክር ቤቱ አስተላልፈውለታል። ምክር ቤቱ መቀመጫውም በሳዑዲ መዲና ሪያድ ነው። ሆኖም አብዛኛው የየመን ህዝብ የሚኖረው በሁቲ አማጽያን ቁጥጥር ስር ባሉ አካባቢዎች ነው። በሰሜናዊ የሀገሪቱ ክፍል ግብር የሚሰበስቡ ሲሆን የሀገሪቱንም መገበያያ ገንዘብም ያትማሉ።

የመንግሥታቱ ድርጅት የጸጥታው ምክር ቤት ሁቲዎች በአውሮፓውያኑ 2010፣ ከ100 ሺህ- 200 ሺህ የታጠቁ ወታደሮች እና ያልታጠቁ ደጋፊዎች እንዳላቸው ገልጿል።የሁቲ አማጽያን ሰፊውን የቀይ ባህር ጠረፍ ይቆጣጠራሉ። ከነዚህም አካባቢዎች ነው ጥቃቶቹን እየፈጸሙ የሚገኙት። እነዚህ ጥቃቶች ከሳዑዲ አረቢያ ጋር እያደረጉት ላለው የሰላም ድርድር አግዟቸዋል።"ለሳዑዲዎች የቀይ ባህር መተላለፊያ የሆነው ባብ አል ማንዳብ መዝጋት እንደሚችሉ በማሳየት በስምምነቱ ላይ ከፍተኛ ጫና ማሳረፍ ችለዋል" ይለናል ቢቢሲ።

ሻሎም ! አሜን።

# ስፖርት





# ፈተናዎችን የተሻገረው የአፍሪካ ጨዋታዎች

ብርሃን ፈይሳ

አፍሪካውያንን ከሚያስተሳስሩና እርስ በእርስ ያላቸውን ግንኙነት ከሚያጎለብቱ ጉዳዮች መካከል የስፖርት መድረኮች ጎልተው ይጠቀሳሉ። የአፍሪካ ጨዋታዎች ፓን አፍሪካዊነትን ከማቀንቀን ባለፈ አፍሪካዊያን ወጣቶች የውድድር እድል እንዲያገኙ ከማድረግ አንጻርም ከፍተኛ ሚና አለው። በዚህ እሳቤ የተጠነሰሰው የአፍሪካ ጨዋታዎች በተለያዩ ምክንያቶች ሲካሄድና ሲቋረጥ አሁን ካለበት ደርሷል። ዘንድሮም ለ13 ጊዜ በጋና አስተናጋጅነት ሲካሄድ ቆይቶም ዛሬ ይጠናቀቃል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ረጅም እድሜ ካስቆጠሩ የስፖርት ውድድሮች መካከል ሊጠቀስ የሚችለው የአፍሪካ ጨዋታዎች መነሻውን እአአ 1920 ያደርጋል። የዘመናዊው ኦሊምፒክ መስራችና አባት የሆኑት ፈረንሳዊው ፔሪ ደ ኩበርቲን አማካኝነት መካሄድ እንደጀመረም ይነገራል። ይሁንና በወቅቱ በአፍሪካ ሀገራት ተንሰራፍቶ በነበረው የነጮች የቅኝ አገዛዝ ምክንያት ተቀባይነትን ያገኘ አልነበረም። ቅኝ ገዢዎች ስፖርትን ምክንያት አድርገው አፍሪካዊያን ስለነጻነታቸው የሚሰበሰቡበት መድረክ ይሆናል የሚል ስጋት ነበረባቸው። በዚህ ሁኔታ ያልተሳካው ይህ ሙከራ ከአምስት ዓመት በኋላ በአልጄሪያ አልጀርስ እንዲካሄድ ከውሳኔ ቢደረስም በመጨረሻው ሰዓት ሊጨናገፍ መቻሉን የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ በ1995 ዓ.ም ያሳተመው መጽሔት ላይ ሰፍሮ ይገኛል።

በድጋሚ እአአ በ1929 በግብጽ አሌክሳንደሪያ ሊካሄድ ተሞክሮ ነበር፣ ይሁንና በራሷ መቆም ያልቻለችው አፍሪካ እንደፈለጉ በሚያደርጓት ቅኝ ገዢዎች በድጋሚ እንዳይካሄድ ተደርጓል። በተደጋጋሚ የተሰናከለው የዚህ ውድድር ሃሳብም ዳግም እውን ሊሆን ሌሎች አስርት ዓመታትን ማስቆጠር የግድ ሆኖበታል። እአአ በ1960 ደግሞ ፈረንሳይ የምትገዛቸው ሀገራት መካከል «የፈረንሳይ ማህበረሰብ» ውድድር ለማዘጋጀት ሙከራ ብታደርግም ሌሎች የአፍሪካ ሀገሮችን ያላሳተፈ በመሆኑ ምክንያት ዓላማውን ሊያሳካ አልቻለም።ነገር ግን ወቅቱ አፍሪካዊያን ሀገራት ከቅኝ ከገዢዎች ተላቀው የራሳቸውን እጣ ፋንታ መወሰንና እርስ በእርስ ያላቸውን ግንኙነት ማጠናከር የጀመሩበት መሆኑን ተከትሎ የመላ አፍሪካዊያን ጨዋታን የሚመለከተውን ጉዳይ አጀንዳቸው ውስጥ ሊያካትቱ ችለዋል።

በአህጉሪቷ የሚገኙ ሀገራትን አንድነት ለማጠናከር ስፖርት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው በመገንዘብ አፍሪካዊያን መሪዎች እአአ በ1963 በአዲስ አበባ በተካሄደው የአፍሪካ ህብረት ስብሰባ ወቅት ውድድሩ እንዲካሄድ ከስምምነት ላይ መድረሳቸውን ታሪክ ያወሳል። ህብረቱ ይህንን ተግባራዊ የሚያደርገው ደግሞ በየሀገራቱ ከሚገኙ ብሄራዊ የኦሊምፒክ ኮሚቴዎች ጋር በመሆን ነው። በስምምነቱ መሰረት ውድድሩ በየሁለት ዓመቱ የሚያዘጋጅ ኮሚቴ የሰየሙ ሲሆን፣ እአአ በ1965 የመጀመሪያውን የመላ አፍሪካ ጨዋታዎች በኮንጎ ብራዛቪል እንዲካሄድ አድርጓል። በዚህ ውድድር ላይ 30 ሀገራት በ2ሺ500 አትሌቶቻቸው ተወክለው ሲሳተፉ ግብጽ ደግሞ በርካታ ሜዳሊያዎችን በማጥለቅ የደረጃ ሰንጠረዡን በበላይነት ልትቆጣጠር ችላለች።

ቀጣዩ የመላ አፍሪካ ጨዋታዎችን እንድታዘጋጅ የተመረጠችው ማሊ ብትሆንም በወቅቱ በሀገሪቷ በነበረው የመንግሥት ለውጥ ምክንያት ሊካሄድ ባለመቻሉ ለተጨማሪ ዓመት ሊራዘም የግድ ሆኗል። እአአ በ1971 ሁለተኛውን የመላ አፍሪካ ጨዋታዎች እንድታዘጋጅ ናይጄሪያ ተመራጭ ብትሆንም የዝግጅት ጊዜው አንሷል በሚል እስከ 1973 ሊራዘም የግድ ሆኗል።ከዚያ በኋላ ያሉት ዓመታት የተለመዱት የአፍሪካዊያን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች አንዳንድ መስተጓጎሎች ይከሰቱ እንጂ በየአራት ዓመቱ የተሳታፊ ሀገራትን ቁጥር እንዲሁም ውድድር የሚካሄድባቸውን ስፖርቶች በማሳደግ 13ኛው ላይ ደርሷል። በእርግጥ እንደ ውድድሩ ኦሊምፒክ ከሚካሄድበት አንድ ዓመት ቀድሞ የሚከናወን ቢሆንም በታሪክ ለሁለተኛ ጊዜ የውድድሩ አዘጋጅ የሆነችው ጋና መሰናዶዋን ባለማጠናቀቋ ምክንያት ተራዝሞ የፓሪሱ ኦሊምፒክ ወራት ብቻ እየቀሩት ተካሂዷል፡፡

145 ሚሊዮን ዶላር በወጣበት በዚህ ውድድር ላይ ከ54 የአፍሪካ ሀገራት የተወጣጡና ከ2ሺ600 በላይ የሚሆኑ አትሌቶች በ30 ዓይነት ስፖርታዊ ውድድሮች ለአሸናፊነት ተፋልመዋል። ይህም እአአ በ2019 በሞሮኮዋ ራባት ከተካሄደው የመላ አፍሪካ ጨዋታዎች በአራት ብልጫ ያለው ነው፡፡

አፍሪካዊ ጉዳዮች ላይ ጠንካራ አቋም ያላት ኢትዮጵያም በዚህ ውድድር ከመጀመሪያው አንስቶ ስትሳተፍ ቆይታለች። ይሁንና የምትሳተፍባቸው የውድድር አይነቶች ጥቂት በመሆናቸው ምክንያት በርካታ ሜዳሊያዎችን በማግኘት ስሟን ከሜዳሊያ ሰንጠረዡ አናት ማሳረፍ አልቻለችም። ባለፉት 12 የመላ አፍሪካ ጨዋታዎች ተሳትፎዋም 45 የወርቅ፣ 54 የብር እንዲሁም 75 የነሐስ በድምሩ 174 ሜዳሊያዎችን በማስመዝገብ በደረጃ ሰንጠረዡ 7ኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች።




## ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ
## ጨረታ ቁጥር ሰ/አ/አ/ዲ/ግ/ጨ/003/2016 (ሎት-3 )

በአዲስ አበባ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የሰሜን አዲስ አበባ ዲስትሪክት ኤሌክትሪክ አገልግሎት በስሩ ለሚገኙ የሥራ ክፍሎች እና አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ለአገልግሎት የሚውሉ የ2016 በጀት ዓመት የተለያዩ አይነት የስቴሽነሪ እና ቶነሮች በዘርፉ ከተሰማሩ ድርጅቶች ላይ በግልጽ ጨረታ መግዛት ይፈልጋል፡፡

| ሎት | የዕቃው አይነት | የመዝጊያ ቀን እና ሰዓት | የመክፈቻ ቀን እና ሰዓት | የጨረታ ዋስትና ማስከበሪያ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | A 4 PAPER,26A,37A 59A,80A,81A,90A 64A, TK-3160,BROTHER TN 3417,CEXV42TONNER CARTIRAGE,28*40 Rool Paper post machine | መጋቢት 23 ቀን 2016 ዓ.ም ከቀኑ 8፡00 | መጋቢት 23 ቀን 2016 ዓ.ም ከቀኑ 8፡30 | 42,000.00 (አርባ ሁለት ሺህ) |

1. ማንኛውም በዘርፉ የተሰማራ የታደሰ የንግድ ፈቃድ፣ የተጨ. እ.ታ፣ የግብር ከፋይ መ/ቁጥር እና ከገቢዎች ባለስልጣን ጽ/ቤት ጨረታ ላይ እንዲሳተፉ የሚል ማስረጃ ያለው በጨረታው መሳተፍ ይችላል፡፡
2. ተጫራቾች የመንግስት ድርጅቶች በሚያወጡት ጨረታ ላይ ለመሳተፍ እንዲችሉ በግዥ ኤጀንሲ ድረ-ገፅ ላይ የተመዘገቡ ስለመሆናቸው ማረጋገጫ ማቅረብ አለባቸው፡፡
3. በዚህ ጨረታ ለመሳተፍ ከላይ የተዘረዘሩትን ማስረጃዎች በማያያዝ መወዳደር የሚችሉ ሲሆን ዝርዝር ሁኔታው በጨረታ ሰነዱ ውስጥ ይገኛል፡፡
4. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ማስታወቂያው በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለሎት 3 የማይመለስ ብር 300.00 (ሦስት መቶ ብር) በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ EEU-North AACC. (1000149984384) ገቢ በማድረግ የባንክ ስሊፕ በማስገባት ይዘው ቀርበው የጨረታ ሰነዱን መውሰድ ይችላሉ፡፡
5. አድራሻ፡- ራስ ደስታ ሆስፒታል አለፍ ብሎ በሚገኘው ገተር ህንፃ 2ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 206 ሰሜን አዲስ አበባ ዲስትሪክት ግዥ፣ ሎጅስቲክስ፣ ዌርሀውሲንግ እና ፋሲሊቲ ቢሮ፡፡
6. ተጫራቾች ለጨረታ ዋስትና ማስከበሪያ የሚያቀርቡት የገንዘብ መጠን ከላይ በሠንጠረዡ ውስጥ በተገለፀው መሠረት ሆኖ በባንክ በተረጋገጠ ቼክ ሲፒኦ /CPO/ ወይም በቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና (Bid Bond) ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
7. ተጫራቾች የመወዳደሪያ ሰነዳቸውን በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ ቴክኒካል እና ፋይናንሻል በአንድ ላይ በማድረግ «ኦሪጅናል እና ኮፒ» በማለት በተለያየ ፖስታ በሰም በማሸግ እና ሁለቱን በአንድ ትልቅ ፖስታ በማድረግ ጨረታ ቁጥር ሰ/አ/አ/ዲ/ግ/ጨ/003/2016 (ሎት-3 ) የሚል ምልክት በማድረግ ሎት 3 መጋቢት 23 ቀን 2016 ዓ.ም ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ድረስ ከላይ በተጠቀሰው አድራሻ ለዚሁ ጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት የሚኖርባቸው ሲሆን በሰም ያልታሸገ ኤንቨሎፕ ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ውድቅ ይደረጋል፡፡ በዚሁ ቀን ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ላይ ተዘግቶ በተመሳሳይ ቀን ከቀኑ 8፡30 ሰዓት የሚከፈት ይሆናል፡፡
8. ጨረታው ከላይ በተገለፀው መሠረት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡
9. ተጫራቾች ተጨማሪ ማብራሪያ ከፈለጉ በስልክ ቁጥር +251-111-267138 መደወል ይችላሉ፡፡
10. ዲስትሪክቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ ኤሌክትሪክ አገልግሎት-የሰሜን አዲስ አበባ ዲስትሪክት ጽ/ቤት**




# የጎበዞቹ ምክር ለልጆች

**እየሩስ ተስፋዬ**

ሰላም እንዴት ናችሁ ልጆችዬ? ሳምንቱን በጥሩ አሳለፋችሁ?ጥናት እና ትምህርት እንዴት ነው? ወላጆቻችሁስ እያገዟችሁ ነው? እናተስ እገዛ እንዲያደርጉላችሁ ትጠይቃላችሁ? በጣም ጥሩ! እናንተ ጎበዞች ስለሆናችሁ ትምህርታችሁን በጥሩ ሁኔታ እያስኬዳችሁት እንደሆነ እገምታለሁ። የእናንተ ወላጆች ነገ ጥሩ ቦታ እንድትደርሱላቸው ስለሚፈልጉ በሚገባ እንደሚያግዟችሁም ተስፋ አደርጋለሁ።

ልጆችዬ ኢትዮ ሮቦ ሮቦቲክስ የትምህርትና የስልጠና ማዕከል ከአጋር ተቋማት ጋር በመተባበር ባዘጋጀው «ሁለተኛው የአፍሪካ ሮቦቲክስ ሻምፒዮንሽፕ » ውድድር በርካታ ተማሪዎች እና ወላጆች ተገኝተው ነበር። እኛም በዚህ ውድድር ላይ ተሳትፎ ካደረጉት ተማሪዎች መካከል ለእናንተ ልምዳቸውን እንዲያካፍሏችሁ በማሰብ አነጋግረናቸዋል። ከመልዕክታቸው ብዙ እንደምትማሩ እናምናለን። ያስተላለፉት መልዕክትም እንሆ..

ምስጋናው ታምራት ይባላል። የሰባተኛ ክፍል ተማሪ ሲሆን ሬነሳንስ በተባለ ትምህርት ቤት ነው የሚማረው። እርሱና ጓደኞቹ የሰሩት ሮቦት እቃ ማንሻ ነው። ምስጋናው ለወደፊቱ አንጂነር መሆን ይፈልጋል።ታዲያ የነገ ምኞቱን ለማሳከት ዛሬን ትምህርቱን በጥሩ ሁኔታ እየተከታተለ ይገኛል። ከቴክኖሎጂ ጋር የተያያዙ ትምህርቶችንም ከትምህርቱ ጎን ለጎን እየተማረ ነው። ወላጆቹም ድጋፍ እያደረጉለት ሲሆን «ልጆች አዳዲስ እውቀቶችን እንዲያገኙ ጠንክረው መማር አለባቸው» ይላል።

ሌላኛው በውድድሩ ላይ ያገኘነው ተማሪ እዮብ በፍቃዱ ይባላል።እድሜው አስር ነው። የአራተኛ ክፍል ተማሪ ሲሆን በአቡነ ጎርጎሪዎስ ትምህርት ቤት ነው የሚማረው።በዘንድሮው የአንደኛ የትምህርት መንፈቅ ዓመት አንደኛ መውጣቷ። ሳይንቲስት ለመሆን ፍላጎት ያለው ሲሆን በትርፍ ሰዓቱ በቤት ውስጥ የተለያየ የፈጠራ ሥራዎችን ለመሥራት ይጥራል። ሌሎች ተማሪዎች እንደ እርሱ አንደኛ እንዲወጡ በርትተው ማጥናት እንዳለባቸው ይመክራል።

ልጆችዬ! ተማሪ እዮብ ሌላም ምክር አለው። ምክሩ ምን መሰላችሁ ? ልጆች በፍጹም ጊዜያቸውን በስልክ በጌም (ጨዋታ) እና በማይጠቅማቸው ነገር ማሳለፍ የለባቸውም ይላል። በተጨማሪም ወላጆች ልጆቻቸው የሚፈልጉትን ነገር በመጠየቅ ለነገ ሕይወታቸው የሚጠቅማቸውን ነገር እንዲያደርጉም ምክሩን ይለግሳል።

ናታን በፍቃዱ ዕድሜው አስራ ሁለት ዓመት ነው። የሚማረው ደግሞ በአቡነ ጎርጎሪዎስ ትምህርት ቤት ነው።በውድድሩ ላይ ሮቦቶችን ከጓደኞቹ ጋራ በመሥራት በውድድሩ ላይ ተሳትፏል። እርሱና ጓደኞቹ ሮቦቱን ለመሥራት የሁለት ወራት ጊዜ እንደፈጀባቸው ይናገራል። የሮቦት ኢንጂነር የመሆን ህልም ያለው ተማሪ ናታን፤ በትምህርት የሚያገኘውን እውቀት በቤት ውስጥ በካርቶን ላይ በመሥራት እንደሚለማመድ ይናገራል።ቤተሰቦቹም እገዛ ያደርጉለታል። ናታን በመጀመሪያ መንፈቅ ዓመት ሁለተኛ መውጣት የቻለ ጎበዝ ተማሪ ነው።

በርትቶ ስላጠና ጥሩ ውጤት ማምጣት ችሏል። ሌሎች ተማሪዎች እንደርሱ ጎብዘው ትምህርታቸው ላይ መበርታት እንዳለባቸው ይመክራል። በተጨማሪም በራሳቸው ተነሳሽነት ማጥናት እና ወደፊት መሆን የሚፈልጉትን ነገር በመለየት ጠንክረው መማር እንዳለባቸው ይናገራል።

ሌላኛውን ተማሪ እናስተዋውቃችሁ አይደል ልጆችዬ? በጣም ጥሩ። በረከት ታምራት ይባላል። የአስራ ሶስት ዓመት ታዳጊ ነው። ለወደፊት የአውሮፕላን አብራሪ(ፓይለት) የመሆን ፍላጎት አለው። ታዲያ እርሱ ነገ ፓይለት ለመሆን ዛሬን ምን ማድረግ እንዳለበት ጠንቅቆ ያውቃል። ከትምህርቱ ጎን ለጎን አውሮፕላን አብራሪ ለመሆን የሚረዱ ጽሁፎችን ያነባል። በተጨማሪም ቤት ውስጥ የተለያዩ የፈጠራ ሥራዎችን በመሥራት ሙከራዎችን ያደርጋል።

በዚህ ውድድር ከተሳተፉ ሴት ተማሪዎች መካከል ተማሪ የሁዳድ አብደላ አንዷ ናት። የአስራ አንድ ዓመት ተዳጊዋ በቀኝ አዝማች አንዳርጌ ትምህርት ቤት ትማራለች። የአራተኛ ክፍል ተማሪ ስትሆን በዘንደሮው የመጀመሪያ መንፈቅ ዓመት አንደኛ እንደወጣች ትናገራለች። ለወደፊት የሮቦት ኢንጂነር የመሆን ፍላጎት አላት። ዛሬ ላይ ከሮቦት ጋር የተያያዙ ትምህርቶችን




**በአፍሪካ ሮቦቲክስ ሻምፒዮንሽፕ ውድድር በርካታ ተማሪዎች እና ወላጆች ተገኝተዋል፣**

ከትምህርቷ ጎን ለጎን እየተማረች ትገኛለች። ልጆች ወደፊት መሆን የሚፈልጉትን ለማሳካት በትጋት ትምህርታቸውን መከታተል እንዳለባቸው ትመክራለች። እርሷ ነገ ተምራ በቴክሎጂው ዘርፍ ሀገሯን ለማገልገል ጥረት እያደረገች ትገኛለች።

ናታን ፍቅሩን እናስተዋውቃችሁ አይደል? የሰባተኛ ክፍል ተማሪ ሲሆን የሮቦት ጎማዎችን በመሥራት ከጓደኞቹ ጋር በጋራ በመሆን በውድድሩ ላይ ተሳትፎ አድርጓል። በትምህርቱም የደረጃ ተማሪ ከሚባሉት መካከል ነው። በውድድሩ ላይ ለመሳተፍ ከሌሎች ጓደኞቹ ጋር በመነጋገርና በኅብረት በመሥራቱ ነገሮች እንደቀለሉት ይገልፃል። ሌሎች ተማሪዎችን በኅብረት በማጥናት እና በመተጋገዝ ብዙ እውቀቶችን ማግኘት እንደሚችሉ ይመክራል።

ልጆች በውድድሩ ላይ ተሳታፊ ከነበሩት ተማሪዎች መካከል ጎበዝ የሆኑ ልጆችን በማነጋገር ልምዳቸውን እና ምክራቸውን አጋርተናችኋል። በተለይም በትምህርታቸው እንዴት ጥሩ ውጤት ማምጣት እንደቻሉ ልምዳቸውን በሚገባ ተናግረዋል ብለን እናስባለን። ከእናንተ መካከል በትምህርቱ ደከም ያለ ተማሪ ካለ ትምህርቱ ላይ የበለጠ ማተኮር እንዳለበት ብሎም የወላጆቹን እገዛ መጠየቅ እና በኅብረት በመሥራት ውጤት ማሻሻል እንደሚቻል እንደተገነዘባችሁ ምንም ጥርጥር የለኝም። ልጆችዬ በሌላ ጊዜ ጥሩ ውጤት ስላመጡ ጎበዝ ልጆች የምንላችሁ ይኖረናል። ለዛሬው በዚሁ እንሰነባበት አይደል? እስከ ሳምንት በቸር እንዲያገናኘን በመመኘት ለዛሬው በዚሁ አበቃን።